# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 110 ታኅሣሥ 20 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - በሃዱሽ አብርሃ

# የካንሰር ታካሚዎች ለህክምና እስከ ሁለት ዓመት ወረፋ ይጠብቃሉ

- ለውጭ ሀገር ህክምና በየአመቱ 100 ሚሊየን ዶላር ይወጣል
- አራት የጨረር ሕክምና መሳሪያዎች በመጋዘን ተቀምጠዋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፉ ከመጡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መካከል አንዱ የካንሰር በሽታ ነው፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት ባወጣው መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ በየአመቱ 70 ሺህ ሰዎች በካንሰር የሚያዙ ሲሆን ቢያንስ 50 ሺህ የሚሆኑ ዜጎችም ለህልፈት ይዳረጋሉ፡፡

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ያሉት የካንሰር ህክምና መስጫ ማዕከላት ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ የገንዘብ አቅም ያላቸው ጥቂት ዜጎች ለሕክምና ባህር ማዶ ሲሻገሩ፣ ብዙዎች ግን ወረፋ እየተጠባበቁ ለህልፈት የሚዳረጉበት አጋጣሚ ብዙ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቀውንና ጨረር በማመንጨት ካንሰርን የሚገድለውን ‹‹ሌይነር አክስለሬተር›› የተሰኘ ዘመናዊ የካንሰር ህክምና መስጫ ማሽን እአአ በ2017 ወደሃገር ውስጥ አስገብቷል፡፡

ለጎንደር፣ ለሃይደር፣ ለጅማ፣ ለጥቁር አንበሳ፣ ለጳውሎስ፣ ለሐዋሳና ለሃሮማያ ዩኒቨርሲቲዎች ለእያንዳንዳቸውም አንድ ደርሷቸዋል፡፡ በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክተር ወይዘሮ ሕይወት ሰለሞን እንደገለጹት፣ ሰባቱ ማሽኖች የተገዙት

የካንሰር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደመቀሌ ዳግም በረራ በመጀመሩ መደሰታቸውን መንገደኞች ገለጹ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ለአንድ አመት ተኩል ወራት አቋርጦ የነበረውን ወደመቀሌ የሚደረግ በረራ ዳግም በመጀመሩ መደሰታቸውን መንገደኞች ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “የፌዴራል መንግስት ሕዝብን ከረሃብ በመታደግና መሰረተ ልማቶችን ወደነበሩበት በመመለስ ውጤታማ ሥራ ሰርቷል”

-የሽሬ እንዳስላሴ ነዋሪዎች

**አዲሱ ገረመው**

ሽሬ እንዳስላሴ፡- የፌዴራል መንግስት ሕዝብን ከአደጋ በመታደግና መሰረተ ልማቶችን ወደነበሩበት በመመለስ ውጤታማ ሥራ እየሰራ መሆኑን የሽሬ እንዳስላሴ ነዋሪዎች ተናገሩ፡፡ ነዋሪዎቹ ከዚህ በኋላ ለሠላም እንጂ ለጦርነት የሚከፈል ዋጋ የለም ብለዋል፡፡



በሽረ እንዳስላሴ ከተማ ትናንት ህዝባዊ መድረክ በተካሄደበት ወቅት የውይይቱ ተሳታፊ ወይዘሮ ሀረጓ ኅይቶም እንዳሉት፣ ባለፉት ሁለት ወራት የፌዴራል መንግስት ወደ አካባቢው ከገባ ጀምሮ በርካታ ተግባራትን በውጤታማነት ፈጽሟል፡፡ መሠረታዊ አገልግሎቶች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ከማድረግ ባሻገር በርካቶችን ከረሀብ አደጋ ታድጓል፡፡ ሠላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ትልቅ ዋጋ ከፍሏል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ሠላም ፈላጊ ነው ያሉት ወይዘሮ ሀረጓ፣ ከአሁን በኋላ የሚመለስ ህይወት ባለመኖሩ ያለፈውን ትቶ ስለ ዘላቂው ሠላም ብቻ ማሰብ እንደሚገባ

“የፌዴራል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አበራ ለማ

## በበጋ መስኖ ስንዴ እርሻ ከ973 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

- 106 ሚሊየን ሄክታር በፍራፍሬና ስራስር ልማት ይሸፈናል

ገጽ 4



## “ዳቦ በሚፈለገው ልክ እየቀረበ ባለመሆኑ ተቸግረናል”

- የዳቦ አከፋፋዮችና ተጠቃሚዎች

## “እጥረቱን ለመቅረፍ በየክፍለ ከተማው ሁለት ዳቦ ማምረቻዎች ይገነባሉ”

-የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ

ገጽ 3













ዜና

# በመዲናዋ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች መስፋፋታቸው የቱሪስቶችን ቆይታ በማራዘም ገቢን እያሳደጉ ነው

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- አዳዲሶቹ የቱሪስት መዳረሻዎች የቱሪስቶችን ቆይታ የማራዘም ፋይዳቸው የጎላ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡

የቢሮው የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክተር አቶ ዓምደማርያም ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በመዲናዋ ዙሪያ የተገነቡት ዘርፈ ብዙ አዳዲሶች የቱሪስት መዳረሻዎች አሉ፡፡

የተገነቡትና እየተገነቡ ያሉት አዳዲሶቹ የቱሪስት መዳረሻዎች በመዲናዋና በሀገር ደረጃም የቱሪስቶችን ቆይታ በማራዘም በኩል ፋይዳቸው ትልቅና በቆይታቸው መልካም ገጽታን እንዲመለከቱ የሚያደርጉ ናቸው ብለዋል፡፡

በቱሪስትነት ከአጎራባችና የውጭ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ጎብኚዎች በከተማዋ በአንድ ቀን ቆይታ ብቻ ሲሰላ አንድ ሰው በአማካኝ በቀን ወደ 340 ዶላር የሚሆን ገቢ ማስገኘት ያስችላል ሲሉ ዳይሬክተሩ



ፎቶ - ገበዩ ገብሬ

አቶ ዓምደማርያም ማሞ

ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በፊት በነበረው የቱሪስት ፍሰት ሂደት አዲስ አበባ እንደመሸጋገሪያ ሆና ስታገለግል እንደነበረች የገለጹት ዳይሬክተሩ፣ አሁን የአብርሆት ቤተ-መጻህፍት፣ አንድነት፣ ወዳጅነትና እንጦጦ ፓርኮችን ገንብታ እራሷን የቻለች የቱሪስት መዳረሻ መሆን ችላለች ብለዋል፡፡

ቱሪስቶቹ አዲስ አበባ በሚኖራቸው ቆይታ አዳዲሶቹ መዳረሻዎች በርካታ ቀናቶችን እንዲቆዩ ማድረግ ያስችላል ብለዋል፡፡

በመዲናዋ 18 ሙዝየሞችና 22 የሚደርሱ ፓርኮች እንዳሉ የጠቆሙ ሲሆን፣ መዳረሻዎቹ የተሟላ መሰረተ-ልማት ሲኖራቸው ጎብኚዎች በርከት ላሉ ቀናት ከተማዋ ከትመው እንዲቆዩ ያስችላሉ ብለዋል፡፡

የቱሪስት ቆይታ በተራዘመ ልክም በከተማና ሀገር ደረጃ ያለው የውጭ ገንዘብ እጥረት እየተቀረፈ እንደሚመጣ አመላክተዋል፡፡

መዳረሻዎቹ ብሔርን ከብሔር ጋር የምናዋህድባቸው ናቸው፤ ለጉብኝት ከሀገራት ለሚመጡትም ቱባ ባህላችን የምናስተዋውቅባቸውና አወንታዊ ገጽታን የምንገነባባቸው ናቸው ሲሉም አክለው ተናግረዋል፡፡


የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ከማበራከት አንፃርም የክልል መንግስታትና ሰራተኞች ወደ አዲስ አበባ መጥተው በመዲናዋ የተገነቡትና እየተገነቡ ያሉት አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች እንዲጎበኙ የማድረግ ስራም በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በቅርቡ ከደቡብ ክልል የመጡ አመራሮችና ሰራተኞች ለሁለት ቀናት ሙሉ በከተማዋ ተዘዋውረው እንዲጎበኙ መደረጉ የዚሁ አንድ አካል ነው ብለዋል፡፡

መቀመጫቸውን በመዲናዋ ካደረጉት በተጨማሪ በሀገሪቱ ሰላሳ ሶስት የሀገራችን ዩኒቨርሲቲዎችም በተመሳሳይ ሁኔታ አመራሮችና ሰራተኞቻቸውን ለጉብኝት እንዲልኩና ያሉንን ሀገራዊ የቱሪስት መዳረሻ እንዲያወቁ ለማድረግ እየተሰራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

በተመሳሳይም የባንኮችና ሌሎች ተቋማት የሀገር ሀብት የሆኑትን የቱሪስት መስህቦች እንዲያውቁ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ለአዳዲሶቹ የቱሪስት መዳረሻዎችም ሆነ በአጠቃላይ ለዘርፉ እንደትልቅ ተግዳሮት የሚወሰድ የበጀት እጥረት ችግር ነው ሲሉ ዳይሬክተሩ ተናግረው፣ የቱሪዝም ፈንድ ቢኖር ዘርፉ የብዙ ገቢ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን፣ በብዙ ኢንቨስት ሊደረግበት የሚገባና የተሟላ መሰረተ-ልማት ሊዘረጋለት የሚገባ መሆኑንም መክረዋል፡፡



# ባለፉት 3 ዓመታት አንድ ሺህ ለሚበልጡ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ ተሰጥቷል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ዓመታት ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የቡና ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ባለፉት ሶስት ዓመታትም ከአንድ ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የቡና ላኪነት ፈቃድ አግኝተዋል፡፡

የቡና ላኪነት ፈቃድ ከወሰዱት አርሶ አደሮች መካከል ከ100 በላይ የሚሆኑ ቡናቸውን በቀጥታ ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርቡም ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮ በጀት ዓመት 360 ሺህ ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 2 ቢሊየን ዶላር ገቢ ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ባለስልጣኑ ባለፉት አራት ዓመታት የሪፎርም ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል ያሉት ምክትል ዳሬክተሩ፤ የቡና ምርት ጥራትን ማስጠበቅ፡ የግብይት ስርዓቱን ማዘመንና በምርቱ ላይ እሴት መጨመር ምርታማነቱን ማሳደግ መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡

በሪፎርሙ በቡና ግብይት ላይ ከፍተኛ እድገት በማምጣት የውጭ ምንዛሬ እንዲጨምር ተደርጓል ያሉት ኃላፊው፤ ለአብነትም ባለፈው በጀት ዓመት 302 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ አንድ ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን አስታውሰዋል፡፡

የሪፎርም ስራዎች መተግበር ከጀመሩ ወዲህ ባሉ አራት ዓመታት ወደ ውጭ የተላከ የቡና ምርት በ104 ሺህ ቶን እድገት ማስመዝገቡንም ነው የገለጹት፡፡

ባለስልጣኑ የዓለም የቡና ገበያ ተለዋዋጭነትን መሰረት በማድረግ ተጨማሪ የገበያ መዳረሻዎችን የማፈላለጉን ስራ በትኩረት እያከናወነ መሆኑን እንደ ኤዥያ ባሉ አካባቢዎች አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋት እንቅስቃሴ መጀመሩን መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል፡፡

# የአኗኗር ሥርዓትን ያሻሻለው የውሃ ፕሮጀክት

ጌትነት ተስፋማርያም



በገጠር መንገዱ አውራ ጎዳና ላይ ብን ብን የሚለው አቧራ የተሽከርካሪ ጎማ በሚነካው ሰዓት ይበልጡን ወደላይ ይጎናል። የመንደሩ ቤቶች ደግሞ በአካባቢው አቧራ ምክንያት ሽሯማ መልክ ተላብሰዋል።

በነዚያ የመንደሩ ጎጆዎች የሚኖሩ ህጻናት ደግሞ ፊታቸውን በልብሳቸው በአጠቃላይ ለንጽህናቸው የሚሆን ውሃ ካላገኙ ትራኮማ፣ ኮሌራ ሌላም ሌላም በሽታ በቀላሉ ሊያጠቃቸው እንደሚችል መገመት አይከብድም።

ይሁንና የነገሌ አርሲ ገጠራማ አካባቢ ነዋሪዎች ንጽህናቸውን ለመጠበቅ የሚረዳ የንጹህ ውሃ አቅርቦት ባለመኖሩ ለዓመታት ከተለያዩ በሽታዎች ጋር ኖረዋል። በተለይ ከውሃ ወለድና ከንጽህና ጋር ለተያያዙ በሽታዎች ተጋልጠው መቆየታቸውን የሚናገሩት የአካባቢው ነዋሪዎች ወይዘሮ ጠጀቱ ሻላና አሊይ መሐመድ ናቸው።

ቀድሞ ውሃ በአካባቢያችን ስለማናገኝ የሁለት ሰዓት እግር መንገድ ከተጓዝን በኋላ ከብቶች ከሚጠጡባት ምንጭ የደፈረሰ ውሃ በ20 ሊትር ጀሪካን ቀድተን እንመጣለን። ያቺ ውሃ ለምግብ ማብሰያ እንኳን ስለማትበቃ ንጽህናችንን በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅና እራሳችንን ከሽታ ለመከላከል አቅም አልነበረንም ይላሉ።

አሁን ላይ ግን ችግራችን ተቃሏል። ምክንያቱም በተገነባልን የውሃ ፕሮጀክት የተነሳ ደጃፋችን ላይ ንጹህ ውሃ አግኝተናል። ከዚህ በኋላ እኛም ሆነ ልጆቻችን በኮሌራና በተለያዩ በሽታዎች የመጠቃት ዕድላቸው ይቀንሳል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በነገሌ አርሲ የጎንዲ ጉራቴ ቀበሌ ነዋሪው አቶ ደስታ ከድርና ወይዘሮ ሎሚ ገደፋ በበኩላቸው ቀድሞ የውሃ ፕሮጀክቱ ሳይገነባ አህያና ከብቶች ከሚረጋግጡትና ከሚሸኑበት የምንጭ ቦታ ላይ ውሃ ይቀዱ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ከዚህ ባለፈ አዛውንቶችና ሴቶች ውሃ ለመቅዳት ረጅም ርቀት ስለሚጓዙ ለድካምና ለጊዜ ብክነት ተጋልጠው ቆይተዋል። አሁን ላይ ግን ደጃፋችን ላይ በተዘጋጁልን የውሃ ቦኖዎች የተነሳ ጤናችን ከመጠበቁ ባለፈ ከድካም ተገላግለናል ይላሉ።

አሁን ልጆቻችን ዩኒፎርማቸውን አጥበው ንጽህናቸውንም በየጊዜው እየጠበቁ መማር ይችላሉ። እኛም በተደረገልን ድጋፍ አማካኝነት ባሻን ሰዓት ውሃችንን እየተጠቀምን በጤና መኖር የምንችልበት ዕድል ተፈጥሯል ሲሉ ደስተኛ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

በሃቢታት ፎር ሂዩማኒቲ ኢትዮጵያ የውሃና ንጽህና ፕሮጀክቱ አስተባባሪ ተወካይ አቶ ጉዲሳ ዋቅጋሪ እንደሚያስረዱት፤ ድርጅታቸው ከኮሪያ መንግስትና ከኮይካ (KOICA-GDEF) ባገኘው ድጋፍ በኦሮሚያ ክልል ነገሌ አርሲ ወረዳ ሰባት ቀበሌዎች ከውሃና ንጽህና ጋር የተያያዙ መሰረተ ልማቶችን ገንብቷል።

እንደ አቶ ጉዲሳ ከሆነ በፕሮጀክቱ ከ76 ሺህ በላይ የሆኑ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ እያንዳንዳቸው አንድ መቶና ሁለት መቶ ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ መያዝ የሚችሉ ሁለት የውሃ ማጠራቀሚያና ማከሚያ ሪዘርቫየሮች ቀርሳ ኢላላና ጎዴ በተባሉ ቀበሌዎች ላይ ተገንብተዋል። በተጨማሪም 27 የውሃ ቦኖዎች እና 13 የውሃ መሰረተ ልማቶች መጠገናቸውን ያስረዳሉ።

የውሃ መስመሮችን በመዘርጋትና ነዋሪዎች የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆን በተከናወነው ስራ ከአካባበቢው አስተዳደሮችና ከህብረተሰቡ በትብብር የተከናወነ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ጉዲሳ፤ ህብረተሰቡ በአካባቢው በቀረበለት የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ምስጋናውን እያቀረበ መሆኑን ይናገራሉ።

የውሃና ንጽህና ፕሮጀክቶች ህብረተሰቡ እራሱን ከውሃ ወለድ በሽታና ተያያዥ ችግሮች እንዲጠብቅ ከማድረግ ባለፈ የእንስሶቻቸውንም ጤና ለመጠበቅ የሚረዳ መሆኑን አቶ ጉዲሳ ይገልጻሉ።

በነገሌ አርሲ የተገነቡት የውሃና ንጽህና ፕሮጀክቶች ለህብረተሰቡና ለአካባቢው አስተዳደር የተላለፉ ሲሆን፤ በማህበረሰብ አቀፍ ኮሚቴዎችና በህዝብ ትብብር ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠታቸውን ይቀጥላሉ ሲሉ አስረድተዋል።

ዜና



ዶክተር ይልቃል ከፋለ

## በጦርነቱ የደረሰውን ውድመት መልሶ ለመገንባት መተባበር ያስፈልጋል

### -በደቡብ ጎንደር በጦርነቱ የወደሙ ተቋማትን መልሶ ግንባታ ተጀምሯል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ የደረሰውን ውድመት መልሶ ለመገንባት በአንድነት ቆመን ለተግባራዊነቱ ትብብር ማድረግ አለብን ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለጹ፡፡ በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን በጦርነቱ የወደሙ ተቋማት መልሶ ግንባታ መርሐ-ግብር ተጀምሯል፡፡

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጹሁፍ፤ጦርነት አውዳሚና አጥፊ ነው፤ ኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ የገባችው ኅልውናዋን ለማስከበር እንጂ ፈቅዳ አይደለም።

“ተገደን በገባንበት ጦርነት በርካታ ወገኖችን አጥተናል፣ ከፍተኛ ሐብትና ንብረትም ወድሟል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤በአንድነት ከቆምንና ከተባበርን የወደሙ መሠረተ ልማቶችን በአጭር ጊዜ ከነበረው በተሻለ መልሰን እንገነባዋለን ነው ያሉት።

በአማራ ክልል በሁሉም አካባቢዎች በጦርነት የወደሙ ተቋማትንና መሠረተ ልማቶችን መልሶ ለመገንባትና ለማቋቋም አስፈላጊው ሁሉ ርብርብ እንደሚደረግም አስታውቀዋል።

ርእሰ መስተዳድሩ ይልቃል ከፋለ (ዶ.ር) ህልውናችንን ለማስጠበቅ በገባንበት ጦርነት ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት መድረሱን አመልክተው፤ጦርነቱን ለማቆም በተወሰደው ቁርጠኝነት የሰላም ስምምነት መደረጉን ያስታወሱት ርእሰ መስተዳድሩ ለስምምነቱ ተፈጻሚነት በቅንነት ተቀብለን በቁርጠኝነት እንሠራለን ብለዋል።

ጦርነቱ የአማራና የትግራይን ሕዝብ ክፉኛ ጎድቶ አልፏል ያሉት ርእሰ መስተዳድሩ፤ የደረሰው ጉዳት የሁላችንም ጉዳት ነው፤የአማራና የትግራይን ሕዝብ ትስስር ለመበጠስ የሚደረግ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ መቆም አለበት ብለዋል።

በጦርነቱ ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸው እስከ ትምህርት ቁሳቁስ ወድሞባቸዋል፤ የጤና ተቋማት ወድመዋል፤ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማእከላት ፈርሰዋል፤ ተቋማቱ በተሻለ መንገድ እንዲገነቡ መንግሥት የቻለውን ጥረት ያደርጋል ሲሉ ነው ርእሰ መስተዳድሩ ያረጋገጡት።

የአንድ ሕዝብ ታላቅነት የሚረጋገጠው ችግሮችን በአንድነት መፍታት ሲችል በመሆኑ በጦርነቱ የደረሰውን ውድመት መልሶ ለመገንባት በአንድነት ቆመን ለተግባራዊነቱ ትብብር ማድረግ አለብን ሲሉም ርእሰ መስተዳድሩ ተናግረዋል።

በአንድነት ተረባርበን የመልሶ ማልማት ሥራውን በውጤታማነት ከተወጣን ይኼ ሕዝብ የማይሸነፍና የማይበገር ሕዝብ በመሆኑ ከድህነት የምንወጣበት ጊዜ አጭር ይሆናል ማለታቸውን አሚኮ ዘግቧል።

## “ዳቦ በሚፈለገው ልክ እየቀረበ ባለመሆኑ ተቸግረናል”

- የዳቦ አከፋፋዮችና ተጠቃሚዎች

## “እጥረቱን ለመቅረፍ በየክፍለ ከተማው ሁለት ዳቦ ማምረቻዎች ይገነባሉ”

- የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የዳቦ ፍላጎትና አቅርቦት ባለመጣጣሙ መቸገራቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ የሸገርዳቦ አከፋፋይ ማህበራትና ተጠቃሚዎች ተናገሩ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በበኩሉ እጥረቱን ለመቅረፍ በአማካይ በየክፍለ ከተማው ሁለት የዳቦ ማምረቻዎች እየተገነቡ መሆኑን አስታውቋል።

የሸገር ዳቦ አከፋፋይ የሆኑት አቶ ሰይፉ አቡሙሳ ማህበሩ ተቋቁሞ ወደ ስራ ሲገባ ሸገር ዳቦ በቀን አራት ሺህ ዳቦ ሊያቀርብ ተስማምተው ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን በቀን በአማካኝ 1 ሺህ 800 ዳቦ ብቻ እያቀረበ ይገኛል ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል።

የዳቦው አቅርቦት በማነሱ በቂ ትርፍ እንዳያገኙና የደንበኞቻቸውን ፍላጎት ማሟላት እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው የሚናገሩት አቶ ሰይፉ፤ በአቅርቦት ማነሱ የተነሳ የማህበራቸው የወር ገቢ እንደቀነሰ ተናግረዋል፡፡

ሌላኛዋ የሸገር ዳቦ አከፋፋይ ዓለም በዛ በበኩላቸው፤ የዳቦ አቅርቦቱ በተለይ ጠዋት ላይ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ገልጸው፤ ደንበኞች ደግሞ ጠዋት ላይ ከፍተኛ የሆነ የዳቦ ፍላጎት ስላላቸው ረጅም ሰዓት ተሰልፈው በባዶ ይመለሳሉ ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ከሰዓት በኋላ የደንበኞች የዳቦ ግዥ ፍላጎት አናሳ ነው። በመሆኑም የዳቦ አቅርቦቱ በተለይ ጠዋት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ቢጨምር ስራችንን አትራፊ ከማድረግ ባለፈ የደንበኞችን ፍላጎት ማሟላት እንችላለን ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የሸገር ዳቦ ተጠቃሚ የሆኑት አቶ ታሪኩ ለማ፤ የዳቦ አቅርቦቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ ሳይገዙ የሚመለሱበት ጊዜ እንደሚበዛ ተናግረዋል፡፡

የሸገር ዳቦ ከሌሎች ዳቦ ቤቶች ባነሰ ዋጋ ስለሚገኝ በርካታ ፈላጊ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ጠዋት ጠዋት ረጅም ሰልፍ ተሰልፈን በባዶ እንመለሳለን፡፡ ይህ ደግሞ ለእንግልት ዳርጎናል፡፡ የሸገር ዳቦን እንደሌሎች ምርቶች በማንኛውም ሰዓት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ቢመቻች የማህበረሰቡን ምሬት ማስቀረት ይቻላል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ በበኩላቸው፤ የከተማ አስተዳደሩ የመዲናዋን የዳቦ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ ከግል ባለሃብቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ፤ ከሸገር ዳቦ በተጨማሪ በየክፍለ ከተሞቹ በአማካኝ ሁለት ሁለት የዳቦ ማምረቻዎችን እያስገነባ መሆኑን አስታውቀዋል።

ምክትል ኃላፊው በልደታ፣ በየካና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ግንባታቸው የተጠናቀቁ የዳቦ ፋብሪካዎች ወደ ምርት ሂደት መግባታቸውንም ጠቁመዋል፡፡

በሁሉም ክፍለ ከተሞች እየተገነቡ ያሉ ፋብሪካዎች ሲጠናቀቁ በመዲናዋ ያለው የዳቦ አቅርቦት ማነስ ችግርን በዘላቂነት መቅረፍና የማህበረሰቡንም ፍላጎት ማሟላት ይቻላል ብለዋል፡፡

ምክትል ኃላፊው እንደተናገሩት፤ ሸገር ዳቦ አሁን ላይ በአማካኝ በቀን ከአንድ ሚሊየን እስከ 1ነጥብ2 ሚሊየን ዳቦ እያመረተ ነው፡፡ በቀን የምርት መጠኑን ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊየን ዳቦ ለማሳደግም እየሰራ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን የማህበረሰቡ የዳቦ ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት የሸገር ዳቦ ፋብሪካ ብቻውን አቅርቦቱን መሸፈን አይችልም።

ሸገር ዳቦ ፋብሪካ ስራ ሲጀምር በአዲስ አበባና በዙሪያዋ 212 ተረካቢ ማህበራት ነበሩ ያሉት ኃላፊው፤ አሁን ላይ የማህበራቱ ቁጥር 399 መድረሱን ገልጸዋል። የማህበራቱ መበራከት የሚረከቡትን የዳቦ ቁጥር ያሳነሰ ቢሆንም የምርት መጠኑ ግን አለመቀነሱን ተናግረዋል፡፡

ሸገር ዳቦ ፋብሪካን ጨምሮ በአዲስ አበባ ዳቦ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ቁጥር በአሁኑ ወቅት ስድስት መድረሳቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## አገልግሎቱ ከ900 ሺህ ብር በላይ የሚያወጡ መጽሐፍትን ለሚዛን አማን ህዝብ አበረከተ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ሚዛን አማን፡- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት ከ900 ሺህ ብር በላይ ወጭ የተደረገባቸውን መጻህፍት ለሚዛን አማንና አካባቢው የህዝብ ቤተ መጻህፍትና ትምህርት ቤቶች አበረከተ።

አገልግሎቱ የመጻህፍት ድጋፉን ያደረገው "መጻህፍት ለእውቀት ገበታ፤ መዛግብትና የጽሑፍ ቅርሶች ለዘመን ትውስታ!" በሚል መሪ ቃል በሚዛን አማን ከተማ ለአራት ቀናት በቆየው የንባብ ሳምንት ላይ ሲሆን፤ ለሚዛን አማንና አካባቢው ላሉት የህዝብ ቤተ መጻህፍትና ትምህርት ቤቶች ከ900 ሺህ ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸውን ከአራት ሺህ ሁለት መቶ በላይ የትምህርትና አጋዥ መጻህፍትን አበርክቷል። በሁለተኛ ቀን መርሐ ግብርም ከሁለት ሺህ በላይ ታራሚዎች በሚገኙበት በቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን አማን ከተማ ማረሚያ ቤት የንባብ ቀን ተካሂዷል።

የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ እንደተናገሩት፤ የመጻህፍት ድጋፉ ከአሁን ቀደም በሌሎች ክልሎችም በተመሳሳይ ሲደረግ ነበር። ይህም ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን የመጻህፍት እጥረት ለመቅረፍ ያስችላል።

ከዚህም ባሻገር በየአካባቢው ያሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች የንባብ ልምድ ለማዳበርም አይነተኛ ሚና አለው። ተማሪዎች ከመደበኛ የመማሪያ መጻህፍት በተጨማሪ ለንባብ አጋዥ የሆኑ መጻፍህትን በአቅራቢያቸው እንዲያገኙና እንዲያነቡም ይረዳቸዋል። ድጋፉ በተመሳሳይ በሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎችም ተደራሽ ይሆናል ብለዋል።

የሚዛን አማን ከተማ ከንቲባ አቶ ግሩም ተማም በበኩላቸው፤ የተደረገው ድጋፍ የተማሪዎችን የማንበብ ልምድ እንደሚያዳብር ገልጸው፣ በተለይም መጽሃፍት በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በበቂ ሁኔታ መገኘታቸው በመማር ማስተማሩ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለው ተናግረዋል። ሌሎች ባለ ድርሻ አካላትም መሰል ድጋፎችን በማድረግ አንባቢ ትውልድን ለማፍራት የበኩላቸውን መሰል አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

የመጻሕፍት ልገሳው በተደረገበት ማረሚያ ቤት በመርሃ ግብሩ ላይ ተካፋይ የነበሩት ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ታርመው የወጡት አቶ አማረ ፈንታሁ የማረሚያ ቤት ልምዳቸውን እንደተናገሩት፣ ታራሚ በነበሩበት ሰዓት የመጽሐፍ ድጋፍ እንዳልተደረገ ገልጸው፤ ነገር ግን ለማንበብ በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት ከተለያዩ ቦታዎች ሰዎች መጻሕፍትን እንዲያመጡላቸው በማድረግ ያነቡ እንደነበር አስረድተዋል።

የአሁን ታራሚዎች በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት ዕድሉ ስለተመቻቸላችሁ ጠንካራ የንባብ ባህልን ልታዳብሩ ይገባልም ሲሉ መክረዋል።

በማረሚያ ቤቱ በተካሄደው የንባብ ቀንም የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብት ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ፣ ከሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ዶክተር አብዮት አስረስ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ተወካይ አቶ ወንድሙ ለማ፣ ከቤንች ሸኮ ዞን ሚዛን አማን ከተማ ማረሚያ ቤት ምክትል ኢንስፔክተር አዳሙ መልካሙ፣ መምህራንና ደራሲያን፣ ታራሚዎችና ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።

# በበጋ መስኖ ስንዴ እርሻ ከ973 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል

## - 106 ሚሊየን ሄክታር በፍራፍሬና ስራስር ልማት ይሸፈናል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፡- እስከ አሁን ድረስ በተሰሩ የመስኖ ልማት ስራዎች 973 ሺህ 657 ሄክታር (97 ነጥብ 3 በመቶው ) መሬት በበጋ ስንዴ እርሻ በዘር መሸፈኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። የባለሙያ እና የአርሶ አደሩ የተቀናጀ ስራ መኸር ሰብል አሰባሰብ እና መስኖ ልማት ስራዎች በተቀመጠላቸው አግባብ ተግባራዊ እንዲደረጉ አድርጓል።

የግብርና ሚኒስቴር ህዝብ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ አቶ አበራ ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እስከ አሁን ድረስ በተሰራው ስራ 973 ሺህ 657 ሄክታር ( 97 ነጥብ 3 በመቶው) መሬት በበጋ ስንዴ እርሻ በዘር መሸፈን ተችሏል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በበጋ መስኖ ልማት እና በመኸር ሰብል አሰባሰብ ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በጋ መስኖ ልማት በበጋ ስንዴ እና በመደበኛ መስኖ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በበጋ መስኖ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር በዘር በመሸፈን 52 ነጥብ 82 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። አርሶ አደሩ በቆላ እና በወይና ደጋ አካባቢዎች መኸር ሰብል አሰባሰቡ በመጠናቀቅ ወደ መስኖ ልማት ስራ እየተሸጋገረ በመሆኑ መስኖ ልማቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል። ደጋማ አካባቢዎች ሰብል መሰብሰብ አለመጀመሩን ጠቁመው፤ ተሰብስቦ ሲጠናቀቅ መስኖ ልማቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

እንደ አቶ አበራ ገለጻ ፤ በመደበኛ መስኖ ፍራፍሬዎች እና ስራስር ተክሎች ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ 106 ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈን እየተሰራ ነው። እስከ አሁን ድረስ በተሰራው ስራ 500 ሺህ ሄክታር ታርሷል፣ ከታረሰውም ከ422 ሺህ በላይ ሄክታሩ በዘር ተሸፍኗል።

በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች እና አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ስልጠና እና መረጃ እንዲያገኙ ክልሎች ሁኔታዎችን በመከታተል ተቀናጅተው በመስራታቸው በጋ መስኖ ልማት እና መኸር ሰብል የማሰባሰብ ስራዎች በተቀመጠላቸው አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርጓል፤ ተጠናክሮ ይቀጥላልም ብለዋል።

የመኸር ሰብል አሰባሰቡ ሂደት ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ የሰብል ብክነት በማያስከትል መልኩ እንዲሰበሰብ ዘርፈ ብዙ ስራዎች መሰራታቸውን የገለጹት አቶ አበራ፤ ዘመናዊ ሰብል መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂ መጠቀም በሚያስችልባቸው ቦታዎች በኮምባይነር እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው ብለዋል።

ከዚህ ውጪ ህብረተሰቡ የአካባቢውን ጉልበት በመጠቀም ሰብሎች እንዲሰበሰቡ ለማድረግ ተማሪዎችና መምህራን ጭምር ድጋፍ እያደረጉ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የሚታይ የደመና ክምችት ጉዳት ባያስከትልም በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚሰጠውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የአርሶ አደሩን ሰብል ከብክነት የመታደግ ስራዎች ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት አቶ አበራ፤ እስከ አሁን በተደረገው ሰብል አሰባሰብ ሂደት ከ8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ሰብል መሰብሰቡን አያይዘው ገልጸዋል።

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ትናንት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመቀሌ ተነስተው 11 ሰዓት አካባቢ አዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ የደረሱት ሁለት እህትማማቾች እንደተናገሩት፤ በረራው ዳግም በመጀመሩ አዲስ አበባ ከሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ አድርጓቸዋል።

እህትማማቾቹ አዜብ ለማ እና ሄለን ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በፌደራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶሪያ በተደረገው የሰላም ስምምነት ማግስት በተወሰነው ውሳኔ ያደረጉት ጉዞ ደስተኛ አድርጓቸዋል።

እንደ እህትማማቾቹ ገለጻ፤ ባለፉት ሁለት አመታት በትግራይ በነበረው ጦርነት የተነሳ ህዝቡ በከፍተኛ የሰላም እጦት ችግር ውስጥ ቆይቷል። እነሱም ራሳቸው ከፊል ቤተሰባቸው አዲስ አበባ፤ ከፊሉ ደግሞ ትግራይ ሆኖ ላለፉት ሁለት አመታት ሳይገናኙ ቆይተዋል። በዚህም የተነሳ ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው ቆይተዋል።

አዜብ እንደተናገረችው የጦርነት ጉዳቱ ብዙ ነው። በአንድ በኩል ከቤተሰብ ተለያይቶ ያለምንም ግንኙነት መቆየት አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጦርነቱ የሚደርስ ጉዳት አለ። አሁን ግን ከዚያ ሁሉ ችግር በኋላ ዳግም ሰላም በመስፈኑ ደስተኞች ናቸው።

ይህ የሰላም ስምምነት ወደመሬት ወርዶ በሰላም ለመንቀሳቀስና ለመስራት ህዝቡ ከፍተኛ ጉጉት አለው ያለችው ሄለን በበኩሏ፤ ለዚህም መንገድ መከፈቱ ትልቅ የሰላም እመርታ መሆኑን ተናግራለች።

ጦርነቱ ህዝቡን በገንዘብ፣ በመድሀኒትም ሆነ በምግብ እጦት እንዲጎዳ ያደረገ መሆኑን የገለፁት እህትማማቾቹ፤ በሁለቱ አካላት መካከል የተደረገው ስምምነትም ለመከራው ፍፃሜ ማምጣት የሚያስችል እርምጃ መሆኑን ተናግረዋል።

በተለይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስራ መጀመሩ ለሰላሙም ሆነ ለተራራቀው ቤተሰብ ትልቅ እፎይታ መፍጠሩን እህትማማቾቹ ጠቁመው፤ ይህ ሰላም ዘላቂ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይገባል ብለዋል።

በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ የተመራውና ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችን ያካተተ ቡድን ባለፈው ሰኞ በመቀሌ በመገኘት ከሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች ጋር የተወያየ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ወደመቀሌ የሚያደርገውን በረራ እንደሚጀምር መግለጹ ይታወሳል።

በዚህም መሰረት በትናንትናው እለት ጠዋት የመጀመሪያው በረራ ወደመቀሌ የተደረገ ሲሆን፤ ከሰዓት በኋላም ከመቀሌ ተሳፋሪዎችን በመያዝ አዲስ አበባ መግባቱ ታውቋል።

# “የፌዴራል መንግስት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ተናግረዋል። ከዚህ በኋላ ለሠላም እንጂ ለጦርነት የሚከፈል ዋጋ የለም በማለት፤ የተጀመረው ሠላም ወደኋላ እንዳይመለስ ሕዝቡ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛ መሆኑን ገልጸዋል። ሠላሙን ለማክሸፍ የሚሞክሩ አካላትን መንግስት ክትትል አድርጎ እርምጃ እንዲወስድም ጠይቀዋል። መገናኛ ብዙኃንም የሕዝብን አንድነት ሊያጎለብቱ የሚችሉ ዘገባዎችን በስፋት መስራት አለባቸው ነው ያሉት።

በፌዴራል መንግስት የተከናወነው የነፍስ አድን ሥራው ምስጋና የሚገባው ነው ያለው ወጣት ሠመረ ተኪኤ፤ ጦርነቱ በፈጠረው ችግር ምክንያት ወደ ክልሉ የገቡት አስተባባሪዎች በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሕዝቡን ችግር የመፍታት ሚናቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ገልጿል።

“ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን፤ ሌሎች እኛን ለማፍረስ ብዙ ሠርተዋል። ነገር ግን ኢትዮጵያ መፍረስ እንደማትችል የሠላም ስምምነቱ አረጋግጦልናል” ሲል ወጣት ሠመረ በመድረኩ ተናግሯል።

የስምምነቱን ሂደት ደግፈው እስከመጨረሻው ከመንግስት ጋር እንደሚሰሩ፤ ትራንስፖርት አገልግሎትና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወደ ተሟላ እንቅስቃሴ እንዲገቡ ትኩረት እንዲደረግ ነዋሪዎቹ በውይይቱ ወቅት ተናግረዋል።

በአካባቢው የፌዴራል መንግስት አስተባባሪ አቶ መሐመድ ሱሌ፤ ባለፉት ሁለት ወራት በሽረእንዳስላሴ የፖለቲካ አመራሩ ስምሪት ወስዶ ወደተግባር ሲገባ እንደ አንድ ቁልፍ ግብ ካስቀመጣቸው ጉዳዮች አንዱ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን ማረጋገጥ፤ የኅብረተሰቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ሊያውኩ የሚችሉ ጉዳዮችን በዝርዝር በመለየት አፈጣኝ እርምጃ መወሰድ ነበር እነዚህንም በስኬት ፈጽሟል ብለዋል። መንግስት የኅብረተሰቡን ችግር በመረዳት የእርዳታ እህል የማቅረብ ሥራን እንዳከናወነም ጠቁመዋል።

በጦርነት ከቀዬያቸው የተፈናቀሉ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደቄያቸው እንዲመለሱ መደረጉንና ከመንግስት የአገልግሎት መስጫ ተቋማት መካከል የጤና ተቋማት በፍጥነት ሥራ እንዲጀምሩ መደረጉን ገልጸዋል።

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ ጦርነቱ ባመጣው ዳፋ ምክንያት በርካታ የመንግስት እና የህዝብ ሀብት የፈሰሰባቸው ዋና ዋና የመሰረተ ልማት አውታሮች ወድመዋል። ይሄም የአካባቢውን ማኅበረሰብ ኑሮ ይበልጥ ከባድ አድርጎታል።

ስለሆነም ይህንን ባገናዘበ መልኩና የሕዝብ ጥያቄ ከግምት በማስገባት ችግሮችን በቅደም ተከተል ለመፍታት ጥረት ተደርጓል። በዚህ መሰረት ላለፉት ሁለት ዓመታት በከተማው አገልግሎት መስጠት ያቋረጡ መሰረተ ልማቶችን ስራ ማስጀመር ተችሏል። ለአብነትም የስልክ አገልግሎት ፣ መብራት ሀይል፣ የውሀና ፍሳሽ አገልግሎት እንዲሁም የባንክ አገልግሎት እንዲጀመር ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

# የካንሰር ታካሚዎች...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በ24 ሚሊየን ዶላር ወጪ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ቺፍ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ዶክተር አንዷለም ደነቀ፤ ባግባቡ ከተሰራ ባንከሩን ሰርቶ ማሽኑን ለማስገባት ከአንድ አመት በላይ አይፈጅም ይላሉ። ህንጻው ተገንብቶ፣ ሁለት ማሽን ተክሎ፣ ባንከሩ ተዘጋጅቶ፣ አስፈላጊ ግብአቶችን አስገብቶ ስራ ለማስጀመር እስከ አንድ ቢሊየን ብር ሊፈጅ ይችላል።

ከገቡት ማሽኖችም የጅማ፣ የጥቁር አንበሳና የሃሮማያ ስራ ሲጀምሩ፤ ቀሪዎቹ አራት ማሽኖች በየተቋማቱ እስካሁን በመጋዘን ተቀምጠዋል።

በውሉ መሰረት የማሽን ገጠማ ስራ (ኢንስታሌሽን) እና ተጨማሪ ስራዎች ማሽኑን ያቀረበው ኩባንያ ኃላፊነት ሲሆን፤ የካንሰር ማዕከል (ባንከር)፣ የህንጻ ግንባታና ባለሙያ ማብቃት ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎቹ ኃላፊነት መሆኑንም ዳይሬክተሯ ይጠቁማሉ።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የካንሰር ህክምና ኢንስቲትዩት የካንሰር ማዕከል ኃላፊ ዶክተር አማረ አሰፋ እንደሚሉት፤ የካንሰር ህክምና መስጫ ማሽኑ ስራ ከጀመረ 15 ወራት ሆኖታል። በማዕከሉ በቀን እስከ 107 ሰው፤ በአመት እስከ ሁለት ሺ 500 ሰው ይታከማል፣ ስራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶም በጨረር ብቻ ከአንድ ሺህ በላይ ዜጎች መታከማቸውን ይገልጻሉ።

የጥቁር አንበሳ ማሽን በብልሽት ለሶስት ወራት አገልግሎቱን በማቋረጡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በርካታ ተገልጋዮችን በመቀበል ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደነበረበት፣ እንደአገር የማሽን ህክምና ከሚፈልገው ታካሚ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አለመሆኑንም ይጠቁማሉ።

በሃገራችን በየአመቱ 150 ሺህ ሰው የጨረር ህክምና ይፈልጋል። ይህንን ህዝብ ለማከም ደግሞ ቢያንስ እስከ 200 ማሽኖች እንደሚያስፈልጉ፣ ለህክምናውም ዜጎች በየአመቱ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ እንደሚያደርጉ ይገመታል ሲሉ ዶክተር አማረ ይናገራሉ።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ አቅም ያላቸው ህክምናውን ለማግኘት ወደ ታይላንድ ባንኮክ፣ ቱርክ፣ ሕንድ ይጓዛሉ። ለምሳሌ አንድ ሰው ህንድ አገር ለመታከም ሁለት ወራት ያህል ይፈጅበታል፣ የአልጋና የትራንስፖርት ወጪን ጨምሮ ከ16 እስከ 20 ሺህ ዶላር ይፈጅበታል። ለጨረር ህክምናው ብቻ ደግሞ 32 ሺ ዶላር ይከፍላል።

በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የካንሰር ህክምና ክፍል ኃላፊ ዶክተር ኤዶም ሰይፉ እንደሚናገሩትም፤ አዲሱ ማሽን ስራ ከጀመረ ሁለት ዓመት አስቆጥሯል። በቅርቡ ለሶስት ወራት በመበላሸቱ በርካቶች ተጉላልተዋል።

ችግሩ ተደራራቢ ህክምናውም ውስብስብ ሆኗል። በቀን ከ30 እስከ 40 በወር ደግሞ ከ400 እስከ 500 የሚጠጉ አዳዲስ ታካሚዎች ይመጣሉ። አብዛኞቹ ታካሚዎች የጨረር ህክምና ስለሚያስፈልጋቸው ለጨረር የሚመዘገበው ታካሚ እየጨመረ ይገኛል። አንድ ታካሚ ለህክምናው ስድስት ወራት ይቀጠር የነበረው ዓመት፣ አሁን ዓመት ከስድስት ወራትና ሁለት ዓመታትም ደርሰናል ነው የሚሉት።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ጤና ህክምና ኮሌጅና በሕይወት ፋና ሁሉን አቀፍ ሆስፒታል የአስተዳደርና ልማት ዳይሬክተር አቶ ፊላ አህመድ በበኩላቸው፤ የጨረር ህክምና ማዕከል ስራ ጀምሯል፣ ጎን ለጎን ከፍቃድ ጋር ተያይዞ አስፈላጊ ዝግጅቶች እየተከናወኑ ይገኛሉ ይላሉ።

እስካሁን በጨረር ህክምናው 45 ሰዎች የሕክምና አገልግሎት አግኝተዋል። 20 ሰዎችም ተመዝግበው ህክምና ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ህክምና እና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን ዶክተር አንተነህ ጋዲሳም፤ የማሽን ገጠማ ስራ እያለቀ መሆኑንና ከጨረር ህክምና ውጭ ያሉ ህክምናዎች እየተሰጠ እንደሚገኝ ይጠቁማሉ።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር አሸናፊ ታዘበውም፤ ህክምናው የሚሰጥበት ክፍል /ባንከሩ/ ሙሉ ለሙሉ ማለቁን፣ ለመጀመር ቴክኒሽያኖችና የሰው ሃይል የማሟላት ስራ እየሰሩ መሆኑን ይገልጻሉ።

ጨረታውን ያሸነፈው የማሽን የገጠማ ስራ (ኢንስታሌሽን) የሚሰራው «ኤልስሜድ ኸልዝ ኬር ሶሉሽን» የኢትዮጵያ ወኪል፣ ማኔጂንግ ዳይሬክተርና ባለቤት አቶ ዳዊት ሃይሉ ጨረታው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኩል እ.ኢ.አ በ2015 እንደወጣ ያስታውሳሉ።

በ2016/17 አካባቢ የሐዋሳና የሐረር ሳይቶች ዝግጁ መሆናቸው እንደተነገራቸው ኤልሲ ተከፍቶ ለሰባቱም አስፈላጊ እቃዎች እንዲገቡ መደረጉንም ነው የሚናገሩት።

የሐረማያ፣ የሐዋሳና የጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች ፈጥኖ ወደ ትግበራ ለመግባት የጸጥታ ችግር፣ ከኮቪድ መከሰት ጋር ተያይዞ የእንቅስቃሴ ገደብ መጣሉ ተደማምረው ጫና ማሳደራቸውንም በምክንያትነት ያነሳሉ።

አቶ ፊላ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ አስፈላጊ ግብአቶችን ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት፣ ስራው ለውጭ አካል በመሰጠቱ በራስ ጉዳይ የመጠመድና አስፈላጊ ግብአቶችን ለማስገባትም ችግር ማጋጠሙ ለመዘግየቱ ምክንያት መሆኑን ያነሳሉ።

ዶክተር አንተነህ በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፤ ማሽኑን እአአ በ2017/18 መረከባቸውን፣ በ2019 የገጠማ ስራው መጀመሩን፣ ገጠማውን የሚሰራው አንድ ቡድን በመሆኑ የጥቁር አንበሳንና የጅማን ጨርሶ ወደሐረር እስኪጓዝ መዘግየቱን ይገልጻሉ። ከሶስት ወራት በኋላም ወደ ትግበራ እንደሚገባ ይናገራሉ።

ዘገየ የሚለውን እንደማይስማሙበት የሚናገሩት ደግሞ ዶክተር አሸናፊ ናቸው፤ በእቅዱ መሰረት በጣም ዘገየ የሚባልበት ሁኔታ ላይ አለመሆኑን፣ የተጀመረው፤ የጅማ፣ የሐዋሳና የሀሮማያ ሳይቶች ከተጀመሩ ከዓመት በኋላ የጎንደር መጀመሩንና የዲዛይን ማሻሻያዎችም መደረጋቸውን ይገልጻሉ።

ከሌሎቹ ሳይቶች በተለየም የኒኩሊየር ሕክምና መስጫ አብሮ በመገንባቱ መዘግየት መፍጠሩን፣ የኒኩሊየር ማስወገጃውና የማሽኖቹ ተከላ ተጠናቅቆ እኤአ 2023 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ስራ እንደሚጀምርም ይገልጻሉ።

እስካሁን ጎንደር ሐዋሳ፣ መቀሌና (ሀይደር) ስራ አለመጀመራቸውን የሚያስታውሱት ኤልስሜድ ኸልዝ ኬር ተወካይ አቶ ዳዊት በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ጎንደርና ሐዋሳ በወቅቱ የባንከሩ ሳይት ከተሰራ በኋላ ከፊት ለፊታቸው ትልቅ ህንጻ ስለገነቡ ማሽኑን ለመግጠም አልቻልንም።

አሁን ህንጻው ተጠናቅቆ ወደ ማሽን ገጠማ ስራ ገብተናል። የሐዋሳው በዚህ ወር፣ የጎንደሩ በሚቀጥለው ወር ይጠናቀቃል። የጳውሎስ ግን እስካሁን ገጠማ አልተካሄም። ሆስፒታሉ የካንሰር ማዕከልን ጨምሮ ሰፊ የግንባታ ስራ ላይ ይገኛል።

ስራ ያልጀመሩ ቀሪዎቹን ማሽኖች ወደትግበራ ለማስገባት ተግዳሮት የሆኑብን የሳይቶቹ ዝግጁ አለመደረግ ነው። አሁን ላሉ ለማሽኖች አስፈላጊ መለዋወጫ አስገብተናል። የግንባታ ብቻ ሳይሆን፤ የኤሌክትሪክና ማሽኑ የሚፈልጋቸው ግብአቶች መኖር ወሳኝ ነው ብለዋል አቶ ዳዊት።

መቀሌ የሚገኘው የሃይደር ሪፈራል ሆስፒታል ማሽኑን ከወሰዱ ሰባቱ ተቋማት አንዱ መሆኑንና ከሰሜኑ ግጭት ጋር ተያይዞ ባለፉት ሁለት ዓመታት ያለበትን ሁኔታ እንደማያውቁም፣ አሁን የሰላም ስምምነት በመፈጠሩ ቡድን ተዋቅሮ ያለበትን ሁኔታ እስከምንመለከት መረጃ የለንም የሚለው ምላሽ ወይዘሮ ሕይወትም አቶ ዳዊትም የሚጋሩት ምላሽ ነው።

የታካሚዎቻችንን ቁጥር በእጥፍ ማሳደግ እንፈልጋለን። አንድ ባንከር ዝግጁ አድርገናል፣ የሰለጠነ የሰው ሃይልም አለን፤ ቢያንስ አንዱ ሲቆም ሁለተኛው ማሽን አገልግሎት እንዲሰጥ ተጨማሪ ማሽን ያስፈልገናል የሚሉት ደግሞ አገልግሎቱን እየሰጡ የሚገኙት የጥቁር አንበሳና የጅማ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው።

አስጊነቱ እየጨመረ ባለው በዚህ በሽታ «በዓመት ከ60 እስከ 70 ሺህ ሰዎች በተለያዩ አዲስ የካንሰር አይነቶች ይያዛሉ። በከፍተኛ ቁጥር ተጠቂ እየሆኑ የሚገኙት ደግሞ ሴቶች ናቸው» ይላሉ በጤና ሚኒስቴር የበሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክተር ሕይወት ሰለሞን።

የራዲየሽን ቴክኒሽያንና የባዮ ሜዲካል ኢንጂነሮች ቁጥራቸው መጨምር አለበት፣ በቂ መለዋወጫ በመጋዘን መኖር ይገባዋል፣ ማሽኑ ሲበላሽ የሚያድሱና የሚያስተካክሉ ባለሙያዎችን ቁጥር ማሳደግ ይገባል የሚለውንም ምክረ ሃሳብ ሁሉም ባለሙያዎች ይጋሩታል።

በኢትዮጵያ መዳን እየቻሉ በህክምና እጦት የሚሞቱ በርካታ የካንሰር ታማሚዎች ቢኖሩም ከዚህ በተቃረነ መልኩ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ሃገር ተገዝተው የገቡ የህክምና መስጫ መሳሪያዎች ሙሉ ለሙሉ ወደስራ ሳይገቡ ለአመታት ቆይተዋል። ይህ ደግሞ የሃገር ሃብት ያለአግባብ እንዲባክን ፣ ዜጎች በህክምና እጦት እንዲሞቱ፣ እንዲሁም ጥቂት አቅሙ ያላቸው ዜጎችም በሀገር ውስጥ መታከም እየቻሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ አውጥተው ወደውጭ እንዲሄዱ በማድረግ የሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተገዝተው የገቡት ማሽኖችም በወቅቱ ወደስራ ካልገቡ ሊበላሹና ለተጨማሪ ኪሳራ ሊዳርጉ ይችላሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አገራዊ የሰላም እሴቶቻችን ለምንፈልጋት የበለጸገች አገር ምስረታ ትልቅ አቅም ናቸው

እኛ ኢትዮጵያውያን ዘመናት ያስቆጠሩ ከሰላም ጋር የተያያዙ ብዙ ባህላዊ ፣ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ያሉን ህዝቦች ነን። እነዚህ እሴቶቻችን ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸሩ፣ እንደ አገርም መለያችን ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

የሰላም ጠንቅ የሆኑ ችግሮችን ቀድሞ ከመከላከል የሚጀምሩት እነዚህ አገራዊ እሴቶቻችን፣ የተጣሉ ግለሰቦችን፣ ጎሳዎችን፣ የማህበረሰብ ክፍሎችን ማስታረቅ፣ ቀጣይ ሕይወትን በተሻለ መንገድ በሰላማዊ መንገድ መምራት የሚያስችል አቅም ያካባቱ ናቸው።

የአካባቢ እና የአገር ሽማግሌዎችን፤ የሃይማኖት አባቶችን ፤ የጎሳ መሪዎችን በማክበርና በመታዘዝ አስተምሮ ላይ የተመሰረቱት እነዚህ እሴቶቻችን ፤ እንደ አገር ለመጣንባቸው ረጅም ዘመናት የሕዝብ ለሕዝብ ሰላም መሰረት እንደሆኑም ይታመናል።

እነዚህ እሴቶቻችን በተለይም ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት "በዘመናዊ ትምህርት እና ስልጣኔ" ስም ባጋጠማቸው ፈተና አገር እንደ አገር አደጋ ውስጥ ከገባች ውሎ አድሯል። በዚህም ለመክፈል የተገደድነው ያልተገባ ዋጋ የከፋ ስለመሆኑ የትናንቶቹ ሳይሆኑ የዛሬዎቹም ታሪኮቻችን ተጨባጭ ማሳያ ሆነዋል።

የለውጥ ኃይሉ ይህንን ታሪክ ለመቀየር ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ ለውጡ ለአገራዊ ሰላም መሰረት በሆኑ ፤ በይቅርታ እና በፍቅር እሴቶቻችን ላይ መሰረት አድርጎ እንዲጓዝ፤ በዚህም የቀደሙት ጥቋቁር የለውጥ ታሪኮቻችን እንዳይደገሙ ረጅም ርቀት ተጉዟል።

የለውጥ ኃይሉ አዲስ የፖለቲካ አካሄድም በመላው ሕዝባችን ከፍ ያለ ተቀባይነት የማግኘቱም ሚስጥር ከዚህ የመነጨ ነበር፤ ይሁንና በታቀደው መንገድ መጓዝ የሚችልበት ዕድል ባለማግኘቱ ላለፉት አራት አመታት እንደ አገርና ሕዝብ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ተገደናል።

መንግስት ግጭቶች ከተፈጠሩም በኋላ በሰላማዊ መንገድ በውይይት/በድርድር እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ጀምሮ፣ የአገር ሽማግሌዎች፤ የሀይማኖት አባቶች ፤ የጎሳ መሪዎች፤ የግጭቶች ዋንኛ ተጋላጭ የሆኑ እናቶችን ጨምሮ ጉዳዮችን እንዲሸመግሉና ሰላም እንዲያሰፍኑ ጥሯል።

ከሕወሓት ጋር የነበረውን አለመግባባት ጨምሮ ከሰላም ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮችን በእጃችን ባሉ ባህላዊ፣ መንፈሳዊ እና ማህበራዊ እሴቶች ለመፍታት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ከምንም ነገር በላይ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠትም ለእዚሁ እውን መሆን የሚጠቅሙ እሴቶቻችንን በተግባር እንዲውሉ ቢሞከርም ግጭቶች ማጋጠማቸው ግን አልቀረም።

አጋጣሚውን እንደ መልካም እድል የወሰዱት ታሪካዊ ጠላቶቻቻንም ለችግሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን፤ አገርን እንደ አገር የህልውና ስጋት ውስጥ ገብታ እንደነበር የሚታወስ ነው። በሕዝባችን መካከል ፈጥሮት የነበረው ግራ መጋባትና ግራ መጋባቱ የፈጠረው ፈተና ብዙ ነበር።

በርግጥ ወደ ግጭት የገቡ ፖለቲከኞቻችን ለነዚህ አገራዊ እሴቶቻችን በቂውን ትኩረት መስጠት ችለው ቢሆን ኖሮ፤ ለውጡ ይዞት ከመጣው የለውጥ አስተሳሰብም ሆነ አስተሳሰቡ ሊፈጥርላቸው ከሚችለው ዘላቂ ተጠቃሚነት አንጻር የከፈልነውን ያልተገባ ዋጋ ከመክፈል እንድን ነበር። አዲስ የፖለቲካ ባህል ለመጪው ትውልድ ፈጥረን የምናልፍበትን እድል መፍጠር እንችል ነበር።

በፌደራል መንግስት እና በሕወሓት መካከል የነበረው ግጭት /ጦርነት በደቡብ አፍሪካው የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት እልባት ማግኘቱ ፤ በኋላም በናይሮቢ፤ በመቀጠልም፤ በመቀሌ ያለውጪ አደራዳሪዎች የመንግስትና የሕወሓት ተደራዳሪዎች ፊት ለፊት ተገናኝተው የመነጋገራቸው እውነታ ለራሳችን ችግር መፍትሄው ራሳችን መሆናችንን ፍንትው አድርጎ አሳይቷል።

ይሁንና አሁን ለተጀመረው ሰላም ውጤታማነት በእነዚህ አገራዊ እሴቶቻችን ላይ በመታመን ሕዝባችን እንደ ሕዝብ የሚፈልገውን እና ብዙ ዋጋ የከፈለበትን ሁለንተናዊ ሰላም ለማስፈን ሁላችንም ራሳችንን ለእሴቶቹ ተገዥ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በርግጥ እነዚህ ዘመናት ያስቆጠሩት የሰላም እሴቶቻችን አሁን ላይ የሚታዩ አለመግባባቶችን ብቻ ሳይሆን፤ በቀጣይ ሆና ለማየት ለምንፈልጋት ሰላማዊና የበለጸገች አገር ምስረታ ከምንም በላይ አቅም መሆን እንደሚችሉ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። መጪ ትውልዶችን በእነዚህ እሴቶች በመግራት የትናንት ጥቁር ታሪኮቻችን ማከም የምንችልበትም እድል ሰፊ ነው !


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ውሃ በቦቴ ቸርቻሪዎችና የደራው የውሀ ገበያ

**ሶሎሞን በየነ**

የአገሬው ሰው "ውሃ የሬሳ ማጠቢያ ነው" የሚል ብሂል አለው። ይህም አባባሉ አንድም ሁሉም ሰው በተፈጥሮ ያገኘውን ውሃ ሳይሰስት ለጠማውና ለታረዘ በደግነት መስጠት እንዳለበት የሚያስተምር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ሁሉን ጥሎ የሚያልፍ ፍጥረት በመሆኑ ባለው መኩራራትና መመጻደቅ እንደሌለበት ይልቁንም ያለውን ተካፍሎና ተዛዝኖ መብላት መጠጣት፤ ያለው ለሌለው ማካፈል እንዳለበት የሚያስተምር አባባል ነው።

ከዚህ የተነሳም በቀደሙት ዘመን ኢትዮጵያውያን ባህልና ወግ "ውሃ" ለጠየቀ ሁሉ የማይነፈግ ውድ የተፈጥሮ ስጦታ ነው። በሌላ በኩል ሳይንሱ ደግሞ የሰው ልጅ መላ አካሉ 50 በመቶው ውሃ ሲሆን ሁሉንም የሰውነት አካል የሚቆጣጠረው የአንጎል ክፍል ደግሞ 75 በመቶ ስሪቱ ውሃ እንደሆነ ያስተምራል። ይህም የሚያሳየው ምድር ላይ ለሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ወሳኝ ከሚባሉ የተፈጥሮ ስጦታዎች አንዱና ግንባር ቀደሙ ውሃ ነው።

ዋተር ኤይድ የተባለው ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ የአፍሪካ የውሃ ማማ እንደሆነች ቢነገርላትም በአፍሪካ በንፁህ ውሃ አቅርቦት ችግር በቀዳሚነት ከሚጠቀሱ አገራት የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያ ስትሆን፤ ኤርትራ፣ ዩጋንዳ፣ ሶማሊያና ዲሞክራቲክ ኮንጎ ይከተሏታል። እንደ ድርጅቱ ሪፖርትም በኢትዮጵያ 60 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የንፁህ መጠጥ ውሃ በአቅራቢያው አያገኝም።

አገሪቱም የውሃ አቅርቦትን እያሻሻሉ ካሉ 10 የዓለም አገራት ውስጥ 7ተኛ ደረጃ ላይ ነች። በመኖሪያ አቅራቢያቸው ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማያገኙ 10 አገራት መካከል 2ተኛ፣ በጣም ዝቅተኛ የውሃ አቅርቦት ካላቸው አገራት ደግሞ በ4ተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። በአገሪቱ 39 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ብቻ በመኖሪያ አቅራቢያው ንፁህ የመጠጥ ውሃ ያገኛል። ያ ማለት አብዛኛው ህዝብ ውሃ ለማግኘት ረዥም መንገድ በመጓዝ አስቸጋሪ የለት ዕለት ህይወት ይገፋል ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ በተለይ በመዲናዋ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚነትና ተደራሽነት ከሌሎች የአገሪቱ ክፍልና ከተሞች አንጻር የተሻለ ቢሆንም፤ በሀብታምና በድሆች መካከል ሲታይ ልዩነቱ የትየ ለሌ እየሆነ መጥቷል። በአብዛኛው የከተማዋ የውሃ ስርጭት ሲታይ በአማካኝ በወር አንዴና ሁለት ጊዜ፤ በዛ ከተባለ ሶስት ጊዜ ነው። በተለይ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ከፍተኛ የውሃ እጥረት በመኖሩ ምክንያት የውሀ አቅርቦቱ በወር አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ የሚሆንበት ጊዜ ያጋጥማል።

**የከተማዋ ነዋሪዎችን የውሃ ችግር የተረዱ ጮሌ ነጋዴዎች ውሃ በቦቲ ተሽከርካሪ ጭነው በየሰፈሩ እየዞሩ መሸጥ ከጀመሩ ሰነባብተዋል**

ይህንን የከተማዋ ነዋሪዎችን የውሃ ችግር የተረዱ ጮሌ ነጋዴዎች ውሃ በቦቲ ተሽከርካሪ ጭነው በየሰፈሩ እየዞሩ መሸጥ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ግለሰቦቹ በተለይ በጋራ መኖሪያቤቶች እና ከፍተኛ የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ከነዳጅ ባልተናነሰ ዋጋ ውሃን እየቸበቸቡ ይገኛሉ።

ይህ ውሀ በቦቴ የመሸጡ እውነታ ስራዬ ተብሎ ሰው ሰራሽ የውሀ እጥረት እየፈጠረ ስለመሆኑም የሚያነሱ አልታጡም። በጋራ መኖሪያቤቶች እና ከፍተኛ የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ቧንቧቸው ደርቆና ዝጎ ውሃ በቦቲ ተሽከርካሪ ጭነው ውሃ ፈላጊ እያሉ የሚቸበችቡ ግለሰቦች "ውሃ ከየት አመጡ?" የሚለውንም ጥያቄ ለማንሳት የሚገደዱም ጥቂቶች አይደሉም።

እንደውም በማስረጃ አልተረጋገጠም እንጅ በሀሜት ደረጃ በሀብታሞች ሰፈር ውሃ አትጠፋም ነው የሚባለው። በተጨባጭ ደግሞ ድሃዋና ለፍቶ አዳሪዎች እናት ግን ካለው የኑሮ ውድነት አኳያ ልጆቿን ሻይ አፍልታ ዳቦ በሻይ እንኳ የምትመገብበት ውሃ አጥታ አንድ ጆሪካን ውሃ 20 እና 30 ብር እየገዛች ኑሮዋን "በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ" አድርጎባታል።

አንዳንድ ጊዜ የመንግሥት አካላት በቦቲ ውሃ ጭነው ለህብረተሰቡ በነጻ ሲያቀርቡ የሚስተዋልበት ጊዜ ቢኖርም፤ ውሃ ለማግኘት ባለው ከፍተኛ ሽሚያ፣ በተለይ በጋራ መኖሪያቤት አራተኛ ወለልና ከዚያ በላይ የሚኖሩ አቅመ ደካሞችና አካል ጉዳተኞች ተሻምተው ውሃውን ለማግኘት የሚቸገሩበት ሁንታ ሰፊ ነው።

ውሃውን እንደምንም አገኙ ቢባል እንኳን ውሃውን እቤታቸው ድረስ ለሚያደርስላቸው የጉልበት ሠራተኛ ከፍተኛ ወጪ ነው የሚያወጡት። ስለዚህ ውሃውን ሲገዙ ደግሞ ወጪያቸው እጥፍ ድርብ ነው የሚሆነው።

ከዚህ ባሻገር በቦቲ ተሽከርካሪ ተጭኖ በየሰፈሩና በየሆቴሉ የሚቸበቸበው ውሃ ምን ያህል ለጤንነት ተስማሚ መሆኑ በምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ተፈትሿል? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ ሌላ ችግር ነው።

ከዚህም ባለፈ በከተማዋ የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች አንዳንድ ግለሰቦች ሕጋዊ ፈቃድ አውጥተው ይሆን አይሁን ባይታወቅም የከርሰ ምድር ውሃ አውጥተው ሲሸጡ ይስተዋላል። ይህስ ኅብረተሰቡ በጋራና በእኩልነት ሊገለገልበትና ሊጠቀምበት የሚገባውን የተፈጥሮ ሀብት የግለሰቦች የሀብት ማካበቻ መሆኑ ተገቢ ነው? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።

ምክንያቱም ሁሉም ማህበረሰብ በጋራ ሊጠቀምበት የሚገባውን የአገር ተፈጥሮ ሀብት አንድ ግለሰብ እየሸጠ ሀብት የሚያካብትበት ሌላኛው ደግሞ መንግሥት በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያቀርብለት የሚገባውን ተፈጥሮ ሀብት ባልተገባ ዋጋ ገዝቶ የሚጠቀምበት የሞራል ሆነ የሕግ ግዴታ የለበትም።

በጥቅሉ በከተማዋ የእውነት የውሃ እጥረት ስላለ ነው ወይስ ግለሰቦች በሚፈጥሩት ሰው ሰራሽ የውሃ እጥረት ህዝቡ ላልተፈለገ ወጪና ኪሳራ እየተዳረገ ነው? እንዲሁም ውሃ በቦቲ ተሽከርካሪ ጭነው ውሃ ፈላጊ እያሉ እየዞሩ የሚቸበችቡ ግለሰቦች ውሃውን ከየት አገኙት? ውሃውስ ምን ያህል ለጤንነት ተስማሚ ነው? ምን ያህል ውሃ የመሸጥ ሕጋዊ ፈቃድስ አላቸው በሚሉት ጉዳዮች ላይ ከተማ አስተዳደሩ ጥብቅ ቁጥጥርና ፍተሻ ሊያደርግ ይገባል።

በተጨማሪም ጉዳዩ ተራ ቢመስልም የሰፊውን ማህበረሰብ ውሃ ጠጥቶ የማደር ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ መንግሥት አሁን ላይ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት በያዘው ቁርጠኛ አቋም ዘርፉን ፈትሾ የመዲናዋን የውሃ ችግር መሰረታዊ መንስኤ በመለየት ዘላቂ መፍትሄ ሊያስቀምጥ ይገባል ባይ ነኝ።

# ነፃ ሃሳብ



**በቀምላቸው አበበ ደማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ዛሬም ፖለቲካዊ ትክክለኝነት

ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል መዋቅራዊና ተቋማዊ ሆኖ የተዘራው የጥላቻ፣ የልዩነት፣ የሀሰተኛ ትርክትና የሴራና አሚካላና ኩርንችት ሳያንስ፤ በተቃዋሚዎች፣ በአክቲቪስቶችና በዩቲውብሮች ዕለት ዕለት እንደ ፍላጻ የሚንበለበለው የጥላቻና የልዩነት ፍላጻና ፖለቲካዊ ኢ-ትክክለኝነት ጨርቃችንን ማስጣሉ አልበቃ ብሎ የአገር መሪዎች ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጤፉ ሲሆኑ ማድመጥና እንካ ስላንትያውን ሲቀላቀሉ ማየት ያማል። ለሚዲያ የሚሰጥ ቃለ መጠይቅም ሆነ መግለጫ እንዴት ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ከግምት ማስገባት ይሳነዋል።

የሚታረቁ የማይመስሉ ልዩነቶች በጦዙበት፤ በለውጥ ሒደት ላይ እንዳለ፤ ለአገራዊ ምክክር እየተዘጋጀ፤ የሰላም ስምምነትን ዳር ለማድረስ ደፋ ቀና እንደሚል፤ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ ስርዓት እንዳቆመ፤ በማንነት ፍላጎቶች እና ጥያቄዎች እንደሚሳሳብ፤ የሕግ የበላይነት ክፍተት እንደሚስተዋልበት፣ ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ጭፍጨፋዎች እንደሚፈጸሙበት፤ ወዘተ . አገርና ሕዝብ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት Political Correcteness (PC) የልብ ትርታው መሆኑ ለቅፅበት እንኳ ሊዘነጋ አይገባም። ለውጡ ከባተ ካለፉት አራት አመት ወዲህ እንኳ ብዙ ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፡፡

በገለልተኛ ወገን በጥናት ባይረጋገጥም በለውጡ ተቀባይነት legitimacy ላይ ያስከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአብነት ማንሳት ይቻላል። የሴራ ፖለቲካና የበሬ ወለደ “ ወሬ “ ከፖለቲካ ትክክለኝነት ልምሻ ጋር ተጃምሎ፣ አብሮና ተባብሮ እንደ ሰደድ እሳት ሲዛመት ታዝበናል። በሁለቱ እኩይ ኃይላት መካከል ማለትም በሴራና በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት ያለውን እሳትና ጭድነት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ተከስተው ከነበሩ ግጭቶች አኳያ ያስተውሏል፡፡

> **የፖለቲካዊ ትክክለኝነትን አንድምታዊና ታሪካዊ ዳራ በስሱ ከሸመን በኋላ ወደ አገራችን ፖለቲካዊ መልክዓ አውርደን እንከናነበዋለን። ክንንቡን ግን ለአገራችን ለሕዝባችን ክብር ስንል መልሰን እናወርደዋለን**

የፖለቲካዊ ትክክለኝነትን አንድምታዊና ታሪካዊ ዳራ በስሱ ከሸመን በኋላ ወደ አገራችን ፖለቲካዊ መልክዓ አውርደን እንከናነበዋለን። ክንንቡን ግን ለአገራችን ለሕዝባችን ክብር ስንል መልሰን እናወርደዋለን። ፖለቲካዊ ትክክለኝነት በ1930ዎቹ ጀምሮ ጥቅም ላይ እንደዋለ የተለያዩ በዘርፉ ላይ የተከተቡ ድርሳናት ያትታሉ። ወደ ኋላ ተመልሰን ይሄን ዘመን ስንቃኝ የዘር፣ የሀይማኖት፣ የፆታ፣ ሰብዓዊ መብት፣ የእኩልነት ጥያቄዎቸ ወዘተ . ጮህ ብለው መሰማት የጀመረበት ነበር ።

ፅንሰ ሀሳቡ በዚህ ተመሳሳይ ዘመን ጥቅም ላይ መዋል የጀመረበት መግፍኤም ይሄው ነው። በሌላ በኩል ፅንሰ ሀሳቡ ከግራ ዘመም አይዶሎጂ ማለትም ከሶሻሊስትና ኮምኒስት ርዕዮት ጋር ተያይዞ እንደመጣ ይነገራል። ሆኖም ብያኔው ግን በርዕዮት አለሙ ልክ የተሰፋ ነው። የፓርቲውን ሕገ ደንብ የሚያከብር መሪ ወይም አባል እንደ ፖለቲካዊ ትክክለኛ ይቆጠራል። በ1980ዎቹ አጋማሽ ደግሞ ሀሳቡ ከተለያዩ የስርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ከአካዳሚያዊ ነፃነት ጋር ተያይዞ ይወሳ ነበር። ይሁንና እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1991 ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ በሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የምረቃ ስነ ስርዓት ላይ ስለ “ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት “ አሳሳቢነት ከተናገሩ ወዲህ ፅንሰ ሀሳቡ ከስርዓተ ትምህርት ክለሳ፣ ከምረቃ ስነ ስርዓት ንግግር ደንብ፣ ከጾታና ዘር ጥቃት፣ ወዘተ ጋር መያያዝ ጀመረ፡፡

የፅንሰ ሀሳቡ ተገዳዳሪዎች ደግሞ ከአስተሳሰብ ፖሊስነት thought police እና መልካም ስምን፣ ዝናን ከማጥፋት፣ ከማጉደፍ ( McCarthyism) ጋር ያያይዙታል። ሆኖም ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ፖለቲካን ከሁሉም ማለትም ከሰብዓዊነት፣ ከፍትሐዊነት፣ ከእኩልነት፣ ከግልፅነት፣ ከተጠያቂነት፣ ከመብት፣ ከአብሮነት፣ ከእርቅ፣ ከሰላም፣ ከመነጋገር፣ ከመቀባበል፣ ወዘተ . አስበልጦ የመመልከት መጥፎ አባዜን መሞገት ነው፡፡

ፅንሰ ሀሳቡ ስራ ላይ ከዋለ ከ80 ዓመታት በኋላም ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ዛሬም አወዛጋቢ፣ አነጋጋሪ ነው። በተለይ የአሜሪካው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ በቲዊተርም ሆነ በመደበኛ ሚዲያዎች መግለጫ ከመስጠታቸው በፊት ማንን እንደሚያስቀይም ? የማንን መብት እንደሚጋፋ ? የንግግራቸው፣ የቲውታቸው ትርጉሙ፣ አንድምታው ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው ስለማያመዛዝኑ ከፖለቲካዊ ትክክለኝነት አንጻር በተደጋጋሚ ነጥብ ሲጥሉ ይስተዋላል።

ቲዊት ባደረጉ ለጋዜጠኞች መልስ በሰጡ ቁጥር ፊደላቸው፣ አፋቸው ወለም እያለው ምህረት የማያውቀው ሚዲያም እግር በእግር እየተከተለ ሲያብጠለጥላቸው እሳቸውም አፋቸውን ጣታቸውን መሰብሰብ ቢቸግራቸው እውነቱን መዘርገፍ እንጂ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጉዳዬ አይደለም ማለት ጀመሩ። በእርግጥ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ማለትም ሚዲያ፣ ሕግ አውጭና ተርጓሚ፣ ሲቪል ማህበራት፣ ወዘተ . ባለበት አገር የፕሬዚዳንቱም ሆነ የፖለቲከኞች፣ የጋዜጠኞች፣ የተሚጋቾች፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ ወዘተ . የአፍ ወለምታ ሆነ ፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት ሳይውል ሳያድር በቅቤ ስለሚታሽ ስለሚታረም ያስተዛዝብ ይሆናል እንጂ ያን ያህል ዘላቂ ጉዳት አያደርስም።

ፕሬዚዳንት ትራምፕ ስልጣን ላይ እያሉ አስተዳደራቸው ከሳኡዲ አረቢያ ጎን የሚቆመው” ለምናደርግላት ወታደራዊ እገዛ እጅ በእጅ በጥሬው ስለምትከፍለን ነው። “ በማለት የሳቱት ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የአሜሪካ ወታደሮች ለግዳጅ የሚሰማሩት የአገራቸውን ደህንነት፣ ጥቅምና እሴት ለማስከበር እንጂ በቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይነት mercenaries አይደለም በሚል ከግራም ከቀኝም አቧራ ማስነሳቱ አይዘነጋም ።

ፕሬዚዳንቱ በዚው ሰሞን ትውልደ ሶማሊያዊ ሴት የምክር ቤት አባልንና ሌሎችን ሶስት ባልጀሮቿን “ የምንሰራው ነገር ካልተዋጠላቸው ወደ አገራቸው መመለስ ይችላሉ። ...” ከዚያ በፊት ደግሞ ሴቶችን፣ ቀደምት አሜሪካውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ አፍሪካውያንና ሜክሲኮአውያን በተመለከተ አይደለም ከአሜሪካ ፕሬዚዳንት ትላንት ከተወለደ ብላቴና የማይጠበቅ ነውረኛ ነገር በመናገራቸው ማወዛገቡ ይታወሳል። በአገራችንም በየደረጃው ያሉ የብልጽግና አመራሮች፣ ተቃዋሚዎች፣ አክቲቪስቶች፣ ዩቲውበሮችና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ደረጃው ይለያይ እንጂ እስከዛሬ በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት አሳራችንን እያበዙት ነው።

በሽግግር ወይም በመሰራት ላይ ላለች እንዲሁም አንድነቷ በቋፍ ላይ ለሚገኝ አገር ግን ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የልብ ትረታዋ ነው። እንደ’ ጥላ ወጊ ‘ stroke በድንገት ሊጥላት፣ ሽባ አድርጎ አሳስሮ የአልጋ ቁራኛ ሊያደርጋት ይችላል። ለውጡን ሊቀለብሰው ከፍ ሲልም ወደለየለት ብጥብጥ ሊዘፍቀን ይችላል። ለመሆኑ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ምንድን ነው ? መሪዎች፣ ፖለቲከኞች፣ ተሚጋቾች፣ ጋዜጠኞች፣ ልሒቃን፣ መምህራን፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ አባ እማ ወራዎች፣ በአጠቃላይ ሰዎች አንድን ቡድንም ሆነ የሕብረተሰብ ክፍል የሚያስከፋ፣ የሚያስቆጣ ንግግርም ሆነ ሌላ ያልተገባ ድርጊት መፈፀም እንደሌለባቸው የሚያሳስብ ፅንሰ ሀሳብ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ይባላል።

አገራችንም በፖለቲካዊ ኢትክክለኝነት የምትንጠራወዝ፣ የምትላጋ፣ የምታተኩር (Obssesed) ናት ማለት ይቻላል። በተለይ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ ስድ ከተለቀቀው ማህበራዊ ሚዲያ ጋር ተዳምሮ፤ በአዳራሽ፣ በአደባባይ፣ በመደበኛ ሚዲያ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ ወዘተ . በለውጥ ኃይሉ፣ በተፎካካሪው፣ በተሚጋቹ፣ በልሒቁ፣ በአገር ሽማግሌው፣ በኃይማኖት መሪው፣ በታዋቂ ሰው፣ ወዘተ . በተደረጉ ንግግሮች፣ በተሰጡ አስተያየቶች፣ መልሶች፣ በተላለፉ ንግግሮች፣ በመግለጫዎች፣ ወዘተ . የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ልምሻዎች ተከስተው ያስከፉት ብሔር፣ ኃይማኖት፣ ማንነት፣ አይዶሎጂ፣ “ መስመር “፣ ወዘተ . ነበር። ይሁንና የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ሆን ተብሎም በአፍ ወለምታም ሊጣስ ይችላል።

የቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ “ አክሱም ‘ ለእንቶኔ ‘ ምኑ ነው ? “ እንዲሁም የተወለዱበትን ሕዝብ ስም ጠርተው “... ከዚህ ወርቅ ሕዝብ መፈጠሬ ያኮራኛል። ...” በማለታቸው ከፖለቲካዊ ትክክለኝነት አንጻር ትልቅ ነጥብ አስጥሏቸው ነበር። ፓርቲን ከሕዝብ ጋር ማመሳሰል፣ ገዥ መደብን ከአንድ ብሔር ጋር ማያያዝ፣ አንድን ዕምነት ከአንድ ብሔር ጋር ማቆራኘት፣ ሰንደቅ አላማን ከአንድ ቤተ ክርስቲያንና ጎሳ ጋር ማመሳሰል አንድ ማድረግ እንደ ዜጋም እንደ አገርም ሁል ጊዜ የምንስታቸው የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ኢላማዎች ናቸው፡፡

ይሁንና የአገራችንም ሆነ የውጭ አንዳንድ ልሒቃን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የንግግርና የሀሳብ ነፃነትን እንደሚገድብ ያወሳሉ። የሜሪ ላንድ ዩኒቨርሲቲው ዳን ሞለር ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የንግግር ነፃነት የመገደብ ጉዳይ ሳይሆን ነፃነቱ የሌላውን መብት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ማንነት፣ ወዘተ . በማይነካ፣ በማያንቋሽሽና በማይሸረሽር መንገድ የመጠቀም አግባብ ነው ሲሉ ይሞግታሉ። አላማውም:-

1ኛ . ተጋላጭ፣ ተገላይ እና በታሪክ አጋጣሚ ተጠቂ የሆኑ የሕብረተረብ ክፍሎችን መከላከል፡፡

2ኛ . ሕዝቡ የሚወያይባቸው፣ የሚነጋገርባቸው ርዕሰ ጉዳዮችን በማረቅ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቂ እንዳይሆኑ መስራት፡፡

3ኛ . በዜጎች መካከል ቁጣን፣ ግጭትን፣ ጥላቻን የሚቀሰቅሱ ንግግሮችን መከላከል መሆኑን ያሳያሉ ፡፡

ይሁን እንጂ ዳን ቀለል ባለ ምሳሌ ሲያስረዱ አንድን የሕብረተሰብ ክፍል ዝቅ የሚያደርግ የታሪክ የመማሪያ መፅሐፍት እንዲታረም መጠየቅ የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡

እንደ ታዋቂው የኢኮኖሚክስ ባለሙያ ግሌን ሎሪ ያሉም ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ሀሳብን የመግለፅና የንግግር ነፃነትን እንደሚገድብ አድርገው የሚወስዱ አሉ። ሎሪ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት የሚቃወሙበት ሌላው መከራከሪያ ራስን መመርመር ማቀብ (self cencorship) ያስከትላል በሚል ነው። የጀርመኑ ፖለቲከኛ ፊሊፕ ጄኒንገር ስለናዚ ዘመን ጀርመናውያን በማውራቱ ብቻ የናዚ ደጋፊ ወይም ፀረ -ፂወናዊ እንዳልሆነ እየታወቀ በመናገሩ ብቻ ከፖለቲካ ህይወቱ እንዲገለል ተደርጓል፡፡

የውሾን ነገር ያነሳ ውሾ በሚል መሆኑ ነው። የዋሽንግተን ከንቲባ ሹመኛም በአንድ ወቅት ጓደኞችን “ niggardly “ (ቆንቋኖች) ብሎ መሳደቡ ቁጣ በመቀስቀሱ ከኃላፊነቱ በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ተገዷል። ከዚህ ከዚህ አንፃር ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ስንመዝነው ለምዕራባውያን ለቅንጦት የቀረበ ሊመስል ይችላል እንደኛ በለውጥ በሽግግር ላይ ላለ አገር ግን የህልውና እንዲሁም የሞት ሽረት ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**እንደ መውጫ**

በአገራችን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን በማበረታታት ረገድ ገዥው ፓርቲ ብልጽግና የአንበሳውን ድርሻ እና ቀድሞ ተነሳሽነቱን በመውሰድ አርዓያ ሊሆን ይገባል። በሕገ ደንቡ ላይ በማያሻማና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ስለፖለቲካዊ ትክክለኝነት አስፈላጊነት ሊደነግግ በቀጣይም ለአባላቱና ለደጋፊዎችም የግንዛቤ ማስጨበጫ ተከታታይ መድረኮችን ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

በከፍተኛ ትምህርትም ሆነ በሌሎች ተቋማት የሚገኙ ልሒቃን በፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ምንነትና አስፈላጊነት ላይ ሀሳብ በመለዋወጥና ችግሩን ከእነ መፍትሔው በማመላከት የዜግነት ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የድርሻቸውን ከመወጣት ባሻገር የፖለቲካዊ ትክክለኝነት ጥያቄን የሚያስነሱ ጉዳዮችን በመለየት መሪዎቻቸው በመግለጫዎቻቸው በንግግሮቻቸው በቅስቀሳቸው ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን ታሳቢ እንዲያደርጉ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸውም ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል፡፡

ሚዲያው በአርትኦት ፖሊሲው ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን በማካተት ኃላፊነቱን ለመወጣት አበክሮ መስራት ይጠበቅበታል። እንደ ዜጋ ደግሞ ሁላችንም የምንፅፈው፣ የምንናገረው፣ የምንስለው፣ የምናዜመው፣ የምንቀርፀው፣ ወዘተ . የሌላውን ወገን ታሪክ፣ ባህል፣ እሴት፣ ሀይማኖት፣ ማንነት፣ ወዘተ . የመያናንቅ፣ የማያንኳስስ እንዲሁም በሌላው ቁስል ላይ እንጨት የማይሰድ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባናል፡፡

የሰለጠነ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እስክንጨብጥ፤ የዴሞክራሲያዊ ተቋማት በአግባቡ እስኪጎለብቱ፤ በመንግስት አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚው መካከል ያለው ግንኙነት ሚዛናው እስኪሆን ፖለቲካዊ ትክክለኝነትን የሙጥኝ ብሎ መያዝ ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም። ስንከተለው የነበረ አገዛዝ ያመጣብን መለያየት መጠራጠር ሳያንስ በፖለቲካዊ ኢ-ትክክለኝነት አገር ልትታመስ ሕዝብም ሊደናገር አይገባም፡፡

ፖለቲካዊ ትክክለኝነት አሁኑኑ ! ! !

# ወቅታዊ

# ‹‹ከተማ ላይ አመራር ብቻ ሳይሆን ባለሙያ እና ባለሀብት ጭምር ሙስና ይፈፅማል››

**አቶ መሐመድአሚን የሱፍ**
**የኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ**

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**በሀገሪቱ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ከሚካሄድባቸው ከተሞች መካከል አንዷ ናት- የኮምቦልቻ ሪጆፖሊታን ከተማ አስተዳደር። በአሁኑ ወቅትም ከ50 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ኢንቨስትመንት እየተካሄደባት ነው። የዝግጅት ክፍላችንም ከጦርነት ማግስት ባለሀብቶችን ለመሳብና ወደቀድሞ እንቅስቃሴዋ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገች ከምትገኘው የከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በዚህች ከተማ በየጊዜው ከንቲባዎችን ጨምሮ አመራር የሚቀያየርባት ከተማ ናት። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ገምግማችኋል?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** ኮምቦልቻ ከተማ ላይ ብቻ ሳይሆን ይህ በብዙ ከተሞች ይስተዋላል። በጥናት የተደገፈ ባይሆንም ብዙ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው የከተሞች በየጊዜው ፈጣን የሆነ ዕድገት መኖሩ ነው። ህብረተሰቡ በርካታ ጥያቄዎችን ያቀርባል። ከመሰረተ ልማት፣ ማህበራዊ መስተጋብሮችና ኢኮኖሚያዊ ብሎም ፖለቲካዊ አንድምታ ያላቸው ጉዳዮች ይበዛሉ። በመሆኑም አመራሩ ጫና ይበዛበታል። ስለዚህ በራሱ ምክንያት ወይንም በአፈፃፀም ማነስ ሥራውን ሊለቅ ይችላል። በዚህ የተነሳ እስካሁን እንደ ሀገር ጠንካራ የከተማ አመራር መፍጠር አልተቻለም። ከተማን መምራት ትልቅ እውቀትና ጥበብ ይጠይቃል፡፡

ሌላው ኪራይ ሰብሳቢነት ነው። ከተማ ላይ አመራር ብቻ ሳይሆን ባለሙያ እና ባለሀብት ጭምር ሙስና ይፈፅማል። ባለሀብቶች አመራሩ የሆነ ጉዳይ እንዲፈፀምለት እጅ መንሻ ያቀርቡለታል። ይህንን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ከባለሙያዎችና ከአንዳንድ የሚዲያ አክቲቪስቶችና መሰሎቻቸው ጋር በማበር የስም ማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ይገባሉ። ይህም አመራሩ ተረጋግቶና መሬት ይዞ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡

ጥሩ የከተማ መሪ እንዲኖር ከተፈለገ ህብረተሰቡ አመራሩን ሊደግፍ ይገባል። በአጋጣሚ የእኔንም ጥያቄ ጭምር ስላነሳህ በደንብ ማውራት ተገቢ ነው። እኔ ስሠራ የነበረው ከቀበሌ ጀምሬ ነበር። በልምዴ በከተማዋ ውስጥ ብዙ ቦታ ላይ ስሠራ የቆየሁ ቢሆንም አሁንም ግን ብዙ የማላውቃቸው ነገሮች አሉ። ስለዚህ አንድ አመራር ተረጋግቶ እንዲሠራ ከላይኛው መዋቅር እስከ ህብረተሰቡ ድረስ ባለው አሠራር ድጋፍ ያስፈልገዋል። ይህ የማይሆን ከሆነና በየጊዜው አመራር የሚቀያየር ከሆነ የከተማዋ የተወሰነ ችግርን ለማቃለል ይቸግራል።

**አዲስ ዘመን፡- ከተማዋን ከድህረ ጦርነት በኋላ እየመሩ ነው። አልተቸገሩም ?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** ከድህረ ጦርነት በኋላ ብዙ ነገሮች ፈትነውናል። በጥቅሉ አመራር ማለት ለራስ ሳይሆን ለሌሎች መኖር ነው። ከአመራር ቅንነት ይጠበቃል። ቁርጠኛ መሆን ይፈለጋል። እኔ ከተማዋን ለመቀየር ጥረት አደርጋለሁ፤ ትልልቅ ለውጦች እንዲመጡም ቁርጠኛ ነኝ፡፡

ይህ አካባቢ አንድ የመውጫ መንገድ ነው። በዚህ አካባቢ በአማካይ አንድ ቤተሰብ ከግማሽ ሄክታር መሬት በላይ የለውም። ነገር ግን ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ሥራ ፈላጊ ለዚያውም የተማረ ወጣት አለ። ስለዚህ ትልቁ መስራት ያለብን ኢንቨስትመንትና ፋብሪካ ላይ ነው። ነገር ግን ይህን ለመስራት የጋራ ጥረት ይጠይቃል። ይህ ሥራ በአንድ ግለሰብ የሚመራ አይደለም። የከተማዋ ከንቲባ ጥረት፣ የከተማዋ አመራሮች አሰራርና ታማኝነት፣ የክልሉ አመራሮች ድጋፍ፣ የሀገሪቱ ፖሊሲ ወሳኝነት አላቸው። አንዳንዱ ነገር ለመግለፅ አስቸጋሪ ነው፤ በአጠቃላይ ሲታይ ግን ከድህረ ጦርነት በኋላ ብዙ ፈተናዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከድህረ ጦርነት በኋላ በምን ተፈተናችሁ?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** በብዙ ነገሮች ተፈትነናል። የመጀመሪያው የከተማዋን የሰላምና ፀጥታ ሁኔታ ማስተካከል ፈታኝ ነበር። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ከፀጥታ መዋቅሩ፣ ከአመራርና ከህብረተሰቡ ጋር ተናቦ በመሥራት በርካታ ነገሮችን ማስተካከል ተችሏል። በአሁኑ ወቅቱ አስተማማኝ ሆኗል። ይሁንና የሰላምና ፀጥታ ስራ በአንድ ቀን ተሰርቶ የሚጠናቀቅ አይደለም። በየጊዜው ንቃትና ጥንቃቄ የሚፈልግ ሥራ ነው። ይህም በመሆኑም እንደአስፈላጊነቱ መሠራት ያለባቸው ተግባራት ይከናወናሉ፤ በመከናወንም ላይ ናቸው። ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡ ትልቅ ድጋፍ እያደረገልን ነው። እኛም እንደ አመራር ነገሮችን ትኩረት ሰጥተን እየሰራን በመሆኑ ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኮምቦልቻ ከተማ ከፀጥታው ችግር በተጨማሪ በከተማዋ ከፍተኛ የሆነ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያና የሰዎች ዝውውር የሚስተዋልበት መሆኑ ይገለፃል። ይህን ፈተና አሁን መሻገር ተችሏል?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** ሰላምና ፀጥታ የመጀመሪያ ችግር ሆኖ የነበረው መዋቅሩ በተደራጀና ግልጽ በሆነ አቅጣጫ እየሰራ አልነበረም። በመሆኑም በሙሉ አቅም እየተሰራ አልነበረም። ሁለተኛው መንግስት ያላስታጠቀው ኢ-መደበኛ ኃይል በከተማዋ ውስጥ በብዛት ነበር። ይህ ለስራው ከፍተኛ ጫና ይፈጥር የነበረ በመሆኑ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር። ስለዚህ ትልቁን ሥራ ሰርተናል የምንለው መዋቅራችን በተደራጀና ግልጽ በሆነ መንገድ ሥራውን መስራት ማስቻላችን ነው፡፡

ሁለተኛው ከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሰውን ኢ-መደበኛውን ኃይል በማወያየት አብዛኛውን ወደ ትክክለኛ መስመር እንዲገባ ተደርጓል። ከዚህ በላይ የሆኑትን ደግሞ በህግ አግባብ መጠየቅ ተችሏል። ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በከተማዋ ውስጥ መንግስት ያላወቀው የታጠቀ ኢ-መደበኛ ኃይል እንደ ፈለገ ጥይት አይተኮስም። ጥይት ያለአግባብ ቢተኮስ የሚጠየቅበት ህግ አለ። የከተማችን ምክር ቤትም ፀጥታውን የሚመራበት የራሱን መመሪያ አውጥቷል። ይህም ከሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ጋር እንዳይጋጩ ታስቦና ጥንቃቄ ተደርጎበት እየተሰራበት ነው፡፡

ሌላው የከተማዋ ፈተና የነበረው ህገ-ወጥ ንግድ ነበር። በሦስት ወር ብቻ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ቅጣት ጥለናል። ግባችን ቅጣት መጣል ባይሆንም ህግና ደንብ መከበር ስለነበረበት ነው። ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ጎዳና ላይም ሆነ በከተማዋ ውስጥ የሚከናወን ህገ ወጥ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል።

ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን በተመለከተ በየቀኑ ሰዎችን እንይዛለን፤ በየቀኑም ሪፖርት ይደርሰናል። ሌሊቱን ሙሉ ጠንካራ ኬላ ጥበቃ እየተደረገ በመሆኑ በየቀኑ አዳዲስ ሪፖርት አለ። ይሁንና ይህን ችግር ለማስቆም ከችግሩ መነሻ ወይም ከምንጩ መሥራት አለበት። ወደ አረብ ሀገራት በህገ ወጥ መንገድ የሚሄዱት በብዛት ከኮምቦልቻ ከተማ ሳይሆን በዙሪያው ያሉና የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ነው። በእነዚህ ቀበሌዎች ህገ ወጥ ደላሎች ገብተዋል። ነገር ግን ኮምቦልቻ በሁሉም አቅጣጫ መውጫ ስለሆነች ይያዛሉ። ስንይዛቸው ምክር አገልግሎት ሰጥተን ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ እናደርጋለን። ህገ-ወጥ ደላሎችንም በህግ አግባብ እንዲጠየቁ እናደርጋለን። ነገር ግን እነዚህ ደላሎችና ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች መረጃ በማጥፋት ይሰራሉ። በመሆኑም ዋነኛውን ደላላ ማግኘት ወይንም ከምንጭ ለማወቅ ይቸግራል፡፡

ይሁንና ህገ ወጥ የሰዎችን ዝውውር ችግር ለመፍታት



ፎቶ፡- ክፍለዮሐንስ አንበርብር

እኛ የምንሰራው ሥራ ብቻ ወይም በኬላ ላይ ፍተሻ ብቻ ማስቆም አይቻልም። እንደ ክልልም ሆነ እንደ ሀገር ከባድ ፈተና በመሆኑ የተለየ ስትራቴጂ መነደፍ አለበት ብዬ አምናለሁ። ይህ ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ከተፈለገ እንደ ሀገር ከላይ እስከ ታች ያለው መዋቅር ሊሠራበት ይገባል።

በአጠቃላይ ግን የኮምቦልቻ ከተማን ሰላም ለማስጠበቅ የሚጠበቅብንን ሁሉ እያደረግን ነው። ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ይዘው ይተናኮሱ የነበሩትን አደብ ማስገዛት የተቻለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እጅግ ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። በጦርነቱ ማግስት በከተማዋ ውስጥ 12 ሰዎች ተገድለው፤ ገዳዮችን መያዝ አልተቻለም ነበር። አሁን መግደል አይደለም የግለሰቦች ዕለታዊ ግጭት ጭምር ሪፖርት ይደርሰናል። ለዚህም የፀጥታ መዋቅራችን በትጋት እየሰራ ነው።

ህገ ወጥ ንግድንም መስመር ማስያዝ የተቻለ ሲሆን፤ ከተማዋ በህገ ወጥ ነጋዴዎች እንዳትጨናነቅ ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው። ኮምቦልቻ ከተማ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መናኸሪያ እንዳትሆን የከተማዋን የፀጥታ መዋቅር ከማጠናከር በላይ ኬላ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል። ሌላው የከተማዋ ኢንቨስትመንት ለማጠናከርና ባለሀብቶችን ለመሳብ ትኩረት የሰጠነው የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ነው። ከዚያም አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችንም ማሟላት ላይ ትኩረት አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ከተማዋ ባለሀብቶችን ሊያማልሉ የሚችሉ ምን የተለዩ መሠረተ ልማቶች አሉ?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** የሰላም ሁኔታን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ውሃ፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦት፣ መንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን እየገነባን ነው። ለምሳሌ በኮምቦልቻ ከተማ ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ በመመደብ የኮምቦልቻን ከተማ ከ15 እስከ 20 ዓመት ችግር የሚፈታ የውሃ ፕሮጀክቶችን እየሰራን ነው። ይህ አንዱና ለባለሀብቶችም ሆነ ለከተማዋ ነዋሪዎች እፎይታ የሚሰጥ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስተር ዐቢይ አሕመድም ወደ ኮምቦልቻ ሲመጡ ካቀረብናቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ የመብራት ችግር እንዲፈታ እና የባቡር ፕሮጀክቱ ወደ ተገቢው ሥራ እንዲገባ ነው። ይህም ባለሀብቶችን የሚስብ ይሆናል። እነዚህ በአንድ ላይ ሲደመሩ የከተማችን ዕድገት ከማፋጠንም በላይ እንደ ሀገር ጥልቅ ውጤት የሚያስገኙ ይሆናሉ ብለን እናምናለን፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ ኮምቦልቻ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጧና መገኛዋ በጣም ምቹ ነው። ለጅቡቲ ወደብ፣ ለክልል ዋና ከተማ፣ ለሀገሪቱ ዋና ከተማ አማካይ ቦታ ያለች ናት። በተጨማሪም ሥራዎችን መሥራት የሚችል የተማረና ከፍተኛ የሆነ የወጣት ኃይል ያለባት ከተማ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ነች። እነዚህ ነገሮች ተደማምረው የከተማዋን ዕድገት ማፋጠን ይቻላል። በመሆኑም እኛ በደንብ ከሠራን በሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን በዓለም ካርታ ላይ የኢንዱስትሪ ማዕከል መሆን እንችላለን። ለዚህ ግን ቁርጠኛ አመራር ይጠይቃል፤ ጠንካራ ሥርዓትም መዘርጋት ያስፈልጋል። ህዝብና መንግስትም መናበብ አለባቸው። በአጠቃላይ ከጦርነት በኋላ ብዙ ፈተናዎችን አልፈን ወደ ሥራ ከገባን በኋላ ብዙ ለውጦችን ማስቀጠል ችለናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ ተቋርጠው የነበሩ የልማት ፕሮጀክቶች አሁን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-**በጦርነቱ የተነሳ የተቋረጡት በርካታ ፕሮጀክቶች ናቸው። ተቋርጠው የነበሩ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ እየተደረገ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሚሰራው የነበረውና ሰባት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የመተላለፊያ ድልድይ እየተሰራ ነው። ይህ ድልድይና አቋራጭ መንገድ ሦስቱን የኢንዱስትሪ መንደሮች የሚያገናኝ ሲሆን 800 ሚሊዮን ብር የተበጀተለት ነው። ከዚህም ሌላ የከተማ አስተዳደሩ በዓለም ባንክ ፈንድ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አሉት። 200 ሚሊዮን ብር በላይ ተጀምረው የነበሩ የካልቨርት፣ ካናል፣ ጠጠር መንገድ ሥራዎችና፣ መናኸሪያና የመሳሰሉ ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል። በዚህ ዓመትም 230 ሚሊዮን ብር ሥራ ይዘን ወደ ግንባታ ገብተናል። በዚህ ዓመት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ዜጎች ቤት እንሰራለን። በአረንጓዴ ልማት ከተሞችን የማስዋብ ስራዎችንም በስፋት የምንሠራ ይሆናል። በዚህ ዓመት ከተማዋ ውስጥም በርካታ የግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ።

በዚህ ዓመት የ‹‹ቦርከና ወንዝ›› ፕሮጀክት ወደ ሥራ ይገባል። የመጀመሪያው ዙር ጥናት ይካሄዳል። ኮምቦልቻ የመዝናኛ ማዕከል የምትሆነው ከቦርከና ወንዝ ግራና ቀኝ ያለውን ቦታ በማልማት ነው፡፡

የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ለመገንባት የሚያስችልና በከተማ አስተዳደሩ የሚመራ ሥርዓት እየዘረጋን ነው። በዚህም የተነሳ ክልሉ የሚያወቀው የመንገድ ጽህፈት ቤት ተብሎ የተቋቋመ ኢንተርፕራይዝ አለ። በፊት የነበሩን ማሽኖች በጦርነቱ ወቅት ተወስደዋል። በአሁኑ ወቅት ግን በራሳችን አቅም ለመስራት እየገባንበት ነው፡፡

ከዓባይ ባንክ ጋር የ220 ሚሊዮን ብር ብድር ውል ገብተን በዚህ ዓመት ሁለት ዶዘር፣ 8 ሲኖ ትራክ፣ ግሬደር፣ ሎደር፣ ሎቤድና ሌሎች ተሽርካሪዎችን ገዝተን ለማስገባት በአሁኑ ወቅት የጨረታ ሂደት ላይ ነን። ይህንንም በሦስት ወር ውስጥ እንፈፅመዋለን ብለን እናምናለን። ይህ ደግሞ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ለመገንባት የማንንም ፈቃድና እገዛ ሳንፈልግ በራሳችን መንገድ የምናከናውነው ይሆናል። ይህ በድምር ውጤት ሲታይ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በከፍተኛ ደረጃ የሚያቃልል ሲሆን መሰረተ ልማቶች በመሟላታቸው ባለሀብቶችን በስፋት ለመሳብ ያግዛል የሚል እምነት አለን። እኛ ተቋም ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥተናል። ከዚህም በተጨማሪ ግብዓት አሟልተን ወደ ሥራ እየገባን ነው። ይህ ማለት የከተማችን ችግር በራሳችን እየፈታን ነው። ሆኖም ከተማችን ከዚህ በላይ ልማት ያስፈልጋታል።

ሌላው መብራት ነው። የመብራት መሰረተ ልማቶች በዋናነት በፌደራል መንግስት የሚሰራ ቢሆኑም መንግስት ቀድሞ የነበሩ ኃይል ተሸካሚ ምሰሶዎች ሙሉ ለሙሉ በአዲስ ምሰሶዎች እንዲቀየሩ ተደርጓል። ይህ የመብራት ችግርም ይፈታሉ። እነዚህ ችግሮች ሲስተካከሉ ኢንቨስትመንቱን ያሳድገዋል፡፡

ከተማዋ በ200 ዓ.ም የመንገድ መብራት ተሰርቶላት ነበር። ይሁንና ግን የተሰራበት መንገድ የጥራት ችግር ስለነበረበት እስከዛሬም ድረስ አይሠራም። በመሆኑም ጉዳይ አከራካሪ ስለነበር ፍርድ ቤት ድረስ ሄዶ በኮንትራክተሩ እና በክልሉ የህግ ክፍል መካከል ክርክር ሲካሄድ ነበር። ሆኖም ችግሩ ለብዙ ዓመታት ሊፈታ አልቻለም። በመሆኑም የከተማ አስተዳደሩ በአዲስ መንገድ በ79 ሚሊዮን ብር በመበጀት አዲስ መንገድ እየሠራ ነው። ከዚህ ቀደም መንገዶቻችን ጨለማ ስለሆኑ ወንጀሎች ተበራክተው ነበር። ህብረተሰቡ በዚህ የተነሳ ቅሬታ ያቀርብ ነበር። በመሆኑም በመንገድ መብራቶች ጥሩ ስራ ጀምረናል፤ አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በርካታ ባለሀብቶች በከተማዋ መዋዕለ ንዋይ ቢያፈሱም ማህበረሰባዊ ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸውን ህብረተሰቡ በቅሬታ ያነሳል። ይህን ችግር ለምን መፍታት አልተቻለም?**



**ከተማችን ከሚገባው አኳያ ኢንዱስትሪዎች አልመጡም። በአሁኑ ወቅት በሙሉ አቅም የሚሰሩት 33 ፋብሪካዎች ብቻ ናቸው**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** በኮምቦልቻ ከተማ የሚከናወን ልማት ሁሉ ለከተማዋ ብቻ ይውላል ማለት አይደለም። ለምሳሌ ቢ.ጂ.አይ ኢትዮጵያን ብንወስደው በዓመት ለከተማዋ የሚከፍለው 200 እስከ 300 ሺ ብር ነው። ሲጭንና ሲያወርዱ ደግሞ የተወሰነ ሚሊዮን ብር እንሰበስባለን። ከዚህ ውጭ የሚከፈለው ለክልሉ መንግስትና ለፌደራል መንግስት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ባለሀብቶች ሁሉ ለከተማዋ ይከፍላሉ ማለት አይደለም። ሁሉንም ማህበራዊ ኃላፊነቶችን ይወጣሉ ወይም አይወጡም ብሎ በአንድ ላይ መጨፍለቅ አይቻልም።

እኛ ከተማችን ከሚገባው አኳያ ኢንዱስትሪዎች አልመጡም። በአሁኑ ወቅት በሙሉ አቅም የሚሰሩት 33 ፋብሪካዎች ብቻ ናቸው። ሌሎች ገና በግንባታ ሂደት ላይ ናቸው። ሌሎቹ ማሽነሪ ተከላ ላይ ናቸው። በመሆኑም ገና በሺዎች የሚቆጠሩ መኖር አለባቸው። በአሁኑ የከተማችን የሪጆፖሊታንት አስተዳደርና መዋቅር እስከ 30 ኪሎ ሜትር ድረስ ይሰፋል። ይህንን አካባቢ በሙሉ ከኢንዱስትሪና ፋብሪካ ጋር ማስተሳሰር አለብን ብለን እናምናለን፡፡

እንግዲህ አሁን ያሉትን የተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸው እየተወጡ ነው ወይ? ብለን ካየን ገና ናቸው። በትንሹ የጀመሩ አሉ። ከነጭራሹ ያልጀመሩ አሉ። አካባቢን በመበከል የሚሰሩም አሉ። ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ያልተወጡትን ወደተግባር እንዲገቡ እየጎተጎትን ነው። የሚጠበቅባቸውን መሥራት አለባቸው ብለን እናምናለን። ነገር ግን ሁሌም ማጨናነቅ ከጀመርን ደግሞ ሥራውን ትተው እንዳይወጡም መጠንቀቅ ይገባል። ከምንም በላይ የሚፈጥሩት የሥራ ዕድልና ዜጎቻችን ተጠቃሚነት ብሎም እንደ ሀገር ያለውን ፋይዳ በሚገባ መገንዘብ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ ውስጥ በአካባቢ ብክለት የሚታሙና ነዋሪዎች ቅሬታ የሚያነሱባቸው ኢንዱስትሪዎችን በተመለከተ ምን ይሳሉ?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** በዚህ ላይ አመራሩ በትኩረት መሥራት አለበት። አንዳንድ ፋብሪካዎች እንደዚህ ዓይነት ችግር አለባቸው። ነገር ግን በርካቶች የሚጠቀሙት ኤሌክትሪክ ስለሆነ በአካባቢ ብክለት አይታሙም። ተረፈ ምርት አወጋገድ ላይም ጠቃሚ የሆኑ አሉ። ለምሳሌ ከቢራ ፋብሪካ የሚወጣው ተረፈ ምርት ለእንስሳት አርቢዎችና አድላቢዎች ትልቅ ጥቅም አለው። ነገር ግን በየቦታው የሚበተንና የሚቀመጥ ሲሆን አደብ ማስያዝ ተገቢ ነው። በአሁኑ ወቅት ችግር እየፈጠሩ ያሉት የድንጋይ ከሰል የሚጠቀሙት ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ፍሳሽ ወደ ወንዝ የሚለቁ አሉ። እነዚህን በአግባቡ መቆጣጠር እና መከታተል ይገባል። ይህ ብክለት ከማስከተሉም በተጨማሪ እንደ ሀገርም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከተማዋ የሪጆፖሊታን አስተዳደርና አወቃቀር መሠረት እስከ 30 ኪሎ ሜትር ድረስ ይሰፋል። በዚህ ሂደት ለሚነሱ አርሶ አደሮችና የከተማ ዜጎች ቀጣይ ሕይወትና የካሳ ጉዳይ ዝግጅት ተደርጓል?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-**ከዚህ ቀደም የነበረው የካሣ ሥርዓት ብዙ ችግር የነበረበት መሆኑ ይታወቃል። ይህ እንደ ሀገርም ብዙ ችግር ያስከተለ ነበር። እኛም ያለፈውን ስህተት መድገም አንፈልግም። አርሶ አደሮችም ሆኑ ሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች ከልማቱ ጋር የሚናበቡና የሚጠቀሙ እንጂ የሚገፉ መሆን የለባቸውም። ሕዝቡ ልማቱን በጣም ይፈልገዋል። ትልቁ ችግር ግን እንዴት ማጣጣም አለብን በሚለው ላይ ትኩረት አለማድረጋችን ነው፡፡

አርሶ አደሮችን በአንድ ላይ በመሰብሰብ ወደ ፋብሪካ ወይም ኢንቨስትመንት ለማስገባት ጥረት ቢደረግም ብዙ ፍላጎት የለም። በወቅቱ ካሳ ሲከፈላቸው ትልቅ ብር ይመስላቸዋል። ግን ወዲያውኑ ይጠቀሙበትና ለችግር ይጋለጣሉ፡፡

አሁን እያደረግን ያለው ለልማት ተብሎ የሚነሱ አርሶ አደሮች የሚሰጣቸውን ብር ዝም ብለው እንዳያባክኑት የከተሜነት ሥራ የሚሰሩበትን አማራጭ መፍጠር ነው። ሕይወቱ እንዳይጎሳቆል በቢዝነስ ፕላን መመራት አለበት። ለምሳሌ በዚህ አካባቢ መጋዘን በብዛት ይፈለጋል። ባለሀብቱ ወደ እኛ እየመጣ መጋዘን ልገንባ ብሎ ያስቸግራናል። እኛ ደግሞ መጋዘን ሳይሆን ኢንዱስትሪ ሥራ እንላለን። መጋዘን ካስፈለገ እና ለከተሞች ግድ ከሆነ መጋዘን ገንብቶ ማከራየት ሥራ የአርሶ አደሩ ይሆናል። በተለይም ከመሬቱ ላይ የሚፈናቀለው አርሶ አደር ተጠቃሚ መሆን አለበት።

የገበያ ማዕከል ገንብቼ አከራይቼ እኖራለሁ የሚል አርሶ አደር ከመጣ ይህንንም ዕድል እንሰጣለን። ከዚህ በኋላ በእኛ የተነሳ መጎሳቆል የለባቸውም። አርሶ አደሮችና የልማት ተነሺዎች በዚህ ደረጃ የምንደግፋቸውና ክትትል የምናደርግላቸው ይሆናል፡፡

አንዱን ድሃ እያደረግን ሌላውን ሃብታም ማድረግ አይቻልም። ይህ ባለፉት ስርዓቶች ውስጥ ብዙ ችግር ፈጥሯል። በእርግጠኝነት መናገር የምችለው ግን ይህ ከተማ በጣም የሚያድግ ነው። በመሆኑም መሬት አጠቃቀማችን የተጠና እና ሳይንሳዊ መሆን አለበት። አመራሩ ይህን ከግምት ውስጥ አስገብቶ መስራት አለበት። እኛ አሁን እየተፈተንን ያለነው በህገ ወጥ ግንባታ ነው። እንደ ሀገር መንግስት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ለከተማ መሬትና ህገ ወጥ ግንባታ ነው። የከተማ መሬት በአግባቡ ከተመራ ለሚፈለገው አገልግሎት በሚገባ ማዋልና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት ይቻላል። ሀብት አለን ማለት ብቻ ሳይሆን ሀብታችንን እንዴት እንጠቀም የሚለውን በሚገባ ማወቅ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ቃለመጠይቅ እያደረግን የፌደራል መንግስት ከፍተኛ አመራሮች ወደ መቀሌ ከተማ ገብተዋል። ኮምቦልቻ ከተማ ደግሞ በነበረው ጦርነት በከፍተኛ ደረጃ የተጎዳች ናት። አሁን ያለውን ሰላምን ሲመለከቱ ምን ተሰማዎት?**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** በጣም ደስታ ይሰማኛል። ጦርነቱ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። አሁን ሰላምን ማስቀደም ተገቢ ነው። ጦርነት በጦርነት ብቻ አይቋጭም። የሰላም ስምምነት መደረጉና ሰላም መምጣቱ ትልቅ ፋይዳ አለው። ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚፈልግ ካለ የኢትዮጵያ ጠላት ነው። እኛ በሀገራችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን፡፡

ይህ ሰላም ለእኛ ትልቅ ዕድል ነው። ሰላም ከሆነ ስለ ጦርነት ማሰብ እናቆማለን። ጦርነት ባለበት አካባቢ ኢንቨስትመንት አይመጣም። ሌላው የትግራይ እና የወሎ ሕዝብ የሚዋሰን ነው። የወሎና የትግራይ ሕዝብ ተመልሶ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወቱ እንዲተሳሰር እንፈልጋለን። በምስራቁ ክፍል የአፋር፣ የወሎና የትግራይ ሕዝብ በማህበራዊ ሕይወት የሚተሳሰር ነው። እኔም እንደ ዜጋ ለእነዚህ ሰላም የሚከፈለውን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነኝ። ስለዚህ ሰላሙ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው። በጦርነቱ ብንጎዳም ከትግራይ ሕዝብ ጋር መስተጋብራችንን መቀጠል እንፈልጋለን። እኔም ከልቤ እደግፈዋለሁ። በመሆኑም ከትግራይ ሕዝብ ጋር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር እንፈልጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ በመሆን ማብራሪያ ስለሰጡን እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ መሐመድአሚን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የኢንቨስትመንት ፍሰት እምርታ - በሲዳማ ክልል

**አንተነህ ቸሬ**

ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት የሆነው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት በርካታ ምቹ ሁኔታዎች አሉት። ከተፈጥሮ ሀብቶቹ መካከልም፣ የሀዋሳ ሐይቅ፣ ፍልውሃዎች፣ ለተለያዩ የግብርና እና የቱሪዝም ስራዎች ሊውሉ የሚችሉ መልከዓምድሮቹ ይጠቀሳሉ። እነዚህ የክልሉ ሀብቶች ሀገርን የሚያኮሩ፣ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት ለመሰማራት የሚያነሳሱ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ፀጋዎች ናቸው።

ክልሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት መዳረሻዎች ያሉበትም ነው። ግዙፉ የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የይርጋአለም የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ ይገኙበታል። በመንግስትና በግሉ ዘርፍ የሚንቀሳቀሱ በርካታ ኢንዱስትሪዎችም ይገኙበታል። ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለማሳደግ በ2 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር የማስፋፊያ ግንባታ እየተካሄደለት ያለው የሀዋሳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካም ሌላው የክልሉ የኢንቨስትመነት መዳረሻ ነው፡፡

በመሰረተ ልማት በኩልም ምቹ ሁኔታዎች ያሉበት ነው፤ ከአዲስ አበባ ሀዋሳ ካለው ነበሩ መንገድ በተጨማሪ ከሞጆ ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታ እየተካሄደለት ይገኛል። ከእዚህ መንገድ ግንባታ የሞጆ ዝዋይ መንገድ ግንባታ ተጠናቆ ወደ ስራ ገብቷል። የአውሮፕላን ማረፊያ ባለቤትም ነው።

የሲዳማ ክልል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን በብርቱ የሚደግፉ ምርቶች መገኛም ነው። ከፍተኛ የቡናና ሌሎች ሀብቶችን የያዘው ይህ ክልል፤ እነዚህ ሀብቶች ከክልሉ አልፈው ለሀገርም እየተረፉ ይገኛሉ። የክልሉ ሁለንተናዊ ሀብትና አቅም የባለሀብቶችን ትኩረት እንደሚስብ ይጠበቃል። ስለሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ሀብትና የዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴዎች የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አቶ ዘነበ ለገሰ ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ የሰጡትን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

### የሲዳማ ክልል የኢንቨስትመንት አቅም

የሲዳማ ክልል በርካታ የኢንቨስትመንት አቅሞች አሉት። ክልሉ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶች ይመረቱበታል። ብዙ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ ቡና፣ ወተት፣ ዶሮ፣ ማር፣ ስጋና ሌሎችም ይመረቱበታል። ክልሉ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ከግብርናው በተጨማሪ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እድል የሚፈጥር ነው። በማዕድን ዘርፍ በክልሉ ከ17 በላይ የማዕድን ዓይነቶች ይገኛሉ።

ክልሉ በኢንቨስተሮች ተመራጭ እንዲሆን ከሚያስችሉት ነገሮች መካከል በአንፃራዊነት የተሻለ የመሰረተ ልማት አቅርቦት (ቀበሌዎችንና ወረዳዎችን የሚያገናኙ መንገዶች) አሉት። አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ያለበት ክልልም ነው። ስራ ፈላጊ ወጣት የሰው ኃይል መኖሩ፣ ከአዲስ አበባ ናይሮቢ የሚዘልቀው መንገድ የክልሉን ዋና ከተማ ሐዋሳን አቋርጦ ማለፉ እና ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ያለው መሆኑ ተመራጭ ከሚያደርጉት መካከል ይጠቀሳሉ።

### የኢንቨስትመንት ተግባራት በሲዳማ ክልል

ክልሉን ከሀብቱ ተጠቃሚ ለማድረግ በርካታ የኢንቨስትመንት ልማት ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። በክልሉ አራት የኢንዱስትሪ ክላስተር ዞኖችን በማደራጀት የክልሉን ሀብት ለኢንቨስተሮች የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል። የክልሉን የኢንቨስትመንት አቅምና ምቹ ሁኔታዎችን ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል። በተሰሩ የንቅናቄ ተግባራት አማካኝነትም በርካታ ባለሀብቶች በክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸው ማወቅ ተችሏል፡፡

በሲዳማ ክልል 2ሺ301 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል 1ሺ867 የሚሆኑት በስራ ላይ ይገኛሉ። 464 ፕሮጀክቶች ደግሞ ፈቃድ ወስደው ስራ ባለመጀራቸው ፈቃዳቸው ተሰርዟል። በስራ ላይ ያሉት ኢንቨስትመንቶች ከ52ሺ በላይ ዜጎችን የስራ እድል ተጠቃሚ አድርገዋል። ከግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፎች በተጨማሪ በክልሉ በአገልግሎት ዘርፉ በሆቴልና መዝናኛ፣ በቴክኖሎጂና በሌሎችም ዘርፎችም በርካታ ባለሀብቶች ተሰማርተዋል።

ለኢንቨስትመንት ዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ውጤት ማስመዝገብ ችሏል። ከ1986 እስከ 2012 ዓ.ም ለ26 ዓመታት ያልተመዘገበ የኢንቨስትመንት ካፒታል በ2014 ዓ.ም ማስመዝገብ ተችሏል። በ26 ዓመታት የነበረው የኢንቨስትመንት ካፒታል ሦስት ነጥብ ሁለት ቢሊየን ብር የነበረ ሲሆን፣ የ2014 ዓ.ም ብቻ ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ሆኗል።

በሀገር ደረጃ ትኩረት በተሰጣቸው ጉዳዮች ረገድ ደግሞ በቅርቡ በበጋ ስንዴ ልማት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች 550 ሄክታር መሬት በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል።

በ2015 ዓ.ም ለ400 ባለሀብቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ በሩብ ዓመቱ ለ165 ባለሀብቶች ፈቃድ መስጠት ተችሏል። ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የዘንድሮው የበለጠ ነው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ከ16ሺ በላይ የሆኑ ዜጎችን የስራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ ችለዋል።

በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ አምስት ወራት 160 ሄክታር መሬት ለባለሀብቶች ለመስጠት ታቅዶ 583 ሄክታር መሬት ማቅረብ ተችሏል። የክልሉ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን የፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል። የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ምን እንደሚመስል እና ጉድለቶቻቸው ምን እንደሆኑ ክትትል ይደረጋል። በዚህ ረገድ በአምስቱ ወራት ለ309 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል።

ክልሉ ትኩረት ከሰጣቸው የኢንቨስትመንት አቅጣጫዎች መካከል አንዱ በምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ ለገበያ ማቅረብ ነው። ሲዳማ ክልል በቡና ሀብት ትልቅ አቅም ካላቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች መካከል አንዱ ነው። በክልሉ 700 የቡና ኢንዱስትሪዎች ይገኛሉ። ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የጥራት ውድድር (Cup of Excellence) ላይ ቀርቦ አሸናፊ የሆነው የሲዳማ ቡና ነው። ከዚህ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራበት አቅጣጫ የተያዘው እሴት ጨምሮ ለገበያ የማቅረብ ጉዳይ ነው። በዚህም ቡናን እሴት ጨምሮ የሚያቀርብ የኢጣሊያ ኩባንያ በይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ስራ ጀምሯል።

ከውጭ የሚመጡ ባለሀብቶች በሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ሲሳተፉ ፋይናንስ እና ቴክኖሎጂ ይዘው እንደሚመጡ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ክልሉ ወጣቶች የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ የባለሀብቶችን የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅም ለመጠቀምና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን አቅም ለመገንባትና ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ክልሉ በትኩረት እየሰራ ነው።

በክልሉ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለክልሉ ኢንቨስትመንት ማደግ ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ መሰረተ ልማቶች የተሟሉላቸው ስለሆኑ የባለሀብቶችን ስራ በአንፃራዊነት ቀላልና ፈጣን ለማድረግ ያስችላሉ። ግዙፉ የሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ በማምረቻ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ትልቅ እድልን ይፈጥራል። በግብርናና የግብርና ውጤቶች ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚገቡበት ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ደግሞ እምቅ የሆነውን የክልሉን የግብርና ዘርፍ አቅም ለመጠቀም ያግዛል። የበንሳ መካከለኛ የኢንዱስትሪ ፓርክም ለክልሉ ኢንቨስትመንት ተጨማሪ አቅም መሆን የሚችል የማምረቻ ስፍራ ነው።

### የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ

በክልሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ያለው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ እየተሻሻለ መጥቷል። ይሁን እንጂ በኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ያላቸው ተሳትፎ አሁንም ዝቅተኛ ነው። ለአብነት ያህል በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከሚገኙ አምራቾች መካከል የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሦስት ብቻ ናቸው። ስለሆነም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ትኩረት የሚፈልግ በመሆኑ በቅርቡ ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክን የማስተዋወቅ ስራ በተሰራበት ወቅት 106 የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተመዝግበዋል።

### የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

ክልሉ የባለሀብቶችን ፍሰት ለመጨመር የሚያደርጋቸው ማበረታቻዎች በአዋጅና በመመሪያ በተደነገጉ የማበረታቻዎች (Incentives) አሰጣጥ መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናል። ክልሉ ‹‹የኢንቨስትመንት አዋጅ 1180/2012››ንና ሌሎች ሕጋዊ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ለባለሀብቶች ድጋፎችንና ማበረታቻዎችን ያደርጋል። ቦታዎችን አዘጋጅቶ ለባለሀብቶች ማቅረብን ጨምሮ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ተግባራትን ያከናውናል። ባለሀብቶች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

### የኢንቨስትመንት ተግዳሮቶች

በሲዳማ ክልል በኢንቨስትመንት አፈፃፀም ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል አንዱ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት የወሰዱትን መሬት ለረጅም ጊዜያት አጥሮ ማስቀመጥ ነው። ይህ ደግሞ ባለሀብቶቹ ወደ ስራ ቢገቡ እነሱም ሆኑ ሀገሪቱ የሚያገኙትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዲያጡ ያደርጋል። ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ባለፉት አምስት ወራት ለ68 ፕሮጀክቶች ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። 19 ባለሀብቶች የወሰዱት መሬት ደግሞ ወደ መሬት ባንክ እንዲመለስ ተደርጓል።

የረጅም ጊዜ ብድር ያለማግኘትም ሌላው የኢንቨስትመንት ዘርፉ ተግዳሮት ነው። አልፎ አልፎ የኃይል መቆራረጥ የሚከሰትባቸው ራቅ ያሉ አንዳንድ ወረዳዎች አሉ። የቢሮክራሲ ውጣ ውረዶች የዘርፉ መሰናክል የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች የሉም። ሕጋዊ ሆነው የኢንቨስትመንት ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች በፍጥነት ይስተናገዳሉ።

### እቅዶች

የሲዳማ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋና ዋናዎቹ ቀጣይ እቅዶች የኢንቨስትመንት ፍሰትን ማጠናከር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለሚያደርጉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ልዩ ትኩረት መስጠት ናቸው። በዚህም ዜጎች ከኢንቨስትመንት ዘርፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ዋስትና የሚሰጡ ዘላቂ ተግባራት ይከናወናሉ።

ለዘላቂ የሀገር ልማትና እድገት አስተማማኝ ዋስትና መሆን የሚችሉትን የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል። ሰላም ከሌለ ኢንቨስትመንት የሚታሰብ አይደለም። ሰላምን ለማስፈን የተወሰደው እርምጃ ለባለሀብቶች እንዲሁም ለመላው ህብረተሰብ ተስፋ የሰጠ ነው። ከዚህ አንፃር በሲዳማ ክልል ያለውን ሰላም አስጠብቆ በማስቀጠል የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲያድግ በትኩረት ይሰራል።

በአጠቃላይ በሲዳማ ክልል በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ቢመጡ ክልሉ ባለሀብቶቹን ለማስተናገድ ዝግጁ እንደሆነ የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አቶ ዘነበ ለገሰ ተናግረዋል፡፡



አቶ ዘነበ ለገሰ

**የሲዳማ ክልል በርካታ የኢንቨስትመንት አቅሞች አሉት። ክልሉ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶች ይመረቱበታል። ብዙ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ ቡና፣ ወተት፣ ዶሮ፣ ማር፣ ስጋና ሌሎችም ይመረቱበታል**

# ጎሜ

# ራሳቸው ሰርቀው ራሳቸው ይጠቁሙናል

**ሙሉቀን ታደገ**

> **የሚገርመው የእኛ ሰፈር ሌቦች ደግሞ ሌብነታቸውን ለመደበቅ ሲሉ የሌባ አይን ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ እንዲሉ ራሳቸው ከሰፈራችን የሆነ ነገር ሰርቀው ራሳቸው መሰረቁን ይጠቁሙናል**

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ ከብዙ ቀናት መሰወር በኋላ ዛሬ ሲነጋጋ ፤ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል በሰፋራችን ከሚገኘው ዋርካ ስር ቆሞ ሲጮህ ፤ በይልቃል አዲሴ ድንገተኛ መሰወር ክፉኛ ተጨንቀው የነበሩ የሰፈራችን ነዋሪዎች በሙሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳቸውን በመተው ይልቃል አዲሴ ወደሚጮህበት ዋርካ ስር ተሰበሰቡ ።

አንድም ሰው እንዳይቀር ተብሎ የታወጀ ይመስል የሰፈራችን ነዋሪዎች ከህጻን እስከ አዛውንት ዋርካው ስር ተገኝተዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴ እየደጋገመ ይድረስ ለእግዜሩ እንደቃሪያ ከተሰነግኩት ልጅህ እያለ ይጮኻል። ነገር ግን የዛሬውን የይልቃል ንግግር ማንም በቀላሉ መገንዘብ አልቻለም።

በሰፈራችን ትዕግስቱ አፍንጫው ስር ነው የሚባለው አብሿሙ ከፌ ጉደታ የይልቃልን የንግግር ሚስጢር ማግኘት ስላልቻለ ከይልቃል በላይ ጮኾ ወፈፌው ይልቃል አዲሴን ከንግግሩ አስቆመው።

«የምትለን ነገር ምኑም እየገባን አይደለም። ይህ ሁሉ ሕዝብ የተሰባሰበው የአንተን መሬት ጠብ የማይሉ ትእንቢት የመሰሉ ንግግሮችን ለማዳመጥ ነው። ስለዚህ የምትነግረንን ነገር በስርዓት ንገረን !»ሲል ይልቃልን ገሰጸው።

ወፈፌው ይልቃል አዲሴም አንድ እጁን ወደ ሰማይ በማንሳት «በእጄ ላይ በምትመለከቷት ኤንቨሎፕ ውስጥ አንድ ከእናታችን የተላከች ደብዳቤ ትገኛለች። ዛሬ ከጠፋሁበት በድንገት እዚህ የተገኘሁት ከእናታችን የተላከችውን ደብዳቤ ለእናንተ እንዳነብላችሁ በእናታችን ታዝዤ ነው» ሲል ለተሰብሳቢው ገለጸ።

ይህን ደብዳቤ እንድትጽፍ ያስገደዳት ዋናው ምክንያት አሁን አሁን የምታገባቸው ባሎቿ ራሳቸው ወንጀል ሰርተው ራሳቸው ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ አስከሳሽ፣ ምስክሩም እና ዳኛ እየሆኑ ስላስቸገሯት እንደሆነ ነግራኛለች ።

«ለማንኛውም ደብዳቤው እንዲህ ይላል» አለና ደብዳቤውን ማንበብ ቀጠለ.... ይድረስ ለእግዜሩ እንደቃሪያ ከተሰነግኩት ልጅህ እግዜሩ አንተ አዳምን እና ሄዋንን ፈጠርክ። ብዙ ተባዙም አልክ። እኔም የአንተን ምክር ሰምቼ እና ፍቃድህ ሆኖ ባል አግብቼ ተባዛሁ። ልጆቼም የአንተኑ ምክር ሰምተው እና ፍቃድህ ሆኖ እንደባህር አሸዋ ተባዙ።

ባሎቼ ቶሎ ቶሎ እየሞቱ ብቸገርም እንደፍቃድህ ሆኖ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ አንድ ባል ሲሞትብኝ ሌላ ባል እያገባሁ እየኖርኩ ነው። ልጆቼን የወልድኳቸው ግን ከመጀመሪያው ባሌ ብቻ ስለነበር ክብሩ ይስፋ ዘር የልጆቼን ዘር ከሌላ ዘር ጋር አልቀየጥኩም። ባሎቼ ይቀያየሩ እንጂ እርስቴን ልጆቼ እና ለልጅ ልጆቼ አውርሼ ተቀምጫለሁ። በዚህም ፈጣሪን አብዝቼ አመሰግነዋለሁ።

የእግር እሳት ሆኖ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ የሚያንገበግበኝ ነገር የባሎቼ በየጊዜው መሞት እና እኔም ያለመታከት አንዱ ባል ሲሞት ሌላ ባል ማግባቴ አይደለም። ይልቁንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የማገባቸው የባሎቼ ፀባይ እንጂ።

ከዛሬ 50 እና 60 ዓመታት በፊት ያገባኋቸው ባሎቼ ይብዛም ይነስም ቀና፣ ሩህሩህ፣ ልጆቼን የሚንከባከቡ እኔን አብዝተው የሚወዱ እና ለእኔ መኖር አብዝተው የሚሰሩ ነበሩ። «ጉድ እና ጅራት ከወደ ኋላ ነው» እንዲሉ አሁን አሁን ግን የማገባቸው ባሎች ልጆቼን በሚፈልጉት መንገድ አቧድነው የሚያባሉ፣ የእኔን ጭጉት (ገንዘብ ማስቀመጫ) የሚበረብሩ እና የሚዘርፉ፣ እኔን አግብተው ሲያበቁ በቤታችን የሚፈጠር ችግር ለመፍታት እኔን ማመከር ሲገባቸው ከእናካቴው ከምድረ ገጽ ብንጠፋ ለሚመኙ ጎረቤቶቻችን ማማከርን እንደስልጣኔ የሚቆጥሩ፣ የእኔን የሚስታቸውን የቆየ ጥበብ ተጠቅመው የቤታቸውን ችግር በራሳቸው ከመፍታት ይልቅ «ሳይቸግር ጨው ብድር» እንዲሉ ያልቸገራቸውን ከጎረቤት መፍትሄ ለማግኘት ሲሉ እኔን ለጎረቤት በባርነት አሳልፈው የሚሸጡ ፣ የእኔን እና የልጆቻቸውን ሀብት በስውር የሚዘርፉ፣ ከልጆቻቸው ጉቦ የሚበሉ ናቸው።

የአውሮፓ ቅኝ ገዥ ኢፔሪያሊስቶችን በከፍተኛ ተጋድሎ ከሰፈራችን እና ከእርስታችን ቀጥቅጠው ያስወጡት ልጆቼ ዛሬም ላይ አይለፍላችሁ ተብለው የተረገሙ ይመስላል። ልጆቼ የአውሮፓ ኢፔሪያሊስቶችን ከእርስታቸው ያስወጡ እንጂ ሰርተው ከማደግ ይልቅ በአቋራጭ ዘርፈው መከበርን በሚሹ የእድር እና የእርስት መሪዎች፣ ደላሎች እና ባለሀብቶች ክፉኛ እየተፈተኑ ኑሯቸውም ተመሰቃቅሎ ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ሆኖባቸዋል።

አሁን ላይ ሰፈራችን እና እርስታችን በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ኩነቶች ላይ እድገቶች እንዳይጎበኙት እና ምንም አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳይችል እንደ ጎን ውጋት ቀዝፎ የያዙት እና አንድም እርምጃ ወደፊት መሄድ እንዳይችል ጋሬጣ ሆኖ ከፊቱ የተቀመጠው የማይነቃነቅ ደንቃራ ስርቆት ወይም ሌብነት ሆኖ ሳለ አንድም የሰፋራችን ሰው ይህንን የእድገት ደንቃራ በስሙ ለመጥራት የደፈረ አልተገኘም። ይልቁንም «ሙስና » እያሉ ያሽሞነሙኑታል እንጂ።

ስርቆት ስለምን ይሽሞነሞናል ? ሌብነት ሌብነት ነው! ስለምን የእድር መሪ ስልጣኑን ተጠቅሞ ሲሰርቅ ሙስና የሚል የዳቦ ስም ይሰጠዋል ? ይህ ስህተት ነው። ሌባ ... ሌባ ነው ! ግለሰብ ሲሰርቅ ሌባ ፤ ባለስልጣን ሲሰርቅ ሙስና የሚባል ስም ሊሰጠው አይገባም!

የህግ የበላይነት በአንድ ሀገር የሚረጋገጠው ባለስልጣናት እና ዜጎች በህግ ፊት እኩል ሲሆኑ ነው። ስለሆነም ባለስልጣን ሲሰርቅ ሙስና ብሎ ማሽሞንሞን ተራ ዜጎች ሲሰርቁ ሌባ ማለት የህግ የበላይነትንም የዘነጋ አካሄድ ስለሆነ ሁሉንም ሌባ አልያም ሁሉንም ሙሰኛ ብሎ መጥራት ያስፈልጋል። እንደኔ ግን ሌባን ... ሌባ ! ብሎ መጥራቱ ብቻ አዋጭ ይመስለኛል።

ሌባን ማሽሞንሞን ስል የአንድ በአንድ ትንሽየ የገጠር መንደር የሚኖር ሌባ ታሪክ ትዝ አለኝ። በአንድ በትንሽዬ የገጠር መንደር የሚኖር እጅጉን የሚፈራ አለ ደሴ የሚባል ሌባ ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን አቶ አለ ደሴ የጎረቤቱን በሬ ይሰርቃል። በሬው የተሰረቀው ሰውየም በሬዩ ስለጠፋ የሰፈራችን ሰው ተሰብስቦ ይጠየቅልኝ ሲል በሰፈራቸው የሚገኙ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሽማግሌዎች ይጠይቃል፡፡

ሽማግሌዎችም የቀረበላቸውን አቤቱታ መሰረት አድርገው የሰፈራቸውን ሰዎች በሙሉ ሰበሰቡ። ሽማግሌዎቹም በዚች ሰፈር በባህል «እውስ ማውጣት» የተባለ በሚታወቀው ሌባውን የማፈላለግ ዘዴ ተጠቅመው የአቤቱታ አቅራቢውን በሬ የሰረቀውን ሌባ ማፈላለግ ይጀምራሉ። «በእውስ ማውጣት » ዘዴም በሬውን የሰረቀው ሰው አቶ አለ ደሴ የተባለው አስፈሪው ሌባ መሆኑንም ይደርሱበታል።

ነገር ግን ሌባውን ስለሚፈሩት በሬውን የሰረቀው ሰው አለ ደሴ ነው ለማለት ፈሩ። ምክንያቱም አንደኛ አቶ አለ ደሴ የእነሱንም በሬ ይሰርቃቸዋል። ሁለተኛ አቶ አለ ደሴ ከግብረ አበሮቹ ጋር ተባብሮ ሽማግሌዎቹንም ሊገድላቸው ይችላል። በመሆኑም አቶ አለ ደሴን የፈሩት «እውስ የሚያወጡ» ሽማግሌዎች በሬውን የሰረቀው ሌባው ከዚህ ሰፈር አይደለም ብለው አረፉት ።

በዚህ የተበሳጨው ፍትህ ፈላጊው በሬው የተሰረቀበት ገበሬ ምን ቢል ጥሩ ነው ... እናንተ ሌባው ከሰፈር የለም እያላችሁ ብትናገሩም ሌባው ግን ከዚህ ሰፈር «አለ» ሲል በአሽሙር ሌባው አቶ አለ ደሴ መሆኑን ተናገረ። ሌባ የጠፋው ሰው በአሽሙር የመናገሩ ዋና ምክንያት አቶ አለ ደሴ ከበሬው መጥፋት ለሚብስ ችግር እንዳይዳርገው በመስጋት ነበር ።

የሰውየው ቅኔ የገባቸው ሰዎችም ሌባውን እያወቁት ትክክለኛውን ፍርድ መፍረድ ባለመቻላቸው እያዘኑ «ሌባውማ «አለ» ። ግን ሌባውን እንዴት አድርገን ማወቅ እንችላለን ? » አሉ ይባላል።

በእኛ እድር እና ሰፈርም እየሆነ ያለው ይሄው ነው። ሌባው አለ። የሰፈራችን ሰዎችም ሌባው ማን እንደሆነ ያውቁታል። ግን ማን ደፍሮ የሌባውን ስም ይናገር። ምክንያቱም የሰፈራችን ሰዎች የሌባውን ስም ቢናገሩ ሌባው ለከፋ ችግር ይዳርገናል ብለው ይሰጋሉ።

የሚገርመው የእኛ ሰፈር ሌቦች ደግሞ ሌብነታቸውን ለመደበቅ ሲሉ የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ አይነት እንዲሉ ራሳቸው ከሰፈራችን የሆነ ነገር ሰርቀው ራሳቸው መሰረቁን ይጠቁሙናል። ራሳቸው ከሳሽ ይሆናሉ። ተከሳሽ፣ ምስክር ፣ ዳኛም ራሳቸው ይሆናሉ። ይህ በሆነበት ሰፈር እንዴት ሌብነት ሊጠፋ ይችላል ?

የእኛ ሰፈር እና የእድር ኃላፊ ግብዝነት የሚስተዋልበት በመሆኑ የሰፈራችንን ሰዎች ከማራቆት በዘለለ የሰፈራችን ህልውና የሆኑትን ካስማ እና ማገር የሚሰባብር እና ለዘመናት ስንገነባው የቆየነውን እድራችንንም የሚያፈርስ ነው።

በእኛ ሰፈር ያሉ ሌቦች መዝረፋቸው ብቻ አይደለም ሰፈራችንን እየጎዳ ያለው። ይልቁንም ስለመስረቃቸው በመረጃ እና በማስረጃ ሲደረስባቸው ስርቆታቸውን ለመሸፋፈን ወይም ለማደባበስ ጎሳን እና ሃይማኖትን እንደ ሽፋን መጠቀማቸው እንጂ። ይህ አካሄድ በብሔር ብሔረሰቦች እና በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ቅራኔ ከመፍጠር ባለፈ እስከደም መፋሰስ እንዳደረሰ በተደጋጋሚ አይተናል። በቅናት በምቀኝነት፣ ከላይም ከታችም ብሎ መቧደን እንደማይጠቅም አይተናል። እንጥላለን ያሉ ሲወድቁ፣ የጠሉትን ሲወርሱ አስተውለናል። ክፋት የእጅን ይከፍላል እንዲሉ ሌላው ከዚህ መማር አለበት።

ይህንን አባባል በአንድ የትንሽየ የገጠር ከተማ የተፈጠረ እውነተኛ ታሪክን እንደምሳሌ ተጠቅሜ ላሳያችሁ፡፡

በአንድ ወቅት በአንድ በትንሽዬ የገጠር ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አንድ መነኩሴ እና አንድ ጠላ በመሸጥ ልጆቿን የምታስተምር እናት ነበሩ።

በትንሿ የገጠር ከተማ የሚኖሩት መነኩሴ እና ጠላ ሻጯ እናት በጣም ይቀራረባሉ። ክፉና ደጉንም በጉርብትና ለዘመናት አብረው ማሳለፍ የቻሉ ነበሩ። መነኩሴው ጠላ ሻጯን እናት አብዝተው ይወዷታል። ሶስት ልጆችን ያለ አባት ጠላ ሸጣ እያሳደገች ብለውም ያዝኑላታል። በዚህም ፈጣሪ ኑሮዋን ያስተካክላት ዘንድ አብዝተው ይጸልዩላታል፡፡

ይሁን እንጂ ጠላ ሻጯ እናት አጋጣሚ ሆኖ ለመሸጥ የጠመቁት ጠላ ባልተሸጠ ጊዜ ይሄ የፀሐይ ቆብ ያደረገ መነኩሴ ምናምን ስለሚያደርግብኝ እያሉ መነኩሴውን ይወነጅሉ ነበር።

አንድ ቀን ጠላ ሻጯ እናትም እኚህን መነኩሴ ካልገደልኩ ጠላዬ መሸጥ አይችልም ብለው ይደመድማሉ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ጠላ ሻጯ እናት ለመነኩሴው ሽሮ ወጥ በላይ በላዩ የተቸለሰበት እንጀራ በትሪ እና በደቂቃዎች መግደል የሚችል መርዝ የተጨመረበት በማንቆርቆሪያ የሞላ ጠላ ያመጡላቸዋል። መነኩሴውም የዘወትር ጸሎታቸውን ሳይጨርሱ ኖረው ጸሎታቸውን እስኪጨርሱ ድረስ ጠላውን እና እንጀራውን ከድነው አስቀመጡ ።

ይህ በእንዲህ እያለ በጠዋቱ ፈረቃ ሲማሩ የዋሉ የጠላ ሻጯ ሶስት ልጆች ከትምህርት ቤት ይመለሳሉ። ሶስቱም ልጆች መነኩሴውንም እንደአባታቸው ይመለከቱ ስለነበር ከትምህርት ቤት መልስ ሁሌም ወደቤታቸው የሚሄዱት መነኩሴውን ካገኙ በኋላ ነበር። እንደተለመደው በዚህ ቀንም የጠላ ሻጯ ልጆች መነኩሴውን ሰላም አረፈዱ አባባ እያሉ ወደ መነኩሴውን ለመሳም ወደ መነኩሴው ቤት አመሩ።

መነኩሴውም የሶስቱንም ልጆች ከሳሙ በኋላ ከጭቃ ከተሰራቸው መደብ መቀመጫ ላይ እንዲቀመጡ አዘዟቸው። ልጆችም የመነኩሴው ነገር ስለማይሆንላቸው በመነኩሴው ቤት ገብተው ይቀመጣሉ። መነኩሴውም ልጆቹን እናታችሁ ካመጣችው ጠላ እና ምግብ ካልቀማሳችሁ ብለው አጥብቀው ይለምኗቸዋል። ልጆቹም መነኩሴውን ያከብሯቸው ኑሮ እናታቸው ካመጣችው ጠላ እና ምግብ ተካፍለው በሉ፤ ጠጡ።

ልጆቹ ግን አንድ እርምጃም እንኳን ሳይንቀሳቀሱ በያሉበት ተዘረሩ። በሁኔታው የተደናገጡት መነኩሴም ጭንቅላታቸውን ይዘው ኡ...ኡ... ብለው ጮሁ። የመነኩሴውን ጩኸት የሰሙ የትንሿ የገጠር ከተማ ነዋሪዎችም «አባ ምን አጋጠመዎት» እያሉ ወደ መነኩሴው ቤት አቀኑ። መነኩሴው ቤት በደረሱ ወቅትም የጠላ ሻጯ ልጆች መሬት ላይ ተዘርረው አገኙ።

የሰፈር ሰዎችም የወደቁትን የጠላ ሻጯን ልጆች አፋፍሰው ወደ ሐኪም ቤት ወሰዷቸው። ነገር ግን መትረፍ የቻለው አንደኛው ልጅ ብቻ ነበር። ሁለቱ ሞቱ።

ልብ በሉ! በሰዎች ላይ ያልሆነ ነገር ተቧድኖ ፤ ከኋላቸው ለመውጋት መስራት ትርፉ ራስን መጉዳት ነው። መጨረሻውም የጠሉትን መውረስ መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

የእናንተው ውድ እናት የተስፋዋ ምድር ብሎ ደብዳቤ ማንበቡን ሲጨርስ የሰፈራችን ሰዎች ወፈፌው ይልቃል አዲሴን በጭብጫባ ሸኙት።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ዓሊ ቢራ የሁለገብነት ፈር ቀዳጅ

**ዋስልኝ አየለ**

ስለ ዓሊ ቢራ የሙዚቃ ችሎታና ተወዳጅነት ከኦሮምኛ ተናጋሪዎች ያላነሰ የአማርኛና የሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ሲያወሩ እንሰማለን። የሙዚቃ ጣዕም የሚያውቁ ሰዎች እንዲህ ናቸው። ውስጣቸው በሙዚቃ ሀሴት የሚያደርገው በግጥሞቹ ሳይሆን በዜማውና ቃናው ነው። ለሙዚቃ ግጥም ሁለተኛ ጉዳይ ነው። ‹‹ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ›› የተባለውም ለዚህ ነው፡፡

ሙዚቃን ለመልዕክት የምንጠቀመው ከሙዚቃ ራቅ ያልን ሰዎች ነን። እንዲህ አይነት ሰዎች ምናልባትም ትኩረት የሚያደርጉት ግጥሙ ላይ ሊሆን ይችላል። ለዚህም ነው ዘፈኖችን ለፍቅረኛ ስሜትን ለመግለጽ ወይም የፖለቲካ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የምንጠቀማቸው፡፡

ለሙዚቃ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ግን መጀመሪያ የሚያጣጥሙት ዜማ እና በውስጡ ያሉ ለእኛ የማይገቡን ሌሎች መለኪያዎቹን ነው።

የሙዚቃ ነገር ረቂቅ ነው። ‹‹ምኑን ወደዳችሁት?›› ብንባል መለኪያው ላይገባን ቢችልም፤ የግጥሞቹን ትርጉም በማናውቀው ቋንቋ የተዘፈኑ ዘፈኖችን እያጣጣምን እንሰማለን።

ይህን ለማለት የፈለኩበት ምክንያት የዓሊ ቢራ ዘፈኖች የዘፈነባቸውን ቋንቋዎች የማያውቁ ሰዎች እንኳን ተመስጠው ሲሰሙት ስለማይ ነው። ‹‹ሰው ከሞተ በኋላ ነው የሚመሰገን›› የሚል ብሂል ቢኖረንም ዓሊ ቢራ ግን በሕይወት እያለ ብዙ ተመስግኗል። ብዙ አድናቂዎች የእሱን ሙዚቃዎች ሰምተው እንደማይጠግቡ በሕይወት እያለ ነው ሲያወሩ የሰማነው፡፡

**ስመሆኑ ዓሊ ቢራን እንዲህ ተወዳጅ ያደረገው ምንድነው?**

ይህን ጥያቄ መመለስ የሚችለው የሙዚቃ ባለሙያው ሰርፀ ፍሬስብሐት ነው። ጅማ ዩኒቨርሲቲ ባለፈው ቅዳሜ ታኅሳስ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ‹‹ዝክረ ዓሊ›› በሚል የዓሊ ቢራን የሙዚቃ ሕይወት የሚዘክር መድረክ አዘጋጅቶ ነበር። በመድረኩ ላይ በርካታ ዝግጅቶች ቀርበዋል። ሌሎችን ለሌላ ቀን እንተዋቸውና ለዛሬው የሰርፀ ፍሬስብሐትን ማብራሪያ እናካፍላችሁ።

‹‹ዓሊ ብዙ ሰው ነው›› ይላል ሰርፀ። በፎክሎር ዓይን ቢታይ ብዙ የባህል ተመራማሪዎች መድረክ አዘጋጅተው ሊወያዩበትና ሊመክሩበት የሚችል ነው። የቋንቋ ሰዎችና የፍልስፍና ሰዎች አገላለጹና ፍልስፍናው ላይ መድረክ አዘጋጅተው ሊወያዩ ይችላሉ። የሙዚቃ ሰዎች ስለድምጹ (ቮካል)፣ አሬንጅመንት ሰፊ ውይይት ሊያደርጉበት ይችላሉ። በሁሉም ዘርፎች ለህትመት የሚሆኑ የጥናት ውጤቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

እንደ ሰርፀ ገለጻ፤ ዓሊ ዲስኮግራፊ(discography) ሊዘጋጅለት ይገባል። ዲስኮግራፊ ማለት የአርቲስቱን ሥራዎች ዝርዝር ከነ ሙሉ መረጃቸው በፈርጅ በፈርጅ የሚያስቀመጥ ሰነድ ማለት ነው።

ወደ ዓሊ የሙዚቃ ሕይወት ቅኝት ሲገባ ‹‹የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች የሁለገብነት ምዕራፍ በዓሊ መሀመድ ቢራ ፈር ቀዳጅነት›› በሚል ርዕስ ነው። ‹‹ሙዚቃ የምክንያታዊነትንና የቋንቋን ድንበር ትጥሳለች›› የሚባለው ‹‹ሙዚቃ የዓለም ቋንቋ›› የሚለውን የተለመደ አባባል ለመግለጽ ነው።

እንደ ሰርፀ ማብራሪያ፤ እነዚህ አባባሎች የዓለምን የሙዚቃ ባለሙያዎች ሲያከራክሩ የቆዩ ናቸው። የፍልስፍና እና የሙዚቃን ግንኙነት የወዳጅነትና የፀብ ሲያደርጉት ቆይተዋል።

ሙዚቃ የምክንያታዊነትን ድልድይ ከጣሰች በቀጥታ ከፍልስፍናዊና ከሃይማኖታዊ ሞራል አስተምህሮ ጋር ትጣላለች። የቋንቋን ድንበር ከጣሰች ደግሞ የገጣሚውን ቦታ አጠያያቂ ታደርጋለች ወይም ዋጋ ታሳጣለች። በዜማ ብቻ ትልቅ ሀሳብ መገለጹ ነው ማለት ነው።

ከዚህ ሁሉ ጥሰት ከወጣች ግን ሙዚቃ በጂኦግራፊና በባህል ዓውድ ውስጥ ብቻ የመደመጥ ዕድሏን ወደተሻለ ደረጃ ታሳድጋለች። ገጣሚውን፣ ፈላስፋውንና የባህል ሞራል ጠባቂውን ከጣሰች በኋላ ደግሞ የዓለም ቋንቋ ትሆናለች።

የኢትዮጵያ ሙዚቃ ከጥንት ሲያያዝ በመጣ ባህሪው፤ ሀሳብ ተሸካሚነቱ፣ የግጥም ምሉዕነቱ ያመዝናል። አንድ ኢትዮጵያዊ ሙዚቃ ወይም ዘፈን አዳመጥኩ ሲል በአብዛኛው ግጥም አዳመጥኩ ማለቱ ነው። የዜማው፣






**የኢትዮጵያ ሙዚቃ ከጥንት ሲያያዝ በመጣ ባህሪው፤ ሀሳብ ተሸካሚነቱ፣ የግጥም ምሉዕነቱ ያመዝናል። አንድ ኢትዮጵያዊ ሙዚቃ ወይም ዘፈን አዳመጥኩ ሲል በአብዛኛው ግጥም አዳመጥኩ ማለቱ ነው። የዜማው፣ የሙዚቃው ፎርም እና ሌሎች ጓዞች የመጀመሪያ ትኩረቱ አይደሉም**

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇

የሙዚቃው ፎርም እና ሌሎች ጓዞች የመጀመሪያ ትኩረቱ አይደሉም። ኢትዮጵያዊ አድማጭ ከቃል ወደ ድምጽ የሚሸጋገር የሙዚቃ ትኩረቱ በይበልጥ ያመዝናል።

ወደ ምዕራቡ ዓለም ከሄድን ግን የሙዚቃ አድማጭ ከሙዚቃ ሀሳብ ጋር የሚገናኘው የሙዚቃውን ፎርም፣ ቅማሬውን፣ እና የድምጽ መዋቅሩን በትኩረት በማዳመጥ ይሆናል። የቃል ዋጋ ቀጥሎ የሚመጣ ቁም ነገር ነው። መጀመሪያ ሙዚቃው ነው የሚነካን።

በዚህ መሰረት የምዕራባውያን ሙዚቃ የማድመጥ ባህል ከድምጽ ወደ ቃል ሲሆን የኢትዮጵያ ግን ከቃል ወደ ድምጽ ነው። ይህን ልዩነት የሚሰብሩ ሰዎች ግን አሉ። እነዚህም ከቃል ወደ ድምጽ እና ከድምጽ ወደ ቃል የሚሄደውን ጉዞ አደናጋሪ አድርገው ሙሉ በሙሉ የሙዚቃቸው ምርኮኛ የሚያደርጉን ድምጻውያን አሉ። እነዚህ ድምጻውያን ፍጹም የቃል ዋጋን ሳናስተውል፣ ቋንቋ ሳይገድበን፣ ትርጉም ሳያስፈልገን የምናዳምጣቸው ናቸው። እነዚህ ድምጻውያን ለተፈጠሩበት የሙዚቃ ዓለም ሁለገብ (universal) የሚባሉ ናቸው።

እነዚህ ድምጻውያን የሚጠቀሙትን የሙዚቃ ፎርም በዓለም ላይ ያለ ሙዚቃ የሚወድ ሰው ሁሉ ሊያዳምጠው የሚችል ጣፋጭ ቃና ይሰጡታል። ያ ቃና ነው ተደማጭነታቸውን የሚያሳድገው፡፡

ከአፍሪካ ውስጥ እንኳን ማሪያ ማኬባን መጥቀስ እንችላለን። የዙሉ ጎሳ ጨዋታዎችን ነው የምትጫወተው፤ ግን ‹‹አፍሪካ›› የሚል ከፍታ ነው የተሰጣት። ማሪያ ማኬባ ይህን ያህል የተወደደችው ቋንቋውን በማስተርጎም አይደለም። ስሜታችንን መቆጣጠር የቻለ ድምጽ እና አዘፋፈን ስላላት ነው።

እንደ ሰርፀ ገለጻ፤ በዚህ ልኬት ነው ዓሊ መሀመድ ቢራን የምናስቀምጠው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በታላቅነቱ ያከበረበት ምክንያት በዚህ የሙዚቃ ስሌት ነው። አንድ የዓሊ ቢራ አድናቂ ‹‹ለምን እንወደደው ቢጠየቅ እኔ ያልኩትን ላይል ይችላል›› ብሏል ሰርፀ። ይህ የብዙዎቻችን ችግር ነው። አንድን በጣም የምንወደውን ዘፋኝ ምኑን እንደወደድነው ብንጠየቅ ምናልባትም ከግጥሙ ውጭ ሌላው ላይገባን ይችላል፤ ግን ሰፍ ብለን ነው የምንሰማው።

‹‹ዓሊ ወርቃማ ድምፅ ያለው ነው›› ይላል ሰርፀ ማብራሪያውን ሲቀጥል። በተለይም በወፍራም ድምጾች የሰራቸው ሙዚቃዎች ወደ ‹‹ቤዝ ሬንጅ›› ወርዶ የሰራቸው ናቸው። ወደ ‹‹ሃይ ሬንጅ›› የሚወጡ ሙዚቃዎቹ አሁን ላሉ የዘመኑ ድምጻውያን ዛሬ ድረስ የቮካል ፈተና የሆኑ ናቸው።

ዓሊ ከሌሎች የኦሮምኛ ድምጻውያን በተለየ የሁለገብነት ተቀባይነት ሊያገኝ የቻለበት ሁለት ምክንያቶችን ያብራራል ሰርፀ። የመጀመሪያው፤ ዓሊ የሚጫወትባቸው የሙዚቃ ስልቶች በሌሎች አገሮች ባህሎች ወይም ለኢትዮጵያዊ አድማጭ አዋሳኝ ከሆኑ የምሥራቁ ኢትዮጵያ ባህሎች የፈለቁ መሆናቸው ነው።

ሁለተኛው ምክንያት፤ የዓሊ እግጅ የተሟላ ሙዚቃዊ ስብዕና ነው። የሙዚቃ ስብዕናው ግልጽና ያልተወሳሰበ ነው። ድምጽ አወጣጡ በጣም ቀላል ነው፤ ቀላል በሆነ አቀማመጥ ነው የሚያስቀምጣቸው። ወጣ ገባ እና ጥምዝምዝ አይበዛባቸውም። ብዙ ሰው ‹‹ቀላል›› ሲባል ተራ ወይም ዝቅተኛ ማለት ይመስለዋል። በሙዚቃ ውስጥ በጣም ከባዱ ሥራ ቀላል ነገር ማስቀመጥ ነው። ሰዎች እየሰሩ ሲሄዱ በረጅም ጊዜ ሊያገኙት የሚችሉት መታደል ነው። ዓሊ ምክንያታዊ ኖት ነው የሚያወጣው። ድምጽ አማረልኝ ብሎ ምክንያታዊ ያልሆኑ ኖቶችን አይነካካም። ይህን ያመጣለት የጥበብ ዕውቀቱ ነው፡፡

ለብዙዎች የዓሊ የሙዚቃ ስልት በኦሮምኛ ውስጥ ብቻ ያለ ሊመስላቸው ይችላል። የሙዚቃዎቹን ባህላዊ ቅርጽ ካየነው ግን በበርካታ ባህሎች ውስጥ የሚገኝ የሙዚቃ ስሪት ነው ያለው። ይህን ብዝሃ መልክ ደግሞ ያገኘው ብዝሃ ባህል ባለበት ምሥራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ማደጉ ነው። ለሙዚቃ በተሰጠው ተሰጥዖ ላይ ይህ የምሥራቅ ኢትዮጵያ አስተዳደጉ ሲጨመርበት የሙዚቃ ሕይወቱን ከፍ አደረገው።

የምሥራቅ ኢትዮጵያ (ሐረሪ) ባህል መገለጫው በርካታ ነው። ለባህሉ ይህን አይነት መልክ መያዝ ደግሞ ከመካከለኛው ምሥራቅ እና ከአንዳንድ የአውሮፓ አገራት ጋር ቀደም ሲል የነበረው የንግድ፣ የባህልና የሃይማኖት ግንኙነት ነው። ስለዚህ በተለመደው የሰሜን ኢትዮጵያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አይነት ሙዚቃዎች የምንረዳው አይደለም። ከመካከለኛው ምሥራቅ የሚቀዳ ቅርጽ አለው።

ዓሊ በኦሮምኛ ብቻ ሳይሆን በሶማሊኛ፣ በሱዳንኛ፣ በሐረሪኛ የሚጫወታቸውን ዜማዎች በሐርሞኒክ ማይነር ሙዚቃዊ ስልት የተከተሉ ናቸው። አንዳንድ የኦሮምኛ ሙዚቃዎቹ በሌሎች የኦሮሞ አካባቢዎች (በወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሰላሌ) ከምንሰማቸው ፈጽሞ የተለዩ ናቸው። የተለዩ የሚሆኑበት ምክንያትም በምሥራቅ ኢትዮጵያ በማደጉ ነው፡፡

ሰርፀ እንደሚለው፤ የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሙዚቃ እንደ ዘመናዊ የሙዚቃ ተቋማቱ ዘመን ተሻጋሪ ያደረጉት ግለሰብ ሙዚቀኞች ናቸው። ከተቋማቱም በላይ የሙዚቀኞች ታሪክ ዘመን ተሻግሮ እንደ ዓሊ ከ50 ዓመት በላይ በስኬት የተጓዙ ይሆናሉ። ከ1950ዎቹ በፊት እንደ ዓሊ የሁለገብነትን ተሰጥዖ የተጎናፀፈ ሙዚቀኛ ብዙም አልነበረም። ድምጻዊ ከሆነ ድምጻዊ ነው፤ ምናልባት ዜማ ሊጨምር ይችላል። የመሳሪያ ተጫዋቾች ከሆነ የመሳሪያ ተጫዋቾች ነው። ዓሊ ግን በሁሉም የተሳካለት ሰው ነው።

ዓሊ የገባበትን የክቡር ዘበኛ የሙዚቃ ቡድን ጨምሮ በሌሎች የጥበብ ተቋማት ውስጥ በድምጻዊነት የተቀጠሩትን ታላላቅ ድምጻውያን በሙዚቃ የተሟሉ ለማድረግ ሲባል የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን እንዲማሩ አስገዳጅ ትዕዛዝ ወጥቶባቸው ነበር። ለምሳሌ ጥላሁን ገሠሠ የሙዚቃ መሳሪያ እንዲማር ደብዳቤ ተጽፎበት ነበር። እሱም የሰጠው መልስ ‹‹እኔ ድምጼ ይበቃኛል›› የሚል ነው።

ሁለገብ ተሰጥዖ ያላቸው በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው። እንደ ዓሊ ቢራ፣ ጌታቸው ካሳ፣ ግርማ በየነ፣ አለማየሁ እሸቴ ያሉት ናቸው የሙዚቃ መሳሪያ መጫወት የሚችሉ። እነዚህ ሙሉ የሙዚቃ ሰው ሊባሉ ይችላሉ።

እንዲያውም ዓሊ ቢራ ዛሬ በድምጻዊነት ከመታወቁ በፊት በኢትዮጵያ ሬዲዮ የሶማሊኛ ፕሮግራም ስቱዲዮ መጥተው ይቀረጹ የነበሩ የሶማሊኛ ድምጻውያንን በጊታርና ሌሎች መሳሪያዎች በማጀብ ትልቅ አስተዋፅዖ ነበረው። ይሄ ብዙ ያልተነገረለት ታሪኩ ነው። በኢትዮጵያ ሬዲዮ የተቀዱ የመጀመሪያ የሶማሊኛ ሙዚቃዎች ዓሊ ቢራ በጊታር እያጀባቸው የተሰሩ ናቸው።

የዓሊ የሙዚቃ ተፈጥሮ በዜማና ግጥም ደራሲነት፣ በድምጻዊነት፣ በሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋችነት፣ በሙዚቃ አቀናባሪነት አካቶ በመያዝ የክዋኔ ተሰጥዖንም አጎናጽፎታል። ዓሊን ‹‹ፕሮዲዩሰር›› ማለትም ይቻላል። በተለይም ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ የሰራቸው ሥራዎች ሙሉ የስቱዲዮ ጣጣቸው የራሱ ነው።

ሰርፀ እንደሚለው፤ የዓሊ የሙዚቃ ሕይወት ሲጠቃለል፤ ከሙዚቃ ሕይወት ውጭ ሌላ ማንነት የሌለው ነው። ከሙዚቃ ሥራ ለመውጣት ሞክሮ አያውቅም፤ እስከ ሕይወት ፍጻሜው ድረስ ከማይክ ጋር ነበር። ሲመቸው ሳይሆን ሳይመቸውም ሙዚቃ ሲጫወት የኖረ ሰው ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የህገ ወጥ ስደት ሰለባዎች

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ውስጥ የሚሳተፍ ሰው ጉዞውን የሚያደርገው የተሻለ ሕይወትና ኑሮ ፈልጎ ነው። እኔም የሄድኩበት ምክንያት ይሄው ነው›› የምትለው ሰሚራ አብደላ ከአንድም ሦስት ጊዜ በዚሁ መንገድ ከአገር በመውጣት ደቡብ ሱዳን፤ ደቡብ አፍሪካና ቤሩት የሚገኙ ግለሰቦች ቤት ተቀጥራ ስትሰራ መቆየቷን ታስታውሳለች።

‹‹ሆኖም መጀመሪያ ላይ ከአገር ወጥቼ ደቡብ ሱዳን የሄድኩበት ሕገወጥ መንገድ ቀላል አልነበረም›› የምትለው ወጣቷ ድንበር አሻግርሻለሁ ብሎ ቀብድ 10 ሺህ ብር የተቀበላት ደላላ መፈጠሯን እስክትጠላ ድረስ መከራ እንዳሳያት ታስታውሳለች።

‹‹የገጠር ልጅ ነኝ። ያኔ በእጄ ላይ ያለው ብር 10ሺህ ብር ነበር። እሱንም አባቴ ለማዳበርያ ብሎ ካስቀመጠውና ከእህል ሽያጭ ላይ የሰጠኝ ነው›› ትላለች። ይሄን እንድታደርግ የገፋፋት አንድ ከሌሎች በሕገ ወጥ መንገድ ለሥራ ብለው ወደ ውጭ ከሚልኩ ደላሎች ጋር በመተባበር እርሻ ማሳ አካባቢ እየተዘዋወረ የአርሶ አደሩን ልጆች የሚያስኮበልል ደላላ እንደነበርም ታስታውሳለች።

ገንዘቡ በአውሮፕላን ለመሄድ ስለማይበቃ በመኪና የሚወስዳት እንደሆነና ሱዳን ስትደርስ ሁሉንም ብር የምትከፍል መሆኑን መንገድ ሲጀምሩ ነግሯታል። ግን 10ሺህ ብሩን ከተቀበለ በኋላ ገንዘቡ አይበቃም በሚል ገንዘቡን እስኪታሚይ በማለት ለ15 ቀናት መንገዳቸውን በመግታት የማታውቀው ሥፋራ ደብቋት ቆይቷል። የተደበቀችበት ቦታ ምቹ ካለመሆኑም በላይ በርካታ ስቃይ ደርሶባታል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ቤሩት እንዳለች አድርጋ እየደወለች አባቷ 40 ሺህ ብር እንዲልኩ ከመጠየቅ ጎን ለጎን የያዘችው ቀለብ በማለቁ ‹ምግብ ለሥራ› በሚል በርካታ ከአቅሟ በላይ የሆነ ሥራ ሲያሰራት ቆይቷል። ቀን ሙሉ ልብስ ስታጥብ፤ የተለያዩ አድካሚ የጉልበት ሥራዎችንም ስትሰራ ትውላለች።

በብዙ ጭቅጭቅ አባቷ ብሩን ልከውላት መንገድ ከቀጠለች በኋላ ለሌላ ስቃይ ተዳረገች። አሰልቺ የሆነ የእግር ጉዞ ማድረግ አንዱ ግዴታ ነበር። እንደ ገሀነም እሳት ከሚለበልበው በረሃ፤ ከውሃ ጥምና ረሀብ ጋር ተዳምሮም ራሷን እንድትስት አደረጋት። ሆኖም በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ እያለች ቱሪስቶችን ታገኛለች። በእነዚህ ቱሪስቶች አማካኝነት ያሰበችበት ደቡብ ሱዳን ብትደርስም ያየችው ፈተና ቀላል አልነበረም።

ሌላኛዋ የህገወጥ ስደት ሰለባ ወይዘሮ የሺእመቤት ክንፉ ናቸው። በህገወጥ መንገድ ከአገር ወጥተው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ለረጅም ዓመታት ሲሰሩ መቆየታቸውንና ብዙ መከራ ማሳለፋቸውን ይጠቅሳሉ። ደቡብ አፍሪካ ከቆዩባቸው ዓመታት የተወሰነውን በእስር ማሳለፋቸውንም ያስታውሳሉ። ወይዘሮዋ አሁን ላይ መንግስት ይሄን የዜጎች ስቃይ ታሳቢ አድርጎ በሕጋዊ መንገድ ከአገር በመውጣት ሰርቶ መኖር የሚቻልበት መንገድ ማመቻቸቱን በበጎ መልኩ ያዩታል።

ሆኖም በሕገወጥ መንገድ መሄድ ዜጎችን ለአስከፊ ስቃይ ይዳርጋል የሚሉት ወይዘሮ የሺእመቤት በሕገወጥ መንገድ የሄደ ያሰበበት ደርሶም ቢሆን ወደ አገር መመለሱ ቀላል ባለመሆኑ በአሰሪዎችና በተለያየ መንገድ የሚደርሱ አስከፊ ችግሮች ችሎ መቆየት ግድ መሆኑን ይናገራሉ። ከተቻለ በአገር ውስጥ የተገኘውን ሰርቶ መኖር ይመረጣልም ብለዋል።

አቶ ደረጀ ፈቅይበሉ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕገወጥ ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል አስፈፃሚ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት አሁን ላይ እነ ሰሚራና ወይዘሮ የሺእመቤት ከአገር በወጡበት ዓይነት መንገድ የወጡ ከ300 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ደቡብ አፍሪካ ውስጥ እንዳሉ ይገመታል። ከነዚህ ውስጥ 80 በመቶዎቹ የመኖሪያ ፈቃድ ያላገኙና በሕገወጥ መንገድ የሚኖሩ በመሆናቸው ለመብት ጥሰትና ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ መሆናቸው ታውቋል።




‹‹በርካታ ዜጎች ታንዛንያና ዛምቢያን አቋርጠው ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚሄዱበት መንገድ አለ›› ይላሉ አቶ ደረጀ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪ ከኬንያ፤ ዙምባቤ፤ ሞዛምቢክ፤ ታንዛንያ በርካታ ሰዎች በህገወጥ መንገድ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንደሚገቡና ተይዘውም በእስር እንደሚገኙም ያወሳሉ። ዛምቢያ ላይ ብቻ ከአምስት ሺ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በሕገወጥ መንገድ ለመሸሽ ሞክረው እስር ቤት ውስጥ እንደሚገኙ አቶ ደረጀ ተናግረዋል። በጅቡቲ አድርገው ሳዑዲ አረቢያ መዳረሻ አድርገው የሚሻገሩም ብዙ መቶ ሺ ዜጎች መኖራቸውን ያስረዳሉ።

እነዚህን ወደ አገር የማስመለሱ ሥራ የዜጋ ተኮር ፖሊሲ ውጤት መሆኑን አቶ ደረጀ ያነሳሉ። እንዳከሉት በዚህ መሰረት ከሳውዲ መንግስትና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከሚያዝያ 2014 እስከ ነሀሴ 23 ቀን 2104 ድረስ 71 ሺህ ዜጎች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተደርጓል። ከዚያ በኋላም 18 ሺህ ተመላሾች የመጡ ሲሆን እስካለፈው አርብ 84ሺህ 258 ዜጎችን ወደ አገራቸው መመለስ ተችሏል። ከመጡት ውስጥ 12ሺ 326ቱ ወይም14 ነጥብ 62 በመቶው ሴቶች ናቸው። 71ሺሀ 923 ቱ ወይም 85 ነጥብ 3 በመቶው ደግሞ ወንዶች ሲሆኑ ከነዚህም መካከል 361 ህፃናት 43ቱ ደግሞ እዛ ከሄዱ በኋላ በደረሰባቸው ችግር አካል ጉዳተኞች የሆኑ ዜጎች ናቸው።

ዜጎች በሕገወጥ መንገድ ወደ እነዚህ አገራት ከሚሄዱባቸው ምክንያቶች የኢኮኖሚ ችግር፤ የደላላ ግፊትና በየአገራቱ ባሉ ሳቢ ጉዳዮች መሆናቸውንም አቶ ደረጀ ያወሳሉ። ሆኖም ወደ ውጭ ለመሄድ የሚከፍሉት ገንዘብም በአገራቸው ላይ ሰርተው መለወጥ የሚያስችላቸው ከፍተኛ ጥሪት መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ለአብነት ከጠቀሱት አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ለመሄድ ከ380 ሺህ በላይ፤ ወደ አፍሪካና ኢዢያ ለመሄድ ከ250 ሺ ብር በላይ፤ መክፈል ይጠበቅባቸዋል። አነስተኛ ክፍያ የሚጠይቁት እንደ ደቡብ ሱዳን ያሉ መካከለኛው ምስራቅ አገራት ሲሆን ደቡብ ሱዳን ለመሄድ እስከ 40 ሺህ ብር ያወጣሉ ብለዋል።

ድርጊቱን ለመከላከልና ለማስቆም መንግስት ሊቢያ ላይ ከተፈፀመው ድርጊት በኋላ በጉዳዩ ዙርያ ሕጎች እንዲወጡ አቋም ይዞ በሰዎች መነገድና በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ለመከላከል አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ማውጣቱንም ያነሳሉ። አዋጁ እየተተገበረ መሆኑንም አውስተዋል።

‹‹ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውርና ድንበር ማሻገር ተግባር ላይ በተሰማሩ ደላሎች አማካኝነት በዓለማችን ከ2 እስከ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች የአስከፊው የሕገወጥ ዝውውር ተግባር ሰለባ መሆናቸውን ጥናቶች ያመለክታሉ። በየዓመቱ በአማካኝ 700 ሺህ ሰዎች ለሕገወጥ የወሲብ ንግድ ይዘዋወራሉ። እ.ኤ.አ ከ2001 እስከ 2002 ባለው ጊዜም ብቻ ዕድሜያቸው ከ5 እስከ 6 የሚደርሱ ሴት ህጻናት ለወሲብ ንግድ ሥራ እንደቀረቡና ከነዚህ ውስጥም 50 ሺው ሴቶችና ህፃናት አፍሪካውያን መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

# ዓለም አቀፍ



ኤፍ-35ኤ የጦር አውሮፕላን

## እስራኤል ከአሜሪካ ገዝታው የነበረውን የጦር አውሮፕላን ከአገልግሎት ውጪ አደረገች

**በጋዜጣዉ ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ እስራኤል ከአሜሪካ ገዝታው የነበረ ኤፍ 35ኤ ስያሜ ያለው የጦር አውሮፕላን ደህንነቱ አስተማማኝ ባለመሆኑ ከአገልግሎት ውጪ ማድረጓን ቢቢሲ አስነበበ።

አሜሪካ ሰራሽ የሆነው ኤፍ-35ኤ የጦር አውሮፕላንን ከገዙት እና ከታጠቁት አገራት መካከል እስራኤል አንዷ ናት።

ይህ ዘመናዊ የጦር አውሮፕላን ባሳለፍነው ሳምንት በአሜሪካ ቴክሳስ የውጊያ ትዕይንት በማሳየት ላይ እያለ እክል እንደገጠመው ሮይተርስ ዘግቧል።

አውሮፕላኑ የቴክኒክ እክል ያጋጠመው መሬት ላይ ለማረፍ እየሞከረ እያለ የመከስከስ አደጋ ደርሶበታል ተብሏል።

አውሮፕላኑ ያጋጠመው አደጋ ተጨማሪ ምርመራ ያሚያስፈልገው እንደሆነ የእስራኤል አየር ኃይል እንደወሰነ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

በዚህም ምክንያት የጦር አውሮፕላኑ ደህንነት እስኪረጋገጥ ድረስ ከእስራኤል አየር ኃይል ሲስተም ውስጥ እንዲወጣ መደረጉ ዘገባው ያመላክታል።

በእስራኤል ጦር ስር ያለው ይህ የውጊያ አውሮፕላን በቴክሳስ የተፈጠረው አይነት አደጋ እንዳይከሰት ስጋት እንዳለበትም ተገልጿል።

ከ10 ወራት በላይ ያስቆጠረው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ከሁለቱ አገራት በተጨማሪ በእጅ አዙር የሚሳተፉ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ ይገለጻል።

ኢራን ሰው አልባ የጦር አውሮፕላን ለሩሲያ እየሰጠች ነው የተባለ ሲሆን ዩክሬን እስራኤል የአየር ላይ ጥቃት ማምከኛ የጦር መሳሪያ እንድትረዳት ጠይቃለች።

ሩሲያ በበኩሏ እስራኤል ከዩክሬን የቀረበላትን ጥያቄ እንዳትቀበል ያስጠነቀቀች ሲሆን እስራኤልም በይፋ የዩክሬንን ጥያቄ ውድቅ ማድረጓ ይታወሳል።

## አልሸባብ በኬንያ ጥቃት መሰንዘሩ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ አልሸባብ በኬንያ ገጠራማ የባህር ዳርቻ በሰነዘረው ጥቃት ሁለት ሰዎችን ሲገድል በርካታ ቤቶች ማቃጠሉ አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

ጥቃቱ የተፈፀው በፈረንጆቹ አዲሱ ዓመት ማታ አካባቢ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ2015 ጀምሮ ሰፋፊ ኦፕሬሽኖች ሲካሄድ በነበረው በአጎራባቹ ቦኒ ጫካ ፓንዳጉ በሚባል ገጠራማ አካባቢን መሰረት በማድረግ ነው። የአልሸባብ ታጣቂዎች በአከባቢው በስፋት ሲንቀሳቀሱ እንደ ነበርም በዘገባው ተገልጿል፡፡

ጫካው የሚገኘው በኬንያ እና በሶማሊያ ድንበር አቅራቢያ ሲሆን ታጣቂዎቹ ባለፉት ዓመታት ጫካውን ተገን በማድረግ ጥቃት ሲፈጽሙ ቆይተዋል።

እንደ ፖሊስ ዘገባ፣ ጥቃት አድራሾቹ በወቅቱ የቱሪስት መዳረሻ የሆነችው በለሙ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኘው ተዓ መንደር ወርረው በርካታ ቤቶችን አቃጥለዋል። ነዋሪዎቹም ጥቃቱን በመፍራት ቤታቸውን ለቅቀው ሸሽተዋል፡፡

የባህር ዳርቻው አካባቢ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጆን ኢሉንጋታ አጥቂዎች በመንደሩ ላይ በሌሊት ጥቃት ማድረሳቸውንና በኬንያ ፖሊስ በወሰደው እርምጃ በኋላ መመለሳቸውን ተናግረዋል።

“ሁኔታው የተረጋጋ ነው፣ በአካባቢው የሚዘዋወሩ ኦፊሰሮች አሉን እና እነሱን ማደናችንን ስንቀጥል የህብረተሰቡ አባላት ለምርመራችን እንዲረዱን የሚያውቁትን እንዲነግሩን እንጠይቃለን። ሲሉ ኮሚሽነር ጆን ኢሉንጋታ ተናግረዋል፡፡

አንድ የአልሸባብ ታጣቂ መሆኑ የተጠረጠረው ግለሰብ ከሳምንት በፊት በምዕራብ ኬንያ በከፈተው ተኩስ ሁለት ሁለት የኬንያ የጸጥታ አካላትና ንጹኃን ዜጎች ከገደለ በኋላ ጥቃት አድራሾቹ ከሳምንቱ



የኬንያ ወታደሮች ጥቃት አድራሾች ላይ እርምጃ ሲወስዱ

በኋላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመፈጸም ወደ ከተማይቱ መግባታቸውም ተገልጿል።

ኬንያ የአልሸባብ እንቅስቃሴ ለመግታት ከ2015 ጀምሮ ከሶማሊያ ጋር ያላትን ድንበር በግንብ እየሰራች ትገኛለች። የፕሮጀክት እቅዱ የኢሚግሬሽን እና የጉምሩክ መግቢያ ነጥቦችን በሲሲቲቪ ካሜራ የተገጠመ የኮንክሪት ግድግዳ መኖሩን ያካትታል። በአካባቢውም ቦይም እየተገነባ ሲሆን ዕቅዱ ለማንኛውም አይነት ጥቃት ምላሽ ለመስጠት ቢያንስ 22 የድንበር ቦታዎችን በጥሩ ሁኔታ የታጠቁ ሰራተኞችን መፍጠርን ያካትታል።

ባለሥልጣናቱ እንደተናገሩት ሥራዎቹ ሲጠናቀቁ 40 ኪሎ ሜትር (25 ማይል) ርቀት ድረስ በመሄድ በታጣቂዎች ለሚሰነዘሩ ጥቃቶች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ያስችላል። በተለይ በማንዴራ እና ለሙ ያለው አጥር ቀደም ሲል እንደፈለጉ ያቋርጡ የነበሩ ታጣቂዎች ለመግታትና የሚደርሱባቸውን ጥቃቶች ለመቀነስ ረድቷል። በመንግስት የጸጥታ ኤጀንሲዎች በተደረገው ጥናት 30 በመቶ የሚሆነው የኬንያ ጸጥታ ችግር ከሶማሊያ ድንበሮች ጋር የተያያዘ ነው ተብሏል።

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም የሱፍ ሀሰን መሐመድ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-58129 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር WDB2100071BOO8108 ሞዴል 210 የሞተር ቁጥር 61196130160522 የሊብሬ ቁጥር 394514 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 19/4/2015 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም እንዳለ ደስታ ወ/ሚካኤል የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-62251 የተሽከርካሪዉ አይነት ሌላ የሻሲ ቁጥር WJMM1lRH004190354 ሞዴል 400ET የሞተር ቁጥር 8210.42L*460-439132* የሊብሬ ቁጥር 0227832/0235538 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የአ/ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ ገነት ተስፋዬ እና በፍ/ባለዕዳ እነ አቶ ካሳሁን ተስፋዬ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 276490 ቀን 15/3/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 243197 በ30/11/2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኘ የቤ.ቁ 1537 የሆነ ካርታ ቁጥር 14/01-11-15-30-5517/01 የሚታወቅ ስፋቱ 175 ካ/ሜ የሆነ ቤት የይዞታ ስፋት 175 ካ/ሜ የሆነ ቤት ይዞታው 175 ካ/ሜ ካርታቸው ላይ 9.60 በቀጣይ መንገድ ጥናት ተግባራዊ ሲሆን 3 ሜትር የሚቀነስ በመሆኑ ተጠቃቃሽ መዝገብ ያለበት የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 573,600(አስምት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ለጥር 30 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል:: የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00.ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቁ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል:: ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም:: በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት::

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚ4 ጥያቄዎችን የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስምና አድራሻ: SEARA ALIMENTOS LTDA አድራሻ: Avenida Marginal Direita do Tietê, 500 - São Paulo - São Paulo - Brazil | | |
| 2 | ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀንና የማመልከቻ ቁጥር FTM/13594/2022 ቀን 2022-7-28 | | |
| 3 | pena branca الريشة البيضاء | 4 | የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ: የምስል እና የቃል |
| | | 5 | የቀለም አይነት ብራይት እና ነጭ |
| | | 6 | አለም አቀፍ ምድብ 29 |
| 7 | አለም አቀፍ ምድብ. 29: ስጋ፣ አሳ፣ ዶሮ እና ጌን፣ የስጋ ውጤቶች፣ ሳይበላሹ እንዲቆዩ የተደረጉ የቀዘቀዙ፣ የደረቁ እና የበሰሉ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች፣ ጄሊዎች፣ ጃሞች፣ ኮምፖቶች፣ እንቁላሎች፣ ወተት፣ አይብ፣ ቅቤ፣ እርጎ እና ሌሎች የወተት ምርቶች ፣ ለምግብ ዘይቶች እና ፋቶች፡፡ | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ ጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 110 20 /4/2015 (29 /12/2022)**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስምና አድራሻ: AstraZeneca UK Limited አድራሻ: 1 Francis Crick Avenue Cambridge Biomedical Campus Cambridge, United Kingdom CB2 0AA | | |
| 2 | ማመልከቻው ቁጥር FTM /13907 / 2022 ቀን 2022-11 -30 | | |
| 3 | ZOLADEX | 4 | የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ፡ የቃል |
| | | 5 | የቀለምአይነት ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6 | አለም አቀፍ ምድብ 5 |
| 7 | አለም አቀፍ ምድብ 5: የመድሀኒት ዝግጅቶችና የካንሰር መድሀኒቶች፡፡ | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡: ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ ይህ ጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOL LXXXII NO 110 20 /4/2015 (29 /12/2022)**

Safaricom
ሳፋሪኮም

## የዳታ ማዕከል ነዳጅ ክትትል ሲስተም ለሚዘረጉ ድርጅቶች የወጣ የፍላጎት መግለጫ ማስታወቂያ

### 1. መግቢያ

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የኔትወርክ ዝርጋታና የማስፋፋት፣ በየክልሉ ቢሮዎች ከፍቶ የመሥራት፣ ሱቆችን እንዲከፍትና ከቴሌኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ጋር የተያያዘ የተቀናጀ አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ አግኝቷል፡ በመሆኑም ሰብስክራይበሮችንና የድርጅት ደንበኞችን ታሳቢ አድርጎ የእነሱን ፍላጎት ለማሟላት አልሞ እየሠራ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት ሳፋሪኮም ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የተለያዩ ቁሳቁሶችንና አገልግሎቶችን ከሚያቀርቡ ብቁ አጋሮች ጋር አብሮ መሥራት ይፈልጋል፡

በመሆኑም ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ የዳታ ማዕከሎች የነዳጅ ክትትል ሲስተም ለማቅረብ የሚችሉ ብቁ አገልግሎት ሰጪዎችን ማሠራት ይፈልጋል፡፡ አገልግሎቱን ማቅረብ የሚፈልጉ ድርጅቶች የፍላጎት መግለጫቸውን እንዲያስገቡም ይጠይቃል፡፡

### 2. ስለ ፍላጎት መግለጫው

ይህ የፍላጎት መግለጫ ያስፈለገው ከታች የተጠቀሱትንና ተያያዥ አገልግሎቶችን ጨምሮ በሳፋሪኮም የዳታ ማዕከል ውስጥ የነዳጅ ክትትል ሲስተም ለመዘርጋት ብቃትና አቅም ያላቸውን አገልግሎት ሰጪዎች ለመለየት ነው

1. በናፍጣ ለሚሠሩ ጀኔሬተሮች በነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች የተቀመጠ ነዳጅ መጠንን በሊትርና በመቶኛ (በፐርሰንት) ምን ያህል እንደሆነ ክትትል የሚያደርግ ሲስተም በሳፋሪኮም የኔትዎርክ ኦፐሬሽን ማዕከል ማስገባት፣
2. የሚዘረጋው ሲስተም ቢያንስ አምስት የተለያዩ የነዳጁን መጠን የሚያሳዩ መንገዶችን የያዘ መሆን አለበት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ዝቅተኛ ነዳጅ (30 በመቶ ሲደርስ) እና በጣም ዝቅተኛ ነዳጅ (15 በመቶ ሲደርስ) የሚያሳይ የማንቂያ አመላካች መሆን አለባቸው ሲስተሙ በመቶኛ የሚገለጸው ዝቅተኛው የነዳጅ መጠን ሊስተካከል (ሊለዋወጥ) የሚችልና ከየትኛውም ቦታ ሆኖ ወደ ቁጥጥር ማዕከሉና ዋና የሥራ ቡድኖች ቢያንስ በኢሜይል የሚያሳውቅ መሆን አለበት፣
3. የሚሠራው ሲስተም በዜሮና በ100 መካከል ከፍተኛው የነዳጅ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በሌትርና በመቶኛ የሚያሳውቅ መሆን አለበት፣
4. አሁን በሥራ ላይ ያለው የዳታ ማዕከል የክትትል ሲስተም በህዋዌ ኔትኢኮ (NetECo) ሲስተም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱን የሚሰጠው ድርጅት የሚሠራው የነዳጅ ክትትል ሲስተም አሁን በሥራ ላይ ካለው ሲስተም ጋር ተናቦ የሚሠራ መሆን አለበት፣
5. ለሶፍትዌሩ ማናቸውም ልዩ የፈቃድ መሥፈርቶች ካሉ መገለጽ አለበት፣
6. ለነባር የሳፋሪኮም የናፍጣ ነዳጅ ማጠራቀሚያዎች የክትትል ሲስተም የመሥራት ችሎታ መኖሩን ማሳወቅ፣
7. አጠቃላይ የነዳጅ ክትትል አገልግሎት የሚሰጥ ሲስተም ማቅረብ

ከነዳጅ ክትትል ሲስተም ጋር የተያያዙ ዝርዝር የአገልግሎቱ መግለጫዎች ይህንን የፍላጎት መግለጫ አስገብተው አገልግሎቱን ለመስጠት ይችላሉ ተብለው ለተመረጡና በጨረታው ለሚሳተፉ ድርጅቶች በሚቀርበው የፕሮፖዛል ጥያቄ ውስጥ ተካቶ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### 3. ተጫራቾች ማሟላት ያለባቸው መሠረታዊ መሥፈርቶች

| ተ.ቁ | መሥፈርቶች |
|---|---|
| 1 | የድርጅቱ ዝርዝር መግለጫ (ፕሮፋይል)፣ በኢትዮጵያ የተመዘገበበት ሕጋዊ ሰነድ፣ የምዝገባ ሰርተፍኬት፣ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር መከፈያ መለያ ቁጥር፣ (ቲን ነምበር) እና የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ |
| 2 | ድርጅቱ የነዳጅ ክትትል ሲስተሙን በራሱ የማይሰራ ከሆነ ወይም ተመሳሳይ ሲስተም የማስመጣት ወይም የማከፋፈል ልምድ ከሌለው በአገር ውስጥ የነዳጅ ክትትል ሲስተም መስራት መቻሉን የሚገልጽ የፍቃድ ማስረጃ ማቅረብ |
| 3 | የነዳጅ ክትትል ሲስተም በመሥራት የተመዘገበ የሥራ ልምድ |
| 4 | የድርጅቱ ዋና ቢሮ የሚገኝበት አድራሻ |
| 5 | አገልግሎት ሰጪው የነዳጅ ክትትል ሲስተም ያቀረበላቸውና እየተጠቀሙበት ያሉ ድርጅቶች ዝርዝር |
| 6 | አሁን አገልግሎት እያገኙ ያሉ ድርጅቶች ዝርዝር |
| 7 | የድርጅቱ ቁልፍ ሠራተኞችን ስም እና ያላቸውን የቴክኒክ ብቃት የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ |
| 8 | ከታች በተራ ቁጥር አራት በተቀመጠው መሠረት የሳፋሪኮም መሥፈርቶችን ሊያሟላ የሚችል ቴክኒካል ፕሮፖዛል ማቅረብ |
| 9 | ያለፉት ሁለት ወይም ሦስት ተከታታይ ዓመታት የሒሳብ ሪፖርት |
| 10 | ድርጅቱ ሳፋሪኮም የግድ ማወቅ አለበት ብሎ የሚያስበውን ማንኛውም ሲስተሙን የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ |

### 4. ቴክኒካዊ መሥፈርቶች

ፍላጎት ያላቸው አገልግሎት ሰጪዎች በተራ ቁጥር ሁለት በተቀመጠው መሰረት የተለያዩ የነዳጅ ክትትል ሲስተም አይነቶችን አካተው ከዚህ የፍላጎት መግለጫ ጋር መላክ አለባቸው

### 5. የፍላጎት መግለጫው አላላክ

አገልግሎቱን ለመስጠት ፍላጎት ያላቸው የፍላጎት መግለጫቸውን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም. ከ 11፡00 ሠዓት ድረስ በኢሜይል አድራሻ bids@ safaricom.et መላክ አለባቸው፡፡

### 6. በቀጣይ የሚከናወኑ ተግባራት

የፍላጎት መግለጫዎች ለሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ከደረሱ በኋላ ኩባንያው የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1. የተላኩትን የፍላጎት መግለጫዎች ይገመግማል
2. ከተላኩት የፍላጎት መግለጫዎች ውስጥ ቅድመ መሥፈርት ያሟሉትን ይለያል
3. ቅድመ መሥፈርት ያሟሉ በጨረታ እንዲሳተፉ ያደርጋል
4. ጨረታውን ላሸነፈው ሥራውን ይሠጣል

**ማስታወሻ**

1. ዝቅተኛውን መሥፈርት ያሟሉ አገልግሎት ሰጪዎች ለቀጣይ ውይይት ይጋበዛሉ
2. ከዚህ የፍላጎት መግለጫ ጋር ዋጋ መካተት የለበትም

**ማሳሰቢያ**

ሳፋሪኮም ቴሌኮሙኒኬሽን ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ጨረታውንም ሆነ የተጫራቾችን የፍላጎት መግለጫ ወይም የአገልግሎት መነሻ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ለማድረግና ለመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ድርጅቱ የሚያሳልፈው ውሳኔ የሚፀና ሲሆን፣ ለተጫራቾች የጨረታውን ውጤት ከማሳወቅ ውጪ በሌሎች ምልልሶች እንዲሳተፍ አይገደድም፡ ሳፋሪኮም ቴሌኮሙኒኬሽን ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወይም እንደ ሳፋሪኮም ቴሌኮሙኒኬሽን ኢትዮጵያ ሆኖ እንዲሰራ ህጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል ከዚህ ማስታወቂያ ጋር በተያያዘ የተላኩ ማስረጃዎች ላይ ጥያቄ የማቅረብም ሆነ የማመሳከር ኃላፊነት አለበት

**ሳፋሪኮም**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አትሌቲክስ በመጪው የፈረንጆቹ ዓመት

ብርሃን ፈይሳ

በቀጣዩ ሳምንት መጀመሪያ በሚያዘው የፈረንጆቹ ዓመት 2023 በስፖርቱ ዓለም በርካታ ውድድሮችና ሁነቶችን ለማከናወን መርሃ ግብር ተይዞላቸዋል። ዓመቱን ሙሉ ውድድር የሚካሄድበት አትሌቲክስ ደግሞ በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ በተሰጠው የዚመን ማራቶን ሲጀመር፤ አህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ደግሞ ከቀጣዩ ወር አንስቶ ቀጥሎ የሚከናወኑ ይሆናል። በአትሌቲክስ ስፖርት ታዋቂ የሆነችው ኢትዮጵያም በዓመቱ የዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ታደርጋለች በሚል ይጠበቃል።

የዓለም አትሌቲክስ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ከተጋፈጡ ስፖርቶች መካከል አንዱ ሲሆን፤ በርካታ ውድድሮችን ለማራዘምና ለመሰረዝ አስገዳጅ የሆነበትን ጊዜ አሳልፏል። በዚህም ምክንያት ስፖርቱን የሚመራው የዓለም አትሌቲክስ፤ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው ዓመት 2022 ችግሩን ለመቅረፍ በርካታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። በጊዜ ሰሌዳው መሰረት ውድድሮችን ወደ ቀድሞ ቅርጻቸው ለመመለስ የሚያደርገው ጥረት በአዲሱ ዓመትም እንደሚቀጥል ያብራሩት ደግሞ የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ሰባስቲያን ኮ ናቸው። በዓመቱ ከሶስት በላይ ታላላቅ ውድድሮች እንደሚከናወኑ የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ ያለፉት ሁለት ዓመታት ስፖርቱን በአዲስ መልክ የመንደፍ ያህል እንደነበረና አሁንም ጠንካራ ስራ እንደሚጠብቃቸውም ትራክ ኤንድ ፊልድ ኒውስ ለተባለው ድረገጽ ገልጸዋል።

በዓለም አትሌቲክስ በተያዘው መርሃ ግብር መሰረት መጪው የየካቲት ወር የዓለም ሀገር አቋራጭ ውድድር በአውስትራሊያ ለ44ኛ ጊዜ ይካሄዳል። ይህ ውድድር ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በግልና በቡድን ስኬታማ ከሆኑባቸው መካከል አንዱ ሲሆን፤ ጀግናው ቀነኒሳ በቀለ ደግሞ 6 የወርቅ ሜዳሊያዎችን በግሉ በመሰብሰብ በውድድሩ ታሪክ ውጤታማ አትሌት ነው። ከሁለት ወር በኋላ በሚካሄደው ውድድር ላይም ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች የሚመረጡበት የጃንሜዳ ሀገር አቋራጭ ውድድር በመጪው እሁድ ታኅሣሥ 23 ቀን 2015 ዓ.ም ይከናወናል።

በዓመቱ በተለይ ከሚጠበቁ ታላላቅ ስፖርታዊ ውድድሮች መካከል አንዱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነው። ከኦሊምፒክ እና ከዓለም እግር ኳስ ዋንጫ በመቀጠል ልዩ ትኩረት የሚሰጠውና በርካታ ሀገራት የሚሳተፉበት ይህ ቻምፒዮና ለመጀመሪያ ጊዜ በተከታታይ ዓመት (2022 እና 2023) ይደረጋል። ኦሊምፒክ ከመካሄዱ አንድ ዓመት አስቀድሞ እንዲሁም በተከታዩ ዓመት የሚደረገው ይህ ውድድር በዓለም አቀፉ ወረርሽኝ ኮቪድ 19 ምክንያት የቶኪዮ ኦሊምፒክ ለአንድ ዓመት መራዘሙን ተከትሎ በተፈጠረ የመርሃ ግብር መደራረብ ቻምፒዮናው በወራት ልዩነት እንዲካሄድ አድርጎታል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ ሀገራት የሩጫ፣ የውርወራ እና የዝላይ ተወዳዳሪዎቻቸውን የሚያፎካክሩበት ይህ ውድድር ከወራት በፊት በአሜሪካዋ ኦሪጎን መከናወኑ የሚታወስ ነው።

እአአ በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ የሚደረግ በመሆኑም ቻምፒዮናው በዋዜማው በሃንጋሪዋ ከተማ ቡዳፔስት የሚከናወን ይሆናል። 200 የሚሆኑ ሀገራት በሚሳተፉበት በዚህ ውድድር ኢትዮጵያ ሰፊ ተሳትፎ ሲኖራት፤ ከመድረኩ 29 የወርቅ፣ 30 የብር እና 26 የነሃስ በድምሩ 85 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ በሰንጠረዡ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። በኦሪጎን በተካሄደው ቻምፒዮና ከአሜሪካ ቀጥሎ ሁለተኛ ሆና ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው። በመሆኑም በዚህ ውድድር ላይም በድጋሚ የሀገራቸውን ስም ለማስጠራት ሯጮቿን የምታሳትፍ ይሆናል።

ሌላኛው የዓመቱ ተጠባቂ ዓለም አቀፍ ውድድር ደግሞ የጎዳና ላይ ሩጫዎች ቻምፒዮና ነው። የግማሽ ማራቶን፣ 5ኪሎ ሜትር እና የአንድ ማይል ሩጫን የሚያጠቃልል ሲሆን፤ ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝባዊ ሩጫንም እንደሚያካትት የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል። ውድድሩም በተረኛዋ የውድድሩ አዘጋጅ የላቲቪያ ዋና ከተማ ሪጋ ይደረጋል። እአአ በ2020 ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በግልና በቡድን አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡበት ይህ ውድድር፤ በአዲሱ ዓመትም ድል የሚመዘገብበት ይሆናል በሚል ይጠበቃል።

ከቀናት በኋላ በሚገባው የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት የዓለም አትሌቲክስ ከሚመራቸው ውድድሮች ባሻገር፤ ዳይመንድ ሊግ፣ አህጉር አቀፍ የቱር ውድድሮች፣ የቤት ውስጥ ቱር እንዲሁም በተለያዩ የዓለም ሀገራት በሚከናወኑ የማራቶንና ሌሎች የጎዳና ላይ ውድድሮች የሚቀጥልም ይሆናል።

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም

**INVITATION TO NATIONAL COMPETITIVE BID**

**FLOATING DATE: AS OF JANUARY 2, 2023**
**CLOSING DATE: AS OF JANUARY 25, 2023**
**RFQ NO. 4188300-2**

1. Ethio telecom intends to sign a Master Frame Agreement (MFA) contract for one (1) year with a possibility of extension up to a maximum of 3 years with the finally awarded bidder(s).
2. Hence, we are pleased to invite all interested and eligible bidders by this **Open National Competitive Bid (NCB) for the Procurement of PVC U Elbow with RFQ No. 4188300-2.** The Tender remains floating from **January 2, 2023,** to **January 25, 2023.**

| *S.NO* | *Description of Items* | *Order Qty* | *UoM* | **Bid security amount(Birr)** | **RFQ No.** |
|---|---|---|---|---|---|
| *1* | PVC U Elbow | 5000 | Pcs | 20,000.00 | **4188300-2** |

Bid documents can be obtained from ethio telecom's web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr ***100.00 (Birr One hundred only)*** by using tele birr payment platform.
In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp.ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".
3. Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/, www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com
   a. **Sealed bids marked as**: "Tender for the Supply of **Procurement of PVC U Elbow with RFQ No. 4188300-2** and be addressed to:
   **Ethio telecom,**
   **Head Quarter**
   **Supply Chain Division**
   **2nd Floor, Room No.211B,**
   **P. O. Box 1047,**
   **Addis Ababa, Ethiopia**
   b. Bid proposal will be received at ethio telecom, **Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on January 25, 2023 5:00 P.M.** Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.
4. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives **on January 26, 2023, at 10:00 A.M, at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No.210.**
5. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.

**Ethio Telecom**

ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም

**INVITATION TO NATIONAL COMPETITIVE BID**
**FLOATING DATE: AS OF JANUARY 2, 2023**
**RFQ NO. 4187299-2**

1. Ethio telecom invites all interested and eligible bidders by this **National Competitive Bid (NCB)** for the procurement of **Pavement work at Bole with RFQ No. 4187299-2** The Tender remains floating from **January 2, 2023.** Bid documents can be obtained from ethio telecom's web sites www.afrotender.com, www.extratenders.com and www.2merkato.com upon payment of a non-refundable fee of Birr ***100.00 (Birr One hundred only)*** by using **tele birr payment platform**.
In addition, If you are interested to be on the supplier list of ethio telecom please register using the following link or copy and paste the link on a browser "https://erp. ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".
2. Interested eligible bidders may obtain further information from ethio's website (i.e. https://www.ethiotelecom.et/tender/ , www.afrotender.com, www.extratenders.com, www.2merkato.com and in person from Head Quarter, 2nd Floor, and Room No. 201B
   a. Sealed bids marked as: "Tender for the procurement of **Pavement work at Bole** with RFQ No. 4187299-2 and be addressed to:
   **Ethio telecom,**
   **Head Quarter**
   **Supply Chain Division**
   **2nd Floor, Room No.211B,**
   **P. O. Box 1047,**
   **Addis Ababa, Ethiopia**
   b. Bid proposal will be received at ethio telecom, **Head Quarter 2nd Floor, Room No. 211B, Before or on January 23, 2023 5:00 P.M.** Bids presented by any bidder after the closing date shall not be accepted.
3. Bids received in time and fulfilling the other formalities shall be opened in the presence of interested bidders or their legal representatives **on January 24, 2023** at **10:00 A.M,** at ethio telecom, Head Quarter 2nd Floor, Room No. 210
4. Ethio telecom reserves the right to reject all or parts of this bid.
5. **Partial bid is not allowed**

**Ethio Telecom**